በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት
በአማርኛ
በየሁለት ወር የሚታተም

የካቲት/መጋቢት ፲፱፻፹፰

፬ኛ ዓመት ቁጥር ፬
$2.75

# ላንዳፍታ



ቡናችንን ለዓለም ገበያ በማቅረብ
ይታወቁ የነበሩት
ቀኛዝማች ከድር ኤባ

# LANDAFTA

*An Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine*
*(Amharic is the official language of Ethiopia)*
February/March 1996
Vol. 4. No.4

- ልብ ወለድ
- ኑሮ በአሜሪካ
  ፍቅርና ጋብቻ በአሜሪካ
- አዳምና ሔዋን
  "ሶማዬ"
  "እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!"

# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE

### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

1996 — 1996

# ካሊፎርኒያ ማርት
# በአትላንታ

## CALIFORNIA MART *IN ATLANTA*

2080 CHESHIRE BRIDGE ROAD
ATLANTA, GA 30324

**የምግብ ሸቀጣሸቀጥ**
**GROCERIES**

እንጀራ — Injera
ጤፍ — Teff
በርበሬ — Berbere
ሽሮ — Shirro
ወዘተ

**የተለያዩ ሸቀጦች**
**መደብር**
**አራት ዓይነት ንግድ**
**በአንድ ቦታ**

**የመዝናኛ ክፍል**
**GAME ROOM**

ካራምቡላ — *Biliard*
የጠረጴዛ ኳስ — *Table Tennis*
ሙዚቃ — *Music*
ልዩ ልዩ መዝናኛዎች

ይደውሉልን




ይጎብኙን

**የስጦታ መደብር**
**GIFT SHOP**

ስጦታዎች — *Gifts*
ጌጣጌጦች — *Jewelery*
ወዘተ

**4 BUSINESS IN 1**

**ምግብ ቤት**
**RESTAURANT**

ቁርስ — ፉል፤ ግንፍልፍል፤
ምሣና እራት — ክትፎ፤ ጥብስ፤
ወዘተ

Mail Order Available
Please, call for Arrangements

(404)320-6747
(404)320-9082

CAPPUCCINO
ESPRESSO

ORDER FOOD
TO GO!!

# ማ ው ጫ CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከአገር ቤት (ከወርቃየሁ)

6 ሰላምታ ከባህር ማዶ ከይግለጡ ለወርቃየሁ

8 እንዲህ ሆነ (ዜና)

10 ጥንቅር - ከዚህም ከዚያም

14 ልብ ወለድ
"ድንቄም ተሞሸረች" በዛብህ ገ.የሰ

17 ለቅምሻ
"ተራማጅነት" ከጳውሎስ ኞኞ
"አቢሳ" ሰይፉ መኩሪያ

19 የትብብር ውጤት
የሲኖዶሱ ስብሰባና ውጤት
የሳንዲያጎ ገብሬል በዓል

22 ቡናችንን በዓለም ገበያ ... ቀ.ከድር ኤባ

26 ኑሮ በአሜሪካ
"ከኢምንት ማህደር" አንዋር መሃመድ
"ነግ በኔ" ዮ ሐንስ ገ.ሕ.
ፍቅርና ጋብቻ በአሜሪካ ዮሐ ንስ ገ.ሕ.)

37 አዳምና ሔዋን
"ዕጣዬ" (አብርኸት)
"እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!" (አትናትዮስ)

44 ስፖርት

45 እናስላው! ሰይፉ መኩሪያ




የሲኖዶሱ ስብሰባ (21)



ቀኛዝማች ከድር ኤባ (22)



የአትላንታው የዩናይትድ ታክሲ ኩባንያ ባለቤቶች በከፊል (19)

ሽፋን ቀኛዝማች ከድር ኤባ


"ላንዳፍታ" የግል መጽሄት ናት። የሚወጡ ጽሁፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሁፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪ ዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሃፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የገጠመኝና የፈጠራ ድርሰት ጽሁፎች ህጋዊ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን እንገልጻለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1996

# ከአዘጋጁ

እንደምን ከረማችሁ። እኛ ደህና ነን። ይኸው ብቅ ብለናል። በዚህ እትም እንዳለፈው ሁሉ የተለያዩ ጽሁፎቻችንን ይዘን ቀርበናል። አገራችንን ኢትዮጵያን በተለያዩ መስኮች ለዓለም ሕዝብ ያስተዋወቁትን አባቶቻችንን ማስታወሱ ተገቢ ነው በሚል የአገራችንን ዋንኛ የኤክስፖርት ምርት ቡናን ለዓለም ገበያ ከጥንት ጀምሮ በማስተዋወቅ ዝነኛ የነበሩትን የቀኛዝማች ከድር ኤባን ታሪክ በአጭሩ አቅርበናል። ባለፈው ዓመት በሞት የተለዩንን የታዋቂው ስፖርት ሰው ይድነቃቸው ተሰማን የቅርብ ጓደኛ የቀኛዝማች ከድር ኤባን ታሪክ ስናቀርብ አንድም በንግዱ ዓለም ያን ያህል ታዋቂነትን ለማትረፍ እንዴት እንደቻሉ ለአሁኑ ትውልድ ትምህርት ይሆናል ከሚል ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በኤኮኖሚው አውታር አገራችንን ለማበልጸግ ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረጉና ታሪኮቻቸው የማይታወቁትን ውድ ኢትዮጵያውያን ለማስታወስም ጭምር ነው። ታሪክ ተጽፎላቸው የምናያቸው ባብዛኛው በፖለቲካው መስክ የተሳተፉትን ሰዎች ብቻ ነው። በስፖርት፣ በሙዚቃ፣ እንዲሁም በምርምር የታወቁ ሰዎች በመጠኑም ቢሆን የተጻፈላቸው ነገር አለ። ለአገር ብልጽግና ትልቅ ሚና የተጫወቱ የግብርና ምርትና የንግድ ሰዎችን ታሪክ መጻፉ ልምዱ እምብዛም ስለሌለ ብዙዎቹ ተረስተው ቀርተዋል። ይህ ያቀረብነው አጭር ዘገባ ይህንን ልምድ እንድንጀምር ይገፋፋል የሚል እምነት አለን።

ወርቃየሁ ከአገር ቤት ይግለጡም ከዚህ ከአሜሪካ ደብዳቤ ተለዋውጠዋል። "ፍቅርና ጋብቻ በአሜሪካ" በተሰኘ ርዕስ ዮ ንስገ.ሕ. ባለፈው እትም የጀመሩትን ጽሁፍ አስፋፍተው አቅርበውልናል። አብረኸትም የኑሮ "ዕጣዋ" ያደረሰባትን የፍቅር ታሪክ ካለፈው የቀጠለውን አቅርባለች። አትናትዮስም ሚስት ለማግኘት ባደረገው ዘመቻ የገጠመውን ታሪክ በተከታታይ አሁንም አቅርቦልናል። እንግዲህ ድግሱ ከኛ ቀርቧል፤ እናንተስ እንላለን።

በዓለም ጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ትልቅ ምዕራፍ የያዘው የአድዋ ድል መቶኛ ዓመት በሚቀጥለው ወር ይከበራል። ይህንኑ ታሪካዊ በዓል ምክንያት በማድረግ በሚቀጥለው እትማችን ሰፋ ያለ ዝግጅት ይኖረናል። ታሪኩን በተመለከተ እንዲሁም ግጥሞችና አስረጅ ጽሁፎች ያላችሁ በአስቸኳይ እንድትልኩልን እንጋብዛለን።

ላንዳፍታ የምትገኘው በዘንድሮው የኦሎምፒክ ከተማ በአትላንታ ስለሆነ በዚህም ላይ ሰፋ ያለ ዝግጅት ስለሚኖረን ጽሁፎቻችሁን እንጠብቃለን።


የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
(404) 728-9122
E-MAIL- mgessesse@aol.com



ላንዳፍታ
ህዳር / ታህሣሥ ፲፱፻፹፰
፬ኛ ዓመት ቁጥር ፫
LANDAFTA
Feb/March 1996 V. IV- No.3



አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Assistant Editors:**
*Workayehu (pen name)*
*Girma Zegeye*

**Contributors:**
*Seifu Mekuria*

**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*

**Distribution**

Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Tailoring

Chicago, IL
Ethio-Village Rest.

Dallas, TX
Maru Grocery
ET. Beauty Supply

L.A., CA
Merkato
Damera

Oak Land, CA
Albo-African Shop

San Diego, CA
Emebet Worku

San Jose, CA
St. Claire news Stand

Seatle, WA
Addis Cafe

St. Louis, MO
A & Z Liquor

St. Paul, MN
Merkato

Tampa, FL
Ibex Ethiopian restaurant

Washington D.C.
Addisu Gebeya
Family Food Market
Merkato Market
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)

Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu



Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone/Fax
(404)728-9122
E-MAIL
mgessesse@aol.com



*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

እንደምን ከርማችኋል? እንኳን ለአዲሱ አመት፣ ለጌታችን ለመድሃኒታችን ለእየሱስ ክርስቶስ የልደት በአልና የጥምቀት በዓል አደረሳችሁ!! ለመሆኑ እንዴት ናችሁ? ኑሮና ብልሃቱስ እንዴት ይዟችኋል? እኛ ደህና ነን። መድሃኒያለም ክብሩ ይስፋ! ገናን፣ ከተራን፣ ጥምቀትን በየአድባራችን አክብረናል። እናንተስ አዲሱ አመት እንዴት ይዟችኋል? መቼም እናንተ ሁሌ ተደስታችሁ ተንበሻብሻችሁ የምትኖሩ ናችሁና የዓመታት መቀያየር የሚቀንስባችሁም ሆነ የሚጨምርላችሁ ነገር ባለመኖሩ የዘመን ከዘመን መለዋወጥን ከቁብ አትቆጥሩት ይሆን

> ዘመን ሳይለወጥ ዘመን ተለውጠ
> አለ ወይ ደስታ ሰው ሀገር ተቀምጦ።
> እንደዚህ ከሆነ የአዲስ አመት ዕጣ
> ምን ቁም ነገር አለው ቢመጣ ባይመጣ።

ትሉኝ ይሆን?

እኛማ የክረምቱን ዝናብ ትዝታ ገና ከህሊናችን ሳይወጣ የበጋው ዝናብ እንደገና መጣሁባችሁ መጣሁባችሁ እያለ ተቸግረናል። የዕርዳታ ስንዴ የለመደው የሀገሬ ገበሬ "እዚህ አይዝነብ ካናዳ ይዝነብ" ይላል። እግዜሩ ሰምቶ አንገቱን አዝሞብን ይሁን እንጃ አዝመራው ተሰብስቦ ጎተራ ሳይገባ ዝናቡ ያለጊዜው መጥቶ መጭውን ጊዜ በትካዜ እንድናስብ አድርጓል። በየገጠሩማ ተማሪው ትምህርቱን አቁሞ ውሎው አጨዳ፣ እህል ስብሰባ ላይ ነው አሉ። ምን ይደረግ? የህይወት ጉዳይ ነው ሳይበሉ መማር የለ! አንዳንዱ ደግሞ አዝመራው በወቅቱ ያልተሰበሰበው ኢህአዴግ በየገጠሩ የገበሬ ሚሊሽያ ምልመላ በመጀመሩና ውጣ ውረድ በመኖሩ ነው ይላል። 'የበላችው ያገሳታል በላይ በላይ ያጎርሷታል' እንዲሉ ያለብንን ችግር ገና ሳንቀርፍ ሌላ ሌላ ችግር ተደንቅሮብናል። ብቻ ይህ ሁሉ ሆኖ ደህና ነን እንላለን። ውለን ካደርን ደህና ነን ነው የሚባለው።

ሰሞኑን ደግሞ በሱዳን ተሰዶ የከረመው በብዙ ሺህ የሚቆጠር የደርግ ወታደር በሽሽት ከሄደበት ሀገር ተፈናቅሎ ከተማው ውስጥ ፈሷል። እንደገና በሀገሩ ላይ አዲስ ዜጋ ሆኖ ስብዕናውን ሽጦ ትልቁን አዲስ ዘመን ጋዜጣውን ዘርግቶ 'በሱዳን ይህን ያህል ዓመት በስደት ቆይቼ ተባረርኩኝ እና ይርዱኝ' ይሎታል፤ ያዘነ ሳንቲም ይወረውርለታል፣ አንዳንዱ ደግሞ እዛ ከምትፈረጥጥ በቅጡ አትዋጋም ነበር እያለ ገላምጦት ያልፋል። ያ አፈር ከመሬት ይደባልቅ የነበረ ጠብደል ወታደር ዛሬ ኮስምኖ አፍ የለው አይናገር በቁጭት ብቻ ከንፈሩን ይነክሳል።

'የእንትናን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም' ሆኖ ሰሞኑን የጀርመኑን ፕሬዚዳንት በጥሩ ጥበቃ ተቀበልናቸው። የከተማው ፖሊስና ትራፊኩም አንድ ሳይቀር አጋኒንክ ባትሉኝ በየ10 ሜትር ልዩነት ሁለት ሁለት ሆነው ሬድዮናቸውን ጆሮአቸው ላይ ደቅነው ሰውየው ያልፉበታል በተባለበት መንገድ ሁሉ መንገዱን እጥር አድርገው ወዴት ነህ? የት ነህ? ምን ታያለህ? ሲሉን ሰነበቱ። ያም ሆኖ ግን ባለፈው በግዮን ሆቴል ለ5 ሰዎች መሞት ምክንያት ሆኖ የፈነዳው ፈንጂና እንደገና ደግሞ የመገናኛው ሚ/ር ዶክተር አብዱል መጂድ ከጅቡቲው ልዑካን ጋር ስብሰባ ሲያካሂዱበት በነበረው ኢምፔሪያል ሆቴል በር ላይ ተሞክሮ የከሸፈው ፈንጂ አደጋ ሲታሰቡ ይሄ ጥበቃ ሲያንስ እንጂ የሚበዛበት አይደለም።

ወዳጆቼ እንደምን አላችሁ? ኧረ ጎበዝ! ስል እሽም ነው! የሚለኝ በማግኘቴ በጣሙን ተደስቻለሁ። እግዚአብሔር ያክብርልኛ! የሰው መውደድ ይስጥልኛ! ወዳጄ የአገሬ ልጅ! ባለፈው በፃፍክልኝ ላይ በአሜሪካ ጭልጥ ያለ ከበርቴ እና ጭልጥ ያለ ድሃ የሚኖርባት ሀገር ናት ብለኸኛል ባይገርምህ ኢትዮጵያችንም እንደዛው እየሆነች የመጣች ይመስለኛል። 'አሜሪካን ስታይል' መሆኑ ነው። ነገር ግን ምናልባት አንተ ድሀ የምትለው አንድ መጠነኛ ቪላ፣ አንድ መኪና፣ አንድ . . . ያለውን ይሆናል። እኔ ግን ድህነት የምለው የእኛን አገሩን መናጢ ድሀ የሚላስ የሚቀመስ የሌለውን ሲሆን በሌላ ጎኑ ደግሞ በእኛ ሀገር የከበርቴውን ዓለም እየፈጠሩ ያሉት የ"ዲሞክራሲው ልጆች"ና የትላንትናዎቹ "ታጋዮች" ዘንድ ነው። አፈጣጠሩ በሁለት በኩል ነው፤ አንደኛው የደቡብ ኮሪያውና የጃፓኑ ተሞክሮ በዝርፊያ (በነ እሱ ቋንቋ በሙስና) ሲሆን ሌላኛው ደግሞ እንደፖለቲካው ሁሉ የንግዱን መረብ በእያንዳንዱ የንግድ ዘርፍ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ በመዘርጋት ነው። ከጋዜጣ ችርቻሮ አንስቶ እስከ ትልቁ የንግድ ዘርፍ ድረስ በሁሉም ቦታ የእነዚሁ "የዲሞክራሲው ልጆች" የገቢ ምንጮች ናቸው። ዛሬ በከተማችን ስማቸው ገኖ የሚሰሙትና የሚታዩት እነ ጉና፣ እነ ሻላ፣ ሜጋ፣ ፋና፣ ... አክሱም ሆቴል፣ ... ኢንሹራንስ ካምፓኒ፣ አስጎብኚ ድርጅቶች . ሁሉ የከተማውን ንግድ በሞኖፖልና በማን አለብኝነት ይዘው ከተማውን በአንድ ጣታቸው እንደፈለጋቸው ያሽከረክሩታል። እነሱ እንደሌላው ነጋዴ ፈቃድ አይጠየቁ፣ የጉምሩክ ቀረጥ የለባቸው፣ ማዘጋጃ ደጅ አይጠኑ ምንአለፋችሁ እንዲሁ ብቻ መቻብቻብ፣ መሸምጠጥ፣ ማፈስ ነው፤ ባለ ጊዜ ናቸዋ!! ታዲያ በነፃ ኢኮኖሚ እጠቀማለሁ ብሎ ደፋ ቀና የሚለው ነጋዴ ያለቀረጥ ከገባው ዕቃ ጋር መወዳደር ያቅተውና በአጭር ጊዜ ውስጥ እያሽቆለቆለ ነፃውን በአፍጢሙ ሲደፋ የሚፈለገው ይኸው ነውና እነሱ እንደገና ከስር ተካ ይሉበታል።

ከአንድ ዘመዴ ጋር ስለዚሁ ስለ አንድ ጎሳ ከንድ አንስተን ስናወራ ነገሩ እየተጋጋለ ሄደና በጣም ተበሳጭቶ ማበሳለጡን በሌላ ልናየው እንችላለን። ነገር ግን በመልሶ ግንባታው ከአለም አቀፍ የረድኤትና አበዳሪ ክፍሎች የመጣው ፈጣን ዕርዳታና መልሶ ግንባታ መርሐ ግብር በሰሜኑ ክፍል ብቻ መሄዱን በጦርነት ለተጎዱትና ለተደመሰሱ ተቋማት ማገገሚያ በሚል ስሜት እንደሆነ ግልፅ ነው። ግን አሁን በትግራይ እየተገነቡ ያሉት ተቋማት በእርግጥ በጦርነት የተጎዱና የተደመሰሱ ናቸው? ኮሌጁ፣ ፋብሪካው፣ የኃይል ምንጩ፣ አውሮፕላን ማረፊያው፣ መንገዱ፣ . . . ሌላም ሌላም እውን በአውሮፕላን በቦንብ የተደበደበው ነው? በሁለትና በሶስት ዓመታት የሶስትና የአራት ኮሌጆች ባለቤት መሆን ለእኔም ለአንተም ቁልጭ ያለ የአድሎአዊነት ማስረጃ ነው። ከዚህም ውጪ በትግራይ ተወላጆች መዋጮ ይሰራሉ የሚባሉት ልማቶች ዞሮ ዞሮ የመንግስት ወገናዊ ዕጅ አሉበት። እዚህ ያለው ተወላጅ መክፈል እንዲችል ማበረታቻና ማጎልበቻ ይደረግለታል፣ ሹመት ያገኛል — ለዚያ ያዋጣል። ለምንድነው ይሄ ሁሉ ርብርቦሽ? ትግራይን አልምቶና ገንብቶ ለኤርትራ የሚደረገውን ዕገዛ አድርጎ በኋላ ምን ለማለት? በትግራይ ተወላጅነት ሽፋን እስፈላጊው ሁሉ ለውጪ አገር ዜጎች ሲደረግ . . . በአስተዳደር በኢኮኖሚውና እንዲሁም በስለላና በመከላከያ ትብብር ሲደረግ ይህ የኢትዮጵያ የኤርትራ ትብብር ወይም ግንባር ወይስ 'የትግራይ ትግሪኝ'? ደግሞስ 'የስጦታ ፈረስ ጥርሱ አይታይም' ወይም ተመፅዋች የሰጡትን ይቀበላል እንዲሉ ሆኖ እንጂ በኢትዮጵያ ያሉት የአሜሪካው አምባሳደር ትግራይ ሄደው ለልዩ ልዩ ስራ ማስፈፀሚያ የተቻለውን ያህል ሲረዱ ቆይተው በአ.አበባ በአሜሪካ መንግስት ዕርዳታ የተሰራ የህዝብ ንፅህና ቤት መርቀው መክፈታቸው እውን ለአ.አበባ ህዝብ አስበው አስበው ሌላ የሚረዱት ነገር አጥተው ነው? የአዲስ አበባ ሕዝብ መች . . . የሚያራግፍበት አጣሁ አለ? መጀመሪያው የሚበላው በተገኘና . . . ደግ ነበር። ዳሩ ጊዜውስ ለሆድ አድሮ በሆድ የሚኖርበት ቢሆን አይደል ያ የትግል አምባ የነበረው የስድስት ኪሎ ዩንቨርስቲ ተማሪ ሁሉን ረስቶ ለሆዱ መጮህ የጀመረው? 'አገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል' ይኋል ይሄንን ነው ብሎ አፈጠጠብኝ።

ወዳጄ ይግለጡ! የእኛ መጨረሻ ዳር የለውም አልከኝ! አንተ ስለሩብ ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ ስሜት ያውም እዛ በሰው አገር አዩኝ አላዩኝ ብሎ አንገቱን ደፍቶ የሚኖረው ይቅርና እዚህ ያለው እንኳ ምንድነህ ብትለው ወይ ኦሮሞ፣ ወይ ትግሬ ወይ . . . ይልህ እንደሆነ እንጂ በሙሉ አፉ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል እግርህ እስከሚቀጠን ትዞራለህ እንጂ የምታገኝ አይመስለኝም። በዚህ ላይ በአሁኑ ጊዜ በየትም ቦታ ወይም መ/ቤት የሚዘጋጁት ፎርሞች ለዚህ ስሜት የሚጋብዙ ናቸው።

ጥያቄው ዜግነት ቀርቶ ብሔር ሆኗል መለያው! ደግሞ እሱንም እንዳልከው እንደቦታው መቀያየር ይቻላል — አንዴ ጎይቶም፣ አንዴ ቶልቼ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቢያድግልኝ እያሉ እንደሁኔታውና አካባቢው ብቅ ማለት ብቻ ነው። ይህ የዘር መለዋወጥ በሽታ በበረሃ ኑሮ ወዲ ሀዲሽ፣ ወዲ ግርማይ በመባባል የጀመረ ነው ይባላል፣ ደግሞ የሚገርምህ ነገር በየክልሉ የበላይ ተቆጣጣሪ ይኸው ወዲ ትግሬ መሆኑ ነው — በደቡብ ክልል፣ በምስራቁ ክልል ሄዶ ይሄ የተወከለው ሰው (ወዲ በርሔ) የክልሉን ባለስልጣን ሁሉ በዚህ ሂድ፣ በዚህ ውጣ፣ በዚህ ውረድ፣ ይህን ተናገር . . . ካላለው የክልሉ ፕሬዚዳንት እንኳ ቢሆን መረጠኝ ወይም ተመረጥኩበት ባለው ክልል የፈለገውን ነገር መስራት፣ የፈለገውን መናገር፣ ማዘዙ አይችልም። ስብሰባ ሊመራ ቁጭ ብሎ እንኳ አይኑ ከዛ ሰው (ወደ ...) ላይ አይነቀልም በአይኑ የይለፍ ምልክት እስከሚሰጠው ይጠብቃል። ለነገሩ ይሄ ምን ይደንቃል? ዋናው ፕሬዚዳንታችንስ ዶ/ር ነጋሶ ታዛቢ አይደሉ? ግን ይሄ አክሮባት እስከመቼ ነው የሚሰራባችሁ ብትለኝ እኔም መጨረሻና ዳር የለውም ባይ ነኝ።

ወዳጄ! ምንም እንኳ የእናንተ አሜሪካዊያን በ200 አመታት የአጭር ዘመን ዕርምጃ የዓለም ቁንጮ ቢሆንም እኛ ደሪቶ ለብሰን፣ ቁልቋል በልተን፣ በደሳሳ ጨለማ ጎጆ እየኖርን፤ የካሌብ ታላቅነት፣ የአክሱም ስልጣኔን፣ የላሊበላ ድንቅ ሥራችን፣ የጎንደርና ላስታ ቅርሳችን፣ የአድዋ፣ የማይጨው፣ ዶጋሊ ገድላችን በደማችን ተቀብሮ አንገታችንን ቀና ቢያደርገን የሚቃጠል ይቃጠል እንጂ የማይፋቅ እውነታ ነው። የ3000 ዘመን ባለታሪክነታችንም ካፋችን ሳይለይ እንደ ዳዊት ብንደግመው ከመገረም አልፎ ኃላፊነት በጎደላቸው ግለሰቦች አይምሮ የተቀመረ 'ትምክተኛ' የሚል ስም አብረው ለጥፈው የንፁህ ዜጎችን ስም ቅስም የመስበር ዘመቻ መካፈል ባልተገባቸው ነበር። ትምክህት ማለት በራስ ባህል፣ በራስ ቋንቋ፣ በራስ ሀገር፣ በራስ ወገን፣ በራስ ጥበብ መተማመን ማለት ነው — ብለን እንንገራቸው? ያ በአሜሪካ ምድር ከገባሁ ቆይቻለሁ ብሎ አዲሱን መጤ ትዕቢተኛ፣ ትምክህተኛ ነህ የሚለውን 'ከለማበት የተጋባበት' ሆነህ ነው እንጂ አንተም እኛም እንዲህ ነን በልና አጥብቀህ ንገርልኝ።

ሳልነግራችሁ የዘነጋሁት ደግሞ አዲስ አበባችን ወደላቀ ስልጣኔነት መሸጋገሩን ነው ምነው? ምን ተገኘ አትሉኝም? ሁሉ ነገር በወረፋ ሆኖልናል፣ ውሐ በወረፋ መብራት በወረፋ፣ . . . አረፍ ሆነናል አይደል? ይሄ እንግዲህ አዲሱ መንግስታችን ያበረከተልን ገፀ በረከት መሆኑ ነው። ኑሮውም በወረፋ አይደል? አንድ በኢትዮጵያ የሚኖር ጣልያናዊ ጓደኛዬ እኛ ገና ድሮ የሰራንላችሁ ድልድይና መንገድ እስካሁን አለ እንኳንስ ሊታደስ ፈርሶ እንኳ አላለቀም እያለ ሁሌ ይፎክርብኛል። እውነቱን እኮ ነው ፋሺስት ጣልያን በኢትዮጵያ የሰራው መንገድ እስካሁን አለ።

ይሄ ፋሽታዊ መንገድ እውነትም አልፈረሰም፣ ብዙ እድሳትም አያስፈልገውም ከጣሊያን በኋላ የመጣ መንግስት ሁሉ ይሄድበታል፣ የታጠቀ ነፍጠኛ ሁሉ ይረግመድበታል 'ኩሽ! ፈ!' ካለ . . . 'ዘራፍ የመለስ አሽከር' ይልና ጥይቱን ያንበቀብቀዋል ብዙ ዳቦ ልትሆን የምትችለው ጥይት ሰማይ ትስምና ትመለሳለች 'ትልቁ ዳቦ ጥይት ሆነ' የሚባለው ይኼኔ ነው።

ባለፈው ጠቅላይ ሚኒስትሩ መለስ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ ስለ ነፃው ፕሬስና ስለወረቀት መናር ተጠይቀው ሲመልሱ 'እኛ እንኳን ወረቀት ለመደጎም ይቅርና ማዳበሪያ መደጎምም ወገባችንን አጉብጦናል። ይሄ ከአቅማችን በላይ ነው' ካሉ በኋላ የወደፊቱ ነፃ ፕሬስ በአሁኖቹ ነፃ ፕሬስ ነን በሚሉት ወገኖች ከርሰ መቃብር ላይ የሚመሰረት ነው ብለዋልና እኔ ነፃ ነኝ ባልልም ነፃ ነህ ብለው . . . እንገናኛለን እስከዛው ግን መልካሙን ሁሉ እየተመኘሁ የምሰናበታችሁ።

ወርቃየሁ (ከሽገር)

# ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ

## ከይግለጡ ለወርቃየሁ

የአገር ልጅ ወርቃየሁ ለመሆኑ እንደምን ከርመሃል። ለአፍታ ድምፅህ ቢጠፋ፣ ብዕርህ ቢደርቅ ጊዜ በእጅጉ አሳሰበኝ ለመሆኑ ትንፋሽህ አልቆመም ወይስ የዓመት ፈቃድ ላይ ሆነህ ነው እንዲህ በእጅጉ በናፍቆት የሚጠብቅህን እንባቢ ልብ ሰቅለህ የጠፋሽው። እኔማ እንዳለሁ አለሁ መኖር ደጉ፣ እድሜ ጎታታው በሰው አገር ብዙ እያሳየኝ ነው። ምን መኖር ብቻ በእጅጉ አምሮብኛል። የውጭው ገፅታዬ ለተመልካች የቅንጦት ሰው፣ የሞላለት ዜጋ አስመስሎኛል። የውጭው ገፅታዬ ውስጤን ማሳየት ቢችል ደግሞ የዘመድ ናፍቆት፣ የአገር ናፍቆት፣ የቤተሰብና የእድገት መንደሬ ናፍቆት የአይምሮዬ ችሎታ ከሚቀበለው በላይ ሆነውበት አንዳንዴ እንደመደንዘዝም፣ እንደመዘንጋትና፣ ከህልሙ እንደሚባንን ሰው ወሰድ መለስ ያደርገኛል። በዚሁ አጠንክረብኝ የህክምና ባለሙያ፣ የአንጎል መርማሪ ሳላማክር አልቀርም። የዚህ አገር ትልቁ በሽታ ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ ታምቆ ከተቀመጠ በአይን ታይቶ በእጅ ከማይዳሰስ፣ ለህክምናና ለመፍትሄ ከሚያስቸግር ህመም የሚመጣ ነው። ግን ለጊዜው ሳይመሽ ከደረስክበት መፍትሄው ብዙም አይርቅ።

ያገር ልጅ ወርቃየሁ! እምይ አሜሪካ በየዕለቱ እያደገችና እያማረባት ሁሌ ወደፊት እንጂ ወደኋላ ለመሄድ የማታስብ፣ ፍፁም ውስብስብና ሁሉን አቀፍ አመራር ያላት አገር በመሆኗ በውስጧ ያቀፈቻቸውንም ህዝቦች እንደአቅሟ እያስተናገደች ለመጪው ዕድገት ትልቅ መግቢያ በመክፈት ለዓለም ህዝብ የበላይነቷን ለማረጋገጥ በመብቃቷ እኛም በነዋሪነታችን የድርሻችንን እያበረከትን ለእድገቷ መልካሙን ሁሉ ሳንመኝ የምንቀር እንዳይመስልህ። እንኳን የእህል ውሃችን ማብቂያ ቀናችንን ሳናውቅ ቀርቶ የምንኖርበትን የጊዜ ገደብ እንኳን ቢነግሩን ለጊዜው ላለንበት ምድርና ህዝብ ደግ መመኛታችን አይቀርም።

አሜሪካ ከፍጥረቷ ጀምሮ ከተለያዩ አገሮች በመጡ ዜጎች በሚገባ ታንፃ የተገነባች በመሆኑ እኛስ አሜሪካዊ ለመሆን ምን ያግደናል ብለህ።

ቀደም ባሉት አመታት በአሜሪካ የሚኖር የአበሻ ዘር አንድ ትልቅ የወደፊት ተስፋ ነበረው። ከቻልኩ ተምሬና እውቀት ቀስሜ፣ ካልቻልኩ ሌት ተቀን በመስራት በቂ ሀብት ይዤ አገሬ እገባለሁ የሚለው አበሻ ቁጥሩ ቀላል እንዳይመስልህ። አሁን ግን ዘፈኑም ዜማውም ተቀይሯል። ንብረት አፍርቼ፣ ትዳር መስርቼ፣ ልጆች ወልጄ፣ አገር ቤት ያሉትን ዘመዶቼን በምንም መንገድ አምጥቼ በሰላም አሜሪካ ለመኖር አብቃኝ የማይል አበሻ ብዙም አታገኝም። ስሞት ግን በድኔን ለአገሬ አፈር አብቁልኝ የሚል የቁም ኑዛዜ መስማትም ጀምረናል። በቁሙ ወገንና አገሩን ያልጠቀመ ሲሞት ሬሳው በወገን እጀብና በተወለደበት አፈር እንዲያርፍለት መመኘቱ ተገቢ አይደለም ባልልም ብልጥነቱና ዘዴው ያስቀኛል። ደግሞ ሲያቀብጠኝ ብነግራችሁ ሬሳ አይገባም ብላችሁ እንዳታውቁ። ምናለበት ጠንካራ ጉልበታችንን ለባዕድ ገብረን በድናችንን ብንልክላችሁ። የምን ምቀኝነት ነው። ለመሆኑ እናንተስ እንዴት ናችሁ። ኑሮና ብልሃቱን አዛምዶ ይህቺን ጊዜ በዘዴ ለመዝለል የምታደርጉት ጥረት ቀላል አይደለም። ዱሮስ ብልሃት መች ጠፋና። ዘዴው የሚተረጉመው ለተንኮል ሆነ እንጂ። ባለፉት ጥቂት ወራቶች የአገሬ ህዝብ ከፍተኛ ድል እንዳስመዘገበ ሰማሁ። የህዝብ እንደራሴዎችና የአገር መሪዎች ስልጣናቸውን በህዝብ ድጋፍ አስጨብጭበው ተረከቡ ማለትን ሰማንና ጎሽ እንዲህ ነው እንጂ አሰኘን። የአገሬ ሰው እስከመቼ በድህነትና በረሃብ ይኮራመታል። እንግዲህ የራሱን መሪዎች ከራሱ ጉዳይ አውጥቶ ከሾመ በቅርቡ ሁሌ የምንቸገርበት ድህነት ጓዙን ጠቅልሎ ከአገር ሊወጣ ምን ቀረው ብላችሁ። እንግዲህ ለቤት የለሹ መጠለያ፣ ለቦዘኔው ሥራ ከተፈለገለት ችግራችን እንደጉም በኖ መጥፋቱ ሳይሆን ይቀራል።

ያገሬ ሰው ብልህነቱን እንደዘንድሮም አስመስክሮ አያውቅ። ፕሬዚዳንቱ ከጀርመን፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር ከየመን ማስመጣቱ ለወደፊት እዚህ ያለነውንስ ለሚቀጥለው የስልጣን ዘመን ድርሻ ሳይኖረን ይቀር አይመስለኝም። ከሩቅ ሆኖ በወንጭፍ አገር ለማስተዳደር ከመሞከር እድሉ ከተሰጠ ከዚህም የሚዘምት አይጠፋም።

ወገን ወርቃየሁ እንዲያው ለነገሩ አሁንስ በዘር፣ በሃይማኖት መከፋፈላችሁ ትንሽ ጋብ አላለም ወይ? ወይስ ብሶበታል? ባለፈው ሰሞን በአንድ ክፍለ ሃገር የክልሉን ቋንቋ ያልተናገረና በፅሁፍ ያላስመሰከረ ዜግነቱ ያጠራጥራል የሚል መመሪያ ከገዥው ቢሮ መተላለፉን ሰማንና መገረም ሳይሆን የሚያስከትለው ጥፋት በእጅጉ አሳሰበን። በዚህ ከቀጠለ ለሚበታተን አካል በድልነት ሲመዘገብ ለቀረው ህዝብ ደግሞ ወደማይተዋወቅበትና የቅርብ ባዳ ወደሚሆንበት ደረጃ ሳያደርሰው አይቀርም? አንዳንዴ አይኔን ጨፍኜ መጪውን ሳስብ በሚቀጥሉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥ የአንድ አገር ልጆች እንደቱሪስት በአስተርጓሚ ሲነጋገሩ እየታየኝ የትዝብት ሳቅ ይይዘኛል። እኛም ከእናንተ የምናንስ እንዳይመስልህ። እኛም የእናንተ ነፀብራቅ በመሆናችን እናንተ ጋ ያለው እኛም ጋ አይጠፋም። የትኛው መሰለህ? መከፋፈሉ፣ መተቻቸቱና፣ መነታረኩ፣ አለመግባባቱና ቢፈቀድ ጦር መዞ ጎራ ለይቶ ለመዋጋት የማይመለስ ስንት የአበሻ ዘር አለ መሰለህ።

ያኔ ገና ከጅምሩ ታላቁ የሰሜን አብዮት ሲፈነዳ ስንት የአገር ልጅ ቤትና ትዳሩ ፈርሶ፣ በፍቅር የኖረው እየተናቆረ በአይን ለመተያየት ተቃፈፈ መሰለህ። አንድ ሰሞንማ እንደ ፋሽን ተቆጥሮ አንዱ አንዱን ማቃለል፣ መዝለፍና ከተቻለም ማጥፋት እንደጀግንነት ተቆጥሮ ነበር። የቻለ ሁሉንም እንደአመጣጡ አስተናግዶ የወቅቱን የወረርሺኝ በሽታ በጥበብ አሳልፎት እዚህ ደረጃ ደርሷል። ልቡ ያበጠበትና ለሁሉ ነገር ችኩል የሆነው ደግሞ እንኳን ከሚቀርቡት ወዳጆቹ ቀርቶ ትዳሩንና ፍቅሩን አፍርሶ ፀፀት አትርፎ አል<u>ፏል</u>።

ይኼውልህ ወርቃየሁ አንድ ሰሞን እንዲህ አርጎን ነበር እልሃለሁ። ለነገሩማ አሁን ጋብ ብሎ መልኩን በመቀየር የተራቀቀ ስልት ይዞ እንጂ የዘርና የጎሳ በሽታ አሜሪካ በሚኖረው አበሻ ላይ አሁንም የዘር ፈረሱን ጭኖ እየጋለበው ነው። በዚህ ላይ የፖለቲካ ድርጅቱ ብዛት ሁሉንም በየፊናው ከፋፍሎታል። ይኼ ደግሞ የሚያስቀው የእኛ ገፅታ ነው። ሁሉም የፖለቲካ ድርጅት የወቅቱ መንግሥት ተቃዋሚ ከሆነ ለምን በአንድ ጎራ እንደማይሰለፍ ይገርመኛል። ተመሳሳይ አቋም ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች በጥቃቅን ሃሳብ ተለያይተው በየስብሰባው አንዱ አንዱን ሲነቅፍ፣ ሲያጥላላና የሌላውን ድርጅት መሪዎች ሲያንቋሽሽ ሌላው ደግሞ በተራው አፀፋውን ሲመልስ ታያለህ። ታዲያ እንዲህ አይነቷ ፖለቲካ የኢትዮጵያውያንን ጥንካሬ ሲያሳሳ ኋለው መንግሥት ደግሞ ጥንካሬን ያስገኝለት ይመስለኛል። በዚህ ላይ የሌሎች አገሮችም መንግሥታት መሳቂያ ሳንሆን የቀረን እንዳይመስልህ።

በል እንግዲህ ብዙ የምለው ነበረኝ። ማለቂያ ስለሌለው ሳልጨርሰው አልነካካውም።

በተረፈ ብዕርህን ይዘህ ብቅ ስትል ለአፀፋው ወደኋላ አልልም። እኔም በወንጭፍ ውርወራ ከዘዴኞቹ ተምሬአለሁ። ወርቃየሁ እባክህ አትጥፋ ሃሳቤን ለመግለፅ የአንተ ብዕር መንደርደሪያና መኮርኮሪያ ስለሆነ ብዕርህን አታድርቀው። በል በወንጭፍ እንጠፋፋ።

እስከዚያ በቸር ያቆየን።

ይግለጡ ነኝ ከነፋሻዋ ከተማ

## ልጆቻችንን
## የት እንደብቃቸው?

ከብርሃኑ (አዲስአባ)

አላፊውና ጠፊው ሰው ትንሽ ትንሽ ህያውነት ይሰማዋል ከተባለ በሌላ በምንም መንገድ ሳይሆን ተከቷቸው በሚሄደው ልጆቹ ብቻ ይሆናል። እያንዳንዱ ወላጅ መጭውን ዓለም የሚያይና ከቀጣዩ ጋር የሚገናኝ በልጆቹ አማካኝነት ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው አይሆኑትን ከሚሆኑበት ምክንያቶች ውስጥ አንዱም ይህ ነው። እኛ ያላገኘነውንና ያልደረሰበትን መልካም ዕድል ሁሉ ልጆቻችን እንዲጨብጡትና እንዲደርሱበት እንመኛለን። በቻልነው ሁሉ ጥሩ ጥሩውን ለልጆቻችን እንመርጣለን። የዚያኑም ያህል ከማይጠቅማቸውና ከሚጎዳቸው ነገር ሁሉ ለመከለልና ለመጠበቅ እንጥራለን።

ልጆችን – በአጠቃላይም ወጣቱን ትውልድ አንፆና አስተካክሎ በማሳደግ ረገድ ወላጅ፣ ትምህርት ቤትና ኅብረተሰብ የጋራ ኃላፊነት አለብን። ልጆች በትምህርት ቤታቸውና በጠባቧ ክፍላቸው ብቻ ሳይሆን የትም የት ይማራሉ። ከወላጅ – ከጎረቤት፣ ከቤተክርስታያን–ከመስጊድ፣ ከገበያ–ከአደባባይ፣ ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥን፣ ወዘተ ትምህርት ይገበያሉ። የትም የት ከመማር አያመልጡም። የትምህርት ባለሙያዎች ወላጆች በልጆቻቸው ፊት ስለሚናገሩትም ሆነ ስለሚሰሩት ነገር ሁሉ መጠንቀቅ እንዳለባቸው ይመክራሉ።

(ወደ ገጽ 11 ይዞራል)

# እንዲህ ሆነ

## ነፃው ፕሬስ በአደጋ ላይ ነው እስራቱ ቀጥሏል

የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጣ ማህበር ፕሬዚዳንት የሆኑት አቶ ከፋለ ማሞ ሰሞኑን ከጀርመን ጋዜጠኛ ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ በአገራችን እንደ አሸን ፈልተው የነበሩት ወርሐዊ መፅሔቶችና ሳምንታዊ ጋዜጦች የዲሞክራሲውን መጎልበት የስልጣናቸውና ጥቅማቸው ማክተሚያ አድርገው የሚመለከቱ ኃይሎች በሚያደርሱት ተፅዕኖ እየተዳከሙ መጥተው ዛሬ በሞት አፋፍ እንደሆነና የነፃ ፕሬስ አሰራር ባህል ለአገራችን አዲስ በመሆኑ፣ መሰረታዊ ትምህርት፣ ስልጠናና ልምድ ያለው ጋዜጠኛ ባለመኖሩ የነፃ ፕሬስ ጠላቶች የሆኑት ወኪሎቻቸውን ወደ ነፃው ፕሬስ መንደር በማስገባትና ነፃውን ፕሬስ የሚያረክሱ ዝግጅቶችን በነፃ ፕሬስ ስም እንዲያወጡ በማድረጋቸውና ነፃውን ፕሬስ ለመግደል ባላቸው ፍላጎት ከፖሊስ ማሳደድ ጀምሮ የነፃ ፕሬስ ውጤቶች ከአዲስ አበባ ውጪ እንዳይሰራጩ ልዩ ልዩ ተፅዕኖዎችን በማድረግ ላይ መሆናቸውንና ነፃ ፕሬስን የሚያነቡ የመንግስት ሰራተኞችን በአይነ ቁራኛ ማየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነፃውን ፕሬስ ለማዳከም የተያዘው ዘመቻ ተደራራቢ ክሶችን በምርመራ ክፍሎች፣ በአቃቢ ህግና በፍ/ቤት በመመስረት በዋስትናና በቅጣት የነፃ ፕሬሶችን የፋይናንስ አቅም ለማዳከም የገንዘብ ቅጣት መቆለል፣ ይህን ያልቻሉትን ጋዜጠኞች ማሰር ሲሆን በዚሁ ሳቢያ በአሁኑ ጊዜ በዚህ አመት ብቻ ወደ 16 የሚሆኑ ጋዜጠኞች በእስር ላይ እንደሚገኙና በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት ልዩ ልዩ ተፅዕኖዎች ናቸው ነፃውን ፕሬስ አደጋ ላይ የጣሉት ካሉ በኋላ ያለ ነፃ ፕሬስ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የማይታሰብ መሆኑንና አምባገነኖች ያለ ታዛቢ በሕዝብ ትከሻ ላይ መፈንጨታቸው የማይቀር መሆኑን በማሳሰብ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ወይ በውዴታ ህዝባዊ መንገድ መተከል ይኖርበታል አለበለዚያ ደግሞ ... ግፊትና የዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ትግል ሌላ የዲሞክራሲን ስርአት የሚያራምድ መንግስት መፍጠር ይኖርበታል ማለት ነው ሲሉ አቶ ከፋለ ማሞ የኢ.ነ.ጋ.ማ. ፕሬዚዳንት ገልፀዋል።

## የቦምብ ፍንዳታ

በድሬደዋ እንድ ሆቴል ቦምብ ፈንድቶ ሰዎች መሞታቸውን ሬውተር ገልጿል። አዲስ አበባ ጊዮን ሆቴል ሶስት ሰዎችን የገደለው የቦምብ ፍንዳታ ከተካሄደ ከጥቂት ቀናት በኋላ በድሬደዋ የፈነዳውን ቦምብ ማን እንዳፈነዳው አልታወቀም።

## ፕሮፌሰር አስራት በእስር ቤት ሰበራ ወንጀል ለ4ኛ ጊዜ ሊቀርቡ ነው።

እውቁ የቀዶ ጥገና ሐኪምና የመአህድ ፕሬዚዳንት የሆኑት ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ባለፈው ጊዜ መንግስትን ሊገለብጡ አሲረዋል ተብለው 3 ክስ ቀርቦባቸው በአሁኑ ሰዓት የ2 አመት የእስራት ፍርዳቸውን በመግፋት ላይ ሲሆኑ አሁን ደግሞ እንደገና በእስር ቤት ውስጥ 30 ሰዎችን አስተባብረው እስር ቤት ሰብረው ለመውጣት አደራጅተዋል የሚል ክስ ተመስርቶባቸው ለ4ኛ ጊዜ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ነው።

## የኤርትራና የየመን ስኩቻ

በሐኒሽ ደሴቶች የይገባኛል ጥያቄ ምክንያት ጦር የተማዘዙትን የመንና ኤርትራን ለመሸምገል በተለይም የኢትዮጵያ መንግስት የበኩሉን ጥረት እያደረገ ባለበት ሰዓት የሁለቱ አገር መንግስታት እርስ በእርስ መወነጃጀላቸው እንዳልቀረና ምላሽ ያላገኙ ጥያቄዎችም ለአደራዳሪዎች ችግር ሳይፈጥሩባቸው እንደማይቀሩ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ያስረዳሉ። ምንም እንኳ በሁለት የአሜሪካ መንግስት ዲፕሎማቶች በተገኙበት በሁለቱ አገሮች የተኩስ አቁም ስምምነት ቢፈፀሙም ውሉ በተፈፀመ በትንሽ ጊዜ ውስጥ የኤርትራ መንግስት ውሉን ጥሶ ጦርነት እንደፈፀመባትና ከሐኒሽ ደሴቶች አንደኛውን እንደተቆጣጠረች ተገልጿል። እንደ አንዳንድ የዜና አውታሮች ምስክርነት ከሆነ ትልቁና ትንሹ በመባል የሚለዩት የሐኒሽ ደሴቶች ከረዥም ጊዜያት ጀምሮ ለወደቧ ቅርብ ለሆነችው በየመን እጅ እንደነበሩና የየመን መንግስትም ደሴቶቹን ለቱሪዝም አገልግሎትና ለአሳ ምርት ሲል የማሳደግ ዕቅድ እንደነበረው ሲጠቅሱ በተቃራኒው ደግሞ የኤርትራው ውጪ ጉዳይ ሚ/ር መ/ቤት ይፋ እንዳደረገው ከሆነ የየመን ጦር ያለእንዳች ማብራሪያና ማስጠንቀቂያ በድንገት መጥቶ ሊሰፍርባት ሞከረ እንጂ ከኦቶማን ኢምፓየር ጀምሮ የኤርትራ አካል ሆና የኖረች ታሪካዊ ምድሩ መሆኑን

ይገልፃል። የሆኖ ሆኖ በአሁኑ ሰዓት ሁለቱም አገሮች በኢትዮጵያ መንግስት እንዲሁም በተለያዩ የአካባቢው አገሮች አማካኝነት እንዲታረቁ የተደረጉት ሙከራዎች እስካሁን ድረስ ሙሉ በሙሉ ውጤት ያላስገኙ መሆናቸው ተገልጿል። ስለዚችው ደሴት ጉዳይ የየመን ፓርላማ በቅርቡ ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ ትልቋ ሀኒሽ ደሴት በኤርትራ ኃይሎች እንዲያዝ ጠንቅ የሆኑትን ግለሰቦች ህግ ፊት እንዲቀርቡና እርምጃ እንዲወሰድ ማሳሰቢያ የሰጠ ሲሆን የየመኑ መሪ የመከላከያ ሚኒስትራቸውን ከሥራ ማሰናበታቸው ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። በተያያዘ ዜና ኤርትራ አሁን በቁጥጥሯ ስር ባደረገችው ደሴት ላይ የጦር መሣሪያዎችንና ታንኮችን በመርከብ በማጓዝ ላይ መሆኗ ተገልጿል።

## ሻለቃ አድማሴ ሞቱ

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የነበሩት ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባደረባቸው የጤና መታወክ በዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል ሲረዱ ቢቆዩም በአንድ ቀን ውስጥ ሶስት ጊዜ በተደረገላቸው ቀዶ ህክምና በባለሙያዎች ችሎታ እምነት በማጣታቸው በራሳቸው ፈቃድ ወደ ደጃዝማች ባልቻ ሆስፒታል ተዛውረው በህክምና ሲረዱ ከቆዩ በኋላ ታህሳስ 27 ቀን 1988 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። በ1916 ዓ.ም በጎባ ከተማ ፋሲል ጊዮርጊስ በተባለው ስፍራ የተወለዱትና የ72 ዓመት አዛውንት የሆኑት ሻለቃ አድማሴ የ7 ወንዶችና የ1 ሴት ልጅ አባት ነበሩ። በአሜሪካ በከፍተኛ የመገናኛ ትምህርት፣ በህንድ በሬዲዮ ኢንጅነሪንግ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን ከ1957-66 ድረስ የሐረር ከተማ ህዝብን በመወከል የፓርላማ ተመራጭ የነበሩና በቅርቡም በረቂቅ ሕገ መንግስቱ ላይ ጥሩ ተሳትፎ የሚያሳዩና በርካታ እውነታዎችን ያንፀባረቁ ታላቅ ሰው ነበሩ።

ሻለቃ አድማሴ ባደረባቸው ሕመም ከዚህ ዓለም ተለዩ የሚል ዜና ዕረፍታቸውን የተናገሩት የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ሻለቃው በህይወት ዘመናቸው የፈፀሙትን ታላላቅ ተግባራት በቁማቸው ሳሉ ሲያድበሰብሱ ቆይተው በመጨረሻው ሰአት በመናገራቸውና 'ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ ነበር' በማለታቸው የመንግስት የዜና አውታሮች በአንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች ትችት ውስጥ ገብተዋል።

## ለአትላንታው ዝግጅት ኮሚቴ ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ባለፈው ጊዜ ባካሄደው ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ የአትላንታ ኦሎምፒክን አስመልክቶ ገንቢ አስተያየቶች የአረቡ ሲሆን በሌላ በኩልም ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ ከተሳትፎ ባሻገር ለውጤት የሚያበቃ ዝግጅት የሚደረግበትን ሁኔታ የሚያመቻች ዘጠኝ አባላት ያሉት የአትላንታ ኦሎምፒክ ዝግጅት ኮሚቴ ተዋቅሯል። የዚሁ ኮሚቴ አባላት ከተሳታፊ ፌዴሬሽኖች፣ ከኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴና ከስፖርት ኮሚሽን የተወከሉ መሆናቸው ታውቋል።

## የአፄ ምኒሊክ ሐውልት ተጀቦነ

ይህን የዳግማዊ ምኒሊክ ሐውልት ያሰሩት ልጃቸውና የዙፋናቸው ወራሽ የነበሩት ንግስት ዘውዲቱ ሲሆኑ፤ ጀርመን አገር የተሰራው ይህ ሐውልት ከንፁህ ነሐስ የተቀረፀው በጀርመናዊው ሐርተል ሲሆን የምረቃውም በዓል ንግስት ዘውዲቱ ከሞቱ በኋላ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ የንግስ በዓል ማለትም በጥቅምት 22/1923 ዓ.ም መሆኑን ታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ። ከዛ በኋላ ግን የጣሊያን መሪ በነበረው ሞሶሎኒ ትዕዛዝ ሐምሌ 4/1928 ከምሽቱ 4 ሰዓት በድብቅ እንዲፈርስ ተደርጎ 20 ሜትር ጥልቀት ባለው ጉድጓድ ውስጥ ተቀብሮም ነበር። በ1934 ኢትዮጵያ ነፃነቷን ካገኘች በኋላ የአፍሪካ ጥቁሮች ሁሉ ንግስና መኩሪያቸው የሆነው ይህ ሐውልት በክብር መቆሙ የሚታወስ ነው። ከዚያን ጊዜ በኋላ ሐውልቱ እንዲፈርስ የተጠየቀው ኢህአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ከየትኛው ክልል እንደመጡ ባልታወቁ የኦሮሞ ብሔር አባሎች በፈረስና በእግረኛ ታጅበው ስፍራውን ከበቡት። ከዚያም ሐውልቱን ጥቁር ጨርቅ አልብሰውት ሄዱ (ማታውኑ የጎዳና ተዳዳሪዎች አውርደው አንሶላ አድርገውት ነበር)። እነሆ አሁን የአድዋ በዓል መቶኛ አመት ሊከበር ትንሽ ጊዜ ሲቀረው የምኒሊክ ሐውልት በአጣና የተከበበ ሲሆን አንዳንድ አርቲስቶች እንደሚሉት ከሆነ ይህን የኢትዮጵያ የህዝብ ቅርስ ከማበላሸታቸው በፊት ባለሙያተኞችን ሊያማክሩ ይገባል። ነሐስን ያህል እጅግ ውድ ንጥረ ነገር ቀለም መቀባት በአለም አርቲስቶች ዘንድ ታላቅ ቀልድ የሚፈጥርና ለማመን የሚያዳግት ቢሆንም ዘውድ ጭነው፣ ጎፈና ለብሰው፣ ጣምራ ጦር ይዘው ፈረስ ላይ የተቀመጡት ምኒሊክ ከዚህ በፊት በአላዋቂ ወርቅማ ቀለም ተለቅልቀዋል። ይህ የአፄ ምኒሊክ ሐውልት ለምንና በማን ትዕዛዝ እንደሚታጠር ገና ተለይቶ ባይታወቅም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ስጋት እንደገና እንዳይቆሸሽ ነው።

# ጥንቅር ከዚህም ከዚያም

## (በሀገር ውስጥ ከታተሙ የግል ጋዜጦች የተጠናቀረ)

* ፖሊስ ይህን ሁሉ የዘራፊ መንጋ ከየት አመጣው? እንዴትስ እንደዚህ ከተማችን ውስጥ ሊበዙ ቻሉ?

አለሙ - ከመርካቶ

● በአገራችን ያለው ዝርክርና ስድ አስተዳደር ስድና ዘራፊን ዜጋ ፈጥሮ ይሆናላ?

*   *   *

* ሰሞኑን እንዴት ነው የከተማው ማዘጋጃ ቤት መንገድ መጠጋገን ጀምሯል?

ኃይሉ - ከመገናኛ

● ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች እንዲሉ ነው።

*   *   *

* መብራት ሐይል ግድብ ውስጥ በቂ ውሐ ባለመኖሩ የኃይል ችግር አለብን ይለናል፣ ሜትሮሎጂ ደግሞ የዘንድሮ ዝናብ ያለወቅቱ መጥቷል እያለ በየቀኑ ይነግረናል ነገሩ ምንድነው?

እያልነሽ - ከ4 ኪሎ

● ፖለቲካ ሌላ ሜትሮሎጂ ሌላ ሆኖ ነው።

*   *   *

* የቴዎድሮስ ፈረስ ስም ማን እንደሚባል ያውቃሉ?

● አባ ታጠቅ ነዋ!

* የጠቅላይ ሚኒስትሩ መለስ ፈረስስ?

● ነጋሶ እንድሎት ይፈልጋሉ?

*   *   *

*ኸረ እነዚህ በየመ/ቤቱ ያሉት ሰዎች ያለፈልዳቸው እየገቡ ነገሩን ሁሉ እያበለሻሹት ነው።

አቡሽ - ከቀበና

● በደቡብ ባዮሎጂስቱ ለአቃቢ ህግነት መሾማቸውን አልሰማሁም እንዳይሉኝ።

*   *   *

* ኸረ የውሐ እጥረት ገደለን በ3 ቀን አንዴ እንኳ አናገኝም እሱም ወደ . . . ተሜነ እንዴ?

ምህረቱ - ከኮልፌ

● ከዚያች መናጢ ግንቦት ወዲህ ምን ያልሆነው አለ? ወደፊት አየሩም በኮታ እንዳይሆን ነው ስጋታችን።

*   *   *

* ውሻው 500km ተጉዞ ጌቶቹን አገኘ የሚል ዜና አንብቤ ገረመኝ።

ማማሻ - ከቤልየር

●ውቅያኖስአቋርጠው መጥተው ለጌቶቻቸው ጭራቸውን የሚቆሉ ሰዎች ባሉበት ዘመን ታማኟ ውሻ ሳትሻል ትቀራለች።

* የሻለቃ አድማሴ ሞት ማንን ያስፈነደቀ ይመስልሃል?

ከቤ - ከካዛንችስ

● በካምቦሎጆ ህዝብ ተወረፉ ከተባሉት አቶ ታምራትና ዶ/ር አብዱል መጅድ ልታጣላኝ ፈልገህ ነው?

*   *   *

* አንተዬ አዳዲስ የአየር ወለድ ልብስ አይነት የተሸላለሙ መኪኖች ከተማውን አቋርጠው ሲነጉዱ አየሁ።

ታደሰ - ከፒያሳ

● ያቺ የመን ፈረደባት በለኛ!

*   *   *

* ሲኒማ ኢትዮጵያ በራፍ ላይ አንድ የመንግስት ፓጃሮ ደረጃዎችን ተሻግሮ ከግንብ ጋር መላተሙ ገረመኝ።·

ኤልያስ - ከፒያሳ

● የእነ ቻክኖሪስና ራምቦን ፖስተር እያየ ሲመረቅን ምን ያድርግ ብለህ ነው።

*   *   * ˋ

* የመብራት ኃይል መ/ቤት የመብራት ራሽን እደላ ምን ይባላል?

ጌታቸው - ከጌጃ ሰፈር

● የኢኮኖሚው እመርታና የኢህአዴግ ገፀ በረከት ይሆናላ!

*   *   *

* እነዚህ በየቦታው የተተከሉት የመንግስት ስልኮች ደመና ሲሆን ለምን አይሰሩም?

ብስኩት - ከኡራኤል

● አስም ይዟቸው ይሆናላ!

*   *   *

* ትግራይን ለማልማት የውጪ ዜጎች ሁሉ መረባረባቸው ምን የሚሉት ነው?

አበራ - ከአብነት

● የመሪዎቻችን የዘር ግንድ የመጣው ከዚያው መሆኑን ተገንዝበው ነዋ!

*   *   *

* ኢትዮጵያ እስከ መቼ በእርጥባን ትኖራለች ምናለ ብንሰራና ራሳችንን ብንችል?

ክንፈ- ከቄራ

● በዕርዳታ ስም የተንበሸበሹትን ባለስልጣኖች መጠየቁ አይቀልም?

*   *   *

* እናንተ ህዝብ ተራበ፣ ተቸገረ ትላላችሁ ይሄው አምሮበት ባውንዱን እየመነዘረ በየቡናቤቱ ባንኮኒ ውስኪውን ሲረጭ ይታይ የለ?

ታምራት - ከቦሌ

● ይህን ሲያደርጉ ያዩት የክልል አንድ ሰዎችን እንዳይሆን?

----------

* ኢ.አ.ድ. በኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ ሰፍኗል የሚሉትን ሰምቶ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ሄዶ አይደል? እስጢፎ - ከእስጢፋኖስ

● የጥበቃው ጋጋታ ለምን እንደሆነ ሳይገባቸው ቀረ ብለው ነው?

----------

* ፃድቃን ገ/ትንሳኤ ኤታማዦር ሹም የሆኑት በውትድርና ችሎታ ከሰዩ በልጠው ነው?

እሸቴ- ከወሎ ሰፈር

● መለኪያ ችሎታ መሆኑ ቀርቶ የአድዋ ልጅነት መሆኑን አላቅም እንዳይሉኝ?

----------

* ብዙ ሰዎች ይታሰራሉ ነገሩ ምንድነው?

ዮሐንስ - ከላምበረት

● የ5 አመቱ መርሃ ግብር በይፋ ተጀመረ በሉኛ!

----------

* ጠ/ሚ/ር መለስ በነፃ ፕሬስ ላይ የማያዳግም ዕርምጃ ለመውሰድ ማቀዳቸው ምን ይባላል?

አዲስ - ከ22 ማዞሪያ

● የአልባኒያ አብዮተኝነት የወለደው አምባገነንነት ለማለት ነው!

----------

* የዩንቨርስቲው ተማሪ ጨኸት አገር መሆኑ ቀርቶ ሆድ ይሁንና ይረፈው?

ተፈራ - ከ4 ኪሎ

● ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ አለ።

----------

* ከኦነግና ከህወሃት የቱ ይሻላል ትላላችሁ?

መስፍን - ከአምቦ

● ከዝንጀሮ ቆንጆ . . . እንድንልዎት ነው?

----------

* ጋዜጣችሁን የቤተመንግስት ሰዎች ያነቡት ይሆን? ሰላም - ከካዛንቺስ

● ማታ ማታ።

----------

* ም/ቤቱ የአቶ መለስ ሆነ እንዴ? መወያየት ሲገባቸው አባላቱ ይጠይቃሉ እሳቸው መልስ ይሰጣሉ

ፀጋዬ - ከላምበረት

● ጋዜጣዊ መግለጫ ሆኗላ!

----------

* እናንተዩ ሹመት በመላጣነት በበራነት ሆነ እንዴ?

● ምን ለማለት ፈልገው ነው?

* ነጋሶን አይቶ - መለስን - መስፍን አይቶ ካሱ ኢላላ . . .

● እንዴት አድረገው አዩት።

# ልጆቻችንን . . .

(ከገጽ 7 የዞረ)

ልጆች ከቤተሰባቸው የሚማሩት ብዙ ነው። ቋንቋውን፣ ባሕሉን፣ ልምዱን ስለሚማሩ እያንዳንዱ ቤተሰብ ለልጁ ተስማሚና ጠቃሚ ትምህርት ቤት ሆኖ መገኘት አለበት። ፊልሞች፣ መጽሐፎች፣ ትያትሮችና ልዩ ልዩ ትርዒቶች ለአዋቂ ለሕፃናት እየተባሉ የሚመድቡት ያለምክንያት አይደለም። ሕፃናትና ልጆች፣ ያለዕድሜያቸው ሊሰሙት፣ ሊያዩትና ሊያውቁት የማይገባቸውን ነገር እንዳይሰሙ፣ እንዳያዩና እንዳያውቁ ለመጠበቅ ነው። በባሕላችንም ሽማግሌና ባልቴት በደረሱበትና ባጋጠማቸው ቦታ ሁሉ የማይገባ ችራ ሲሰራ የሚያዩትን ልጅ እንዲሁ አልፈውት አይሄዱም። ይገስፃሉ፣ ያርማሉ፣ ያስተምራሉ።

ይህ ኃላፊነት የፖለቲካ መሪ፣ የሃይማኖት አባት፣ ነጋዴ፣ ገበሬ ሳንባባል ሁላችንም እኩል ሊሰማንና ሊከብደን ይገባል። መምህራን ሲያስተምሩ፣ የሃይማኖት አባቶች ሲሰብኩ፣ ወላጆች ሲመክሩ ውለው ልጆቻችን አመሻሽ ላይ ከቴሌቪዥን በሚወረወር ጭቃ ሊበከሉ አይገባም። ሕፃናት ትላልቆቻቸውንና ትላልቆች የሚባሉትን መሆንና መምሰል ይመኛሉ።

በተለይም ከሚብለጨለጨው ቴሌቪዥን የሚያዩትን የሚሰሙትን ሁሉ ለመሆንና ለመናገር ወደኋላ አይሉም። ዕብሪትና ትሕትና፣ ብልግና ጨዋነት በውል ለይተው የማያውቁት ሕፃናትና ልጆች ዛሬ ዛሬ ከጎዳና ተዳዳሪዎች አፍ ከሚሰሙት ፀያፍና የሚሰቀጥጥ ቋንቋ ያላነሰ ከመንግሥት ዜና ማሰራጫ እያዳመጡና እየተመለከቱ ናቸው።

ቴሌቪዥን የመመልከት፣ ሬዲዮ የማዳመጥና ጋዜጣ የማገላበጥ ዕድል ያለው የከተማ ልጅ፣ አማሩም ከፉም፣ ብዙዎቹን የአገሪቱን ባለችልጣኖች በችልጣን ደረጃቸው በቁመናቸውና በድምፃቸው ለይቶ ያውቃቸዋል። ታዲያ "እንዲህ አይባልም፣ እንዲሁ ተብሎ አይመገርም" እያልን ያሳደግነው ልጅ ከፍተኛ ከተባሉት ባለሥልጣኖች አንደበት ፈጽሞ ሊነገርም ሆነ ሊደመጥ የማይገባው ሸካራ ቋንቋ ሲሰማና "እንዲህ ይባላል?" የሚል ጥያቄ ሲደቅን ወላጆች ምን እንመልስ? "ትክክል አይደለም" ስንል በኖርንበት አፋችን አደጋ ስለገጠመን ብቻ "ትክክል ነው" እንበል? ወይስ "ባለሥልጣን ባለጌ ነው" ብለን ለሚያልፍ ነገርና ጊዜ በልጆቻችን አእምሮ ውስጥ ቋሚ ስህተት እንቅረፅ? ሁሉንም ሕሊናችን አይቀበለውም። ታዲያ ምን አሻለን? "ጨምላቃ-አጨማለቁት፣ የበከተ-የበሰበሰ" እየተባለ ከሚነገርበት ዜና ማሰራጫ ልጆቻችንን እንዴት እንጠብቃቸው? የትስ ይዘናቸው እንደበቅ?

# Allstate
You're in good hands.

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404) 299-7287 ☐ FAX: (404) 299-6266

AUTO
HOME OWNER'S
RENTER'S
LIFE
BUSINESS
COMMERCIAL AUTO



THEODROS
HAILEGIORGIS
*Exclusive Agent*


Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indemnity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

You're in good hands.

## *RAPID TAX SERVICE*

Professional
Tax Preparation
Individuals & business
Electronic Tax Filing

ፈጣን
የታክስ አገልግሎት
ላእከ ማለደ



**OFFICE HOURS**
Monday - Friday 9:00 am to 6:00 pm
Saturday 10:00 am to 4:00 pm
CALL (RTS) LEAKE MALEDE
PHONE: (404)296-3088 FAX: (404)297-7765
E-Mail:rapid tax@aol.com

# ግዕዝ በኢንተርኔት

በዶ/ ር በቀለ ሞላ

ኮምፕዩተርን በግዕዝ ለመጠቀም ከዛሬ ፲፱ ዓመት በፊት የጀመርነው የቴክኖሎጂ ትግል ብዙ ችግር ቢፈጥርብንም ዓላማችን እየተሳካልን ነው። በቅርቡም የኮምፕዩተር ዓለም ወደ ኢንተርኔት (Internet) በመተሳለፉ ከ256 ላነሱት የላቲን ፊደላት የተሠራው ኮምፕዩተር ለ480 የግዕዝ ፊደሎቻችን አለመብቃት አስቸግሮ ነበር። እንዲህም ሆኖ ዶ/ር አበራ ሞላ እንደልማዳቸው አዲስ ብሬክስሩ (Breakthrough) ቴክኖሎጂ በመፍጠር በትክክለኞዎቹና በተሟሉት 480 የግዕዝ ፊደሎቻችን ለመጀመሪያ ጊዜ ኢንተርኔት ላይ እንዲጻፍ አድርገዋል። ይህ አዲስ ዘዴ ከማንኛውም ዓይነት የግዕዝና የዓለም ፊደላትና ሌሎች አጠቃቀሞች ጋር ይሠራል።

የግዕዝ ፊደል ኢንተርኔት ውስጥ መግባትና የተጠቃሚው የመጻፍ መቻልና በዓለም ከሚገኙ የተለያዩ ኮምፕዩተር ላይ የማንበብ ችሎታ ለኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ እድገት ትልቅ ምጥቀት ነው። የኢንተርኔት አግልግሎት ወጪ ትንሽ በመሆኑ የስልክ የደብዳቤና የወረቀት ወጭዎችን ያስቀንሳል። ይህንኑ ቴክኖሎጂ የኢትዮጵያ ኮምፕዩተሮችና ሶፍትዌር ኩባንያ ከኢትዮወርድ (EthioWord) ፕሮግራሙ ጋር በማጣመር ኢትዮሳይበር (EthioCyber) በሚል ስም መሸጥ ጀምሯል። ◆


በተሟሉ ትክክለኛ የግዕዝ ፊደላት ለመጠቀም

## ኢትዮወርድ *EthioWord*

በተሟሉና በማይቀጠሉ የግዕዝ ፊደሎቻችን በኢትዮኤዲት የተጻፉ ጽሑፎችን በኢንተርኔት (Internet) በftp ጭምር በመላክ በዓለም አቀፉ Web-Internet ፊደሎቻችንን በመጠቀም በኮምፒዩተር መላላክ የሚሰጠውን ደስታ ሳይገንዝቡት አይቀሩም።

ግዕዝ በኢንተርኔት
Ethiopic on the Internet




የላንዳፍታ መጽሔት በአጠቃላይ የሚዘጋጀው በሞዴትና በኢትዮወርድ ነው።

**የኢትዮጵያ ኮምፒውተሮችና ሶፍትዌር**

**Ethiopian Computers and Software**

9781 W. Fremont Pl. Littleton CO 80123, USA

Tel. (303)972-2186 - (202)785-1618 - Fax: (303)973-4342

E-Mail ethiopian@aol.com

ልብወለድ

# ድንቄም ተሞሸረች!!

(በዛብህ ገ/የስ)

የሰፈሩ ሕፃናት ንቅል ብለው በሶምሶማ ሩጫ ይከታተሉናል። ውሾቹም ከመኪናዎቻችን ጎን ለጎን እየሮጡ ይጮሃሉ። ሚዜዬ ከመኪናው ወርዶ የኮቱን ግራና ቀኝ በእጁ ወደታች ይዞ ሮጥ ሮጥ እያለ የአጃቢ መኪናዎች ረድፋቸውን እንዲያስተካክሉ ለመንገር ይጣደፋል። ሚዜ-ዕዳ ቻይ።

ሆታው ቀለጠ። አናስገባም ሠርገኛ ... ባያስገቡ ጉዳቸው የሚፈሳው የእነሱው . . . ምላስ ብል ምን ይውጣቸዋል? . . . ሃይ ሎጋ፣ ሃይ ሎጋ፣ ሃይ ሎጋዬ ሆ! የእኔ ሚዜዎች ደግሞ ጉረኞች . . . እሱን ተዉት እምቢ ቢሏችሁ ምን ልታደርጉ ይሆን? . . . ሚዜው ድሃ ነው ሽቶው ውሃ ነው። እንዴት ነቁ። በሩ ሰው ታጠረ። ወቸው ጉድ! ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ አሉ የአገሬ ሰዎች። ሚዜዎቼ ለጩኸቱ አልደከሙም። እኔ ግን ሰለቸኝ። ማሰቡም ደከመኝ። አፍሬ ነው እንጂ አቦ በሩን ልቀቁት ልል ከጅሎኝ ነበር።

እንዲያ እንዲያ ሆነና መግባት አይቀርም ወደ ሙሽራዬ ወደ የወደፊቷ ባለቤቴ እንድገባ ተፈቀደልኝ። አላበኝ። ሚዜዬ በዓይኑ ይጠቅሰኛል። አበባዬን በግራ በኩል እንድይዝ መንገሩ ነው። እልልልልል . . . ዘፈኑ ቀለጠ። የእኔም ልብ አብሮ ቀለጠ። እጄን አላበኝ። አንዘፈዘፈኝ። ከሙሽራዬ ጋር ተያይዘን በዳስ ውስጥ ወደ ተዘጋጀልን ስፍራ ስናመራ ሳላስበው በቁንጥጫ ድብን አደረገችኝ። ምን ልታወራልኝ ፈልጋ ይሆን ብዬ ከአንገቴ ጋደል ብዬ ጆሮዬን ስሰጣት ጆሮዬን ንክስ አደረገችው። ወቸው ጉድ። ደነገጥኩ። ላቤ በጀርባዬ ፈሠሠ። ከመቅፅበት ቀና አልኩና ግራ ቀኜን ቃኘሁ - ባፈሩት ዓይኖቼ። ከዕድምተኛው ሕዝብ ራቅ ብሎ አንድ ህፃን የሙሽራዬን ንክሻ አይቶ ኖሮ በእጁ እንቅስቃሴ ለጓደኛው ይነግራል። ሌሎችም አይተውን ይሆን? አልኩ በልቤ። ከነድንጋጤዬ እየጎተተኳት ወደ ቦታችን ሄድን። ጭብጨባ እልልታ ሙሽራዬ ... ሙሽራዬ . . . .

ቄሱ ተነስተው የወጉን አደረሱ። እኛም የምንችላትን ያህል "አባታችን ሆይ!"ን ደገምን። ሙሽራዬ ግን ወይ ፍንክች። ፈራኋት። የተዘጋጀውን የቡፌ ምሳ ለማንሳት ተንቀሳቀስን። እየሄድን ሳለን እንደቅድሙ ድብን አደረገችኝ። አላበኝ። ምን ነካት አልኩ በልቤ።

እንደገና ጎንበስ ስል ". . . አንተም እሱም አንድ ናችሁ።" የሚል ቀጭን ውብና አስፈሪ ድምፅ ጆሮዬ ውስጥ ገባ። ተመስገን ከንክሻ ይሻላል . . . አይ፣ አይ . . . ንክሻ ይሻላል። አይ፣ አይ . . . ብዙ አሰብኩ። ማን ነው እሱ? እንዴ ምን ነካት? ባልሽ እኮ ነፕ ልበላት? ሰውስ ምን ይለኛል? ወይ ጭንቀት ጨነቀኝ። የቡፌ ማንሳት ሥነሥርዓት አበቃና ሚዜዎቻችን በሰሃን በሰሃን ያዙልን። ተጓተትን ወደ ክቡር ቦታችን።

ወግ አማረኝና ሳጎርሳት እጄን ዘረጋሁ። የብልጠቷ ብልጠት እምቢም ሳትል እንደመገረም አለችና ጣቴን ቅርጥፍ አደረገችው። መላ አካላቴን ነዘረኝ። ወደ ጆሮዋ ጠጋ አልኩና ምን ሆነሻል? ጤና አይደለሽም እንዴ? አልኳት። የተቆጣሁ መሆኔን ዕድምተኞች እንዳያውቁብኝ ፊቴን ፈገግ አደረግሁ። ልቤ እንደጨለመ። በሹሉ ጫማዋ እግሬን ድብን አድርጋ ረገጠችው። የምሆነው ጨነቀኝ። ግራ ተጋባሁ። በጣም ቀረብኳትና ምነው? አልኩ። በሹክሹክታ "ገና ምን አይተህ" ብላኝ ኩምጭጭ አለች። የበላሁት ተናነቀኝ። አሰብኩ አሰብኩና ሚዜዬን ጠርቼ ችግር ካለባት እንዲጠይቃት ነገርኩት። ለካስ ሞቅ ብሎታል። "ኖ ፕሮብሌም" ብሎኝ አረፈው። ወይ ጭንቀት። ያልታደልኩ ሙሽራ።

የመኪናችን ሹፌር ከመኪናው ወርዶ ከሚዜዎቼ ጋር ይመካከራል። አጋጣሚውን ልጠቀም ብዬ ስፈራ ስቸር ምነው ችግር አለብን ይሆን? አልኳት። እንዴት የለባችሁም! አለባችሁ እንጂ። ስማ! እኔ እኮ እኔ ነኝ። ለእኔ ለራሴ ከማንም በፊት የማውቅ እኔ ነኝ። ተጠራራችሁ - ተወያያችሁ - ለእናንተው ጥቅም። ለእኔማ የማውቀው ስንት ድንቅ ሃሳብ አለኝ። እኔማ ለእኔ የሚሆን ስንት ምኞት አለኝ። እናንተ ግን በእኔ ላይ ተስማማችሁ። እናም ስምምነታችሁ የእኔ ሆኖ ተቆጠረ። ለአንቺ ነው የተስማማነው አላችሁ። ለእኔ እንደሆነ ተቆጠረና ተፈጸመ አላችሁኝ። እኔና ውስጤ ስንወያይ ግን አልተፈጸመም አልኩ። እናም ቆነጠጥኩህ - እናም ነከስኩህ እናም ረገጥኩህ ገና ደግሞ . . . ደግሞ፣ ደግሞ አቅምም ባይኖረኝ ሁሉም ቢያቅተኝ። ያኔም ያከትማል። የእኔና የአንተ ነገር ይፈጸማል። እናም እናንተ ታዝናላችሁ። ጥቁር ልብስም ትለብሳላችሁ። እኔ ግን፣ እኔ ግን . . . እንጃ።

ታዲያ ለዚህ መፍትሔው ምንድ ነው ትያለሽ? መፍትሔውንማ እኔን እንደኔነቴ መተው። እኔን መተው

- ለቀቅ አድርጎ የምትወድህን የምትፈልግህን ማግባት አልያም እንደድሮህ ወንደላጤ መሆን ብቻ ነው።

አንቺስ?

ለእኔማ እኔ አውቃለሁ። ለእኔ እናውቃለን ያሉት ያወቁት አንድ ነገር ምን መሰለህ? ባል እንደሚያስፈልገኝ ብቻ ነው። ምን ዓይነት ባል? ቆንጆ፣ ፉንጋ፣ ፈሪ፣ ደፋር፣ ሩህሩህ፣ ጨካኝ፣ ሌባ፣ ጨዋ፣ ሌላም፣ ሌላም ሊሆን ይችላል ያንን የማውቅ እኔ ብቻ ነኝ።

አሁን ሥነሥርዓታችን እንዳይበላሽ ለምን ለመደሰት አትሞክሪም?

ደስታ? ደስታ? ምን ዓይነት ደስታ? ደስታ እኮ የውስጥ ነው፣ ሰው እኮ ተደሰት ስለተባለ ብቻ የሚደሰት ፍጡር አይደለም። ሲደሰት ግን ይደሰታል። ደስታው ፍፁም ሲሆንም ይገልጸዋል። እናም ያኔ ሀሴት ያደርጋል። ይህ ይሆን ግን ተደሰትኩ ቢል ሁለመናው ይዋሻል። ያልተደሰትኩ ደስተኛ ለመሆን ደግሞ አልፈልግም። ስለዚህ እመነጫጨቃለሁ እናም እራገጣለሁ። ገና ደግሞ . . .

እግዚኦ፣ አውጣኝ አልኩ በልቤ። ታዲያ ለምን ይህን ሁሉ ነገር በፊት አትነግሪኝም ነበር? አሁን እኮ ሰዓቱ አልፏል። እንዴት ልንገርህ። እንዳልነግርህማ አፌን ሸበባችሁት – ለጎማችሁኝ፣ በበህል እስር ቤት አሰራችሁኝ፣ በቄሶች ፀበል አደነዘዛችሁኝ፣ በጨዋ ጨውዬሽ ወግ ለጎማችሁኝ። እነሱ በማይገባ አባታዊና እናታዊ ስልጣን ተጠቀሙብኝ። አንተም በክብርና በገንዘብ ጉቦህ ዓይናቸውን አጨለምክና ልባቸውም ጨልሞ የእኔን ነፃነት አጨለሙብኝ። እናም መናገሬን በመናገራቸው ዋጡት። ጩኸቴንም በትልቁ ጩኸታቸው ሸፈኑት እናም ወሰኑ። ከውሳኔያቸው በኋላ ስነቃ መፍትሔው ወለል ብሎ ታየኝ። እናም ቆነጠጥኩህ፣ እናም ነከስኩህ፣ እናም ረገጥኩህ፣ ገና ደግሞ . . . በነገራችን ላይ ጊዜው አላለፈም። አንተ እንደእኔ ፈሪ ካልሆንክ እንዲያውም ጊዜው አሁን ነው። ከደፈርክ መፍትሔው በጃችን ነው።

መፍትሔው ምንድነው? ብዬ ተቆጣሁ።

ግደለኝና ሙት። በቃ፣ ግድል አድርገኝና ሙትት በል።

አልፈልግም! አልፈልግም! አንባረቅሁኝ ሳላስበው።

የመኪናችን ሹፌር መጣ። እንደተሞሸርን ነን። አንገቷን ደፋ አድርጋ ልክ እንደ እውነተኛዋ ሙሽራ ተሽኮረመመችና እጇን ሰዳ ልምዝገ አደረገችኝ። እጇን ሰደድኩና ልምዝግ አደረግኋት። ሹፌሩ እየነዳ ክላስኩን እያስጮኸ ይከንፋል። ቀና አለችና በሹክሹክታ "አሁን እየጎበዝህ ነው በርታ እሺ" አለች ጮክ ብላ ሹፌራችን አፍሮ ዞር አለ። እሷ ተሽኮረመመች። እኔም አፈርኩ። ደነገጥኩም። የምንጫወትም መስሎት ክላስኩን ለቀቀው።

እጮሃለሁ፣ እጮሃለሁ፣ ጥሪቅ ነው በላኝ ኡ.ኡ.ኡ. እላለሁ። ሾፌር . . .ሾፌር . . . አቁምልኝ አልፈልግም . . . አቁምልኝ በላኝ በላኝ ኡ.ኡ.ኡ . . .

ሹፌሩ መኪናውን አቆመና ወርዶ እየተጣደፈ ሄደ። ሚዜዬን ሊፈልግ እንደሆነ ገብቶኛል። እነሱ እስኪመለሱ እኔን አተካራ ገጠመችኝ። እባክሽ ስነስርዓቱ ይለቅና እንወያያለን። እባክሽ ትንሽ ታገሺ።

አይ! ሞኝህን ፈልግ። አልታገስም። አንተ ከነክብርህ ተቀምጠህ እኔ ክብሬ ከጠፋ በኋላ ልንወያይ! አንተ የልብህ ሞልቶ የእኔ የልቤ ጎድሎ ልንወያይ! ሞኝህን ፈልግ። አልቅዬ ግደለኝና ሙት ሁሉም ያከትማል። እምቢ ካልክ . . .

ሚዜዬ እየተቻኮለ መጣና "ምነው ምን ሆናችኋል?" አለ። እሷ እንደመሽኮርመም ጀመረች። ሾፌሩ ድንጋጤው ስላልለቀቀው ፀጥ አለ። ሚዜዬ ግራ ተጋባ። ከእኛው ጋር ሊሆን ቪዲዮ ቀራጩን ትቶ ከፊት ወንበር ላይ ጉብ አለ። ጉዞ ቀጠልን። ተጫወቱ አለን ሚዜዬ። ወዲያው ድብን አርጋ ቆነጠጠችኝ፣ ደገመችና በታኮዋ እግሬን ውግት አደረገችው። ዝም አልኳት። ዝምታ አይሉት ዝምታ፣ ዝምታ . . . ዝም በጊዜ ዕጥረት ሸርሽራችን ተሰርዟል አለ ሚዜዬ። ኡ.ኡ.ኡ. ብላ ጮኸች። ሾፌሩ በድንጋጤ ፍሬን ሲይዝ ከኋላ ካለው መኪና ጋር ተላተምን። ሚዜዬ አፉን ይዞ ቀረ። እኔ በድንጋጤ ራሴን ልስት ምንም አልቀረኝ። ሚዜዬ ምን ነካሽ? ምነው? ኧረ ነውር ነው ብሎ ጮኸ።

ዝም አልልም እጮሃለሁ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት ዝም አልልም። . . . ነፃነቴን ከነክብሬ አገኘዋለሁ። ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ዝምታ የለኝም። እንደ ደካማ ሴት ለማልፈልገው ሰው ክብሬን ሰጥቼ በፍቺ አልገላገልም። ትንሹን ክብሬን ሰውቼ ትልቁን አገኘዋለሁ። ወጥቼ በእኔ ላይ የወሰኑትን ሁሉ አሳፍራቸዋለሁ እያለች መስቀል አደባባይ ላይ የሙሽራ መኪናዋን የጎን መስታወት ጫማዋን አውልቃ ሰባበረችው። አደባባዩ ላይ ቆምን። አጃቢዎቻችንም ቆሙ። ህዝብ ተሰበሰበ። በጫማው አንዷ እናቴን አለችኝ። ደማሁ። እብድ አላገባም – ጥሪቅ አላገባም – ስለ እኔ እኔ እወስናለሁ። ለራሳችሁ ታውቁ ይሆናል ለእኔ ግን አታውቁልኝም። ለእኔ እኔው አውቃለሁ። እያለች ስትጮህ የሕልም ጩኸት ከእንቅልፌ አባነነኝ።

እማማ ድንቄ በሉ እንግዲህ ሕልሜን ይፍቱልኛ!

አይ! ልጄ ተወኝ እባክህ እንደው በደፈናው ድንቂም ትሞሸርች – ድንቂም ተሞሸረች።

-----------------------------

ዜናዎች በሥዕል



የጥምቀት በዓል በአዲስ አበባ ሲከበር



የገብሬል በዓል.በሳንዲያጐ



ብስክሌተኛው ሳምሶን የሰላም ችቦ ለአትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን የደብር አለቃ ለመላከ ጸሐይ ገብረማርያም ሲያስረክብ



የገና በዓል በአትላንታ ሲከበር

# ለ ቅ ም ሻ . . . ከዚህም ከዚያም
# ከድሮ ጋዜጦቻችን

## ተራማጅነት

(ከጳውሎስ ኞኞ)
አዲስ ዘመን ጥር 19 ቀን 1968 ዓ.ም.

ሁሉም በእግሩ መራመድ እንደሚችለው ዓይነት በሀገር ጉዳይ ተራማጅ ነኝ ታጋይ ነኝ ባዩ በዝቷል። ከልብ ከሆነ ደስ የሚያሰኝ ነው። ከአንገት በላይ ለይስሙላ ከሆነ አሽሟጠጥናችሁ። መስሎ ለመታየትና ለመገመት ወይም ከአካባቢ ጋር መስሎ ለማደር የሚደረግ ከሆነም ታዘብናችሁ።

ተራማጅ የሚለው ቃል ብዙውን ግራ አጋብቷል። አፈ-ጮሌው ተራማጅ ነኝ እያለ ራሱ ለራሱ ስለሚመሰክር ሌላው ግራ ገብቶት አንገቱን ደፍቶ "እንደምትለው ይሁንልህ" ይለዋል። ጠጉርን ማጎፈርና ጢምን ማጎፈር የተራማጆች ምልክት ነው ስለሚባል ልሁን ባዩ በዝቷል። ጠጉር ቆራጮችንና ጢም ላጪዎችን ሥራ ማሳጣት ነው እንጂ ጠጉር የተራማጅነት ምልክት አይደለም። የሌኒን ስዕል ደረት ላይ መለጠፍና ቀይ ከራቫት ማሰር የተራማጅነት ምልክት ነው ይሉናል። እውን ነው እንዴ? መስሎ ለመታየት ካልሆነ በስተቀር በግብር የማይታይ ባዶ ተራማጅነት የተለሰነ መቃብር ነው። መቃብር ላዩ ሌላ ውስጡ ሌላ ነው። ተራማጅነት ጥቅም እስካልተነካ ድረስ መለፍለፍ የማያምን ነው። ተራማጅ ለወገኑ ለሀገሩ ዕድገት ባለው ኃይልና አቅም የሚሰራ፣ አልኩ ባዮችን የሚቆጣጠር፣ ከራሱ ጥቅም ይልቅ ለሌላ ጥቅም የሚሰዋ ነው። እሱ ነው ተራማጅ ማለት። ማንም የማንንም ልብና ተግባር ሳያውቅ ተሽቀዳድሞ አድሃሪ ብሎ መሳደብ የተራማጅነት ምልክት አይደለም። የሚመስላቸውም ስላሉ ብዙ ስህተት ያደርጋሉ። ተራማጆች አይሳደቡም። የመስሪያ እንጂ የመለፍለፊያ ጊዜ የላቸውም። ተራማጆች የሀገርና የወገን ፍቅር ስላላቸው በወገን ዕድገት አይመቀኙም። በወገን ላይ ተንኮል አይገምዱም። ታታሪ ወገናቸውን ያበረታታሉ እንጂ የሚቀበርበትን ጉድጓድ አይቆፍሩም። ተራማጆች ቀን ሲለፍፉ ውለው ሌሊት ለጓደኛ መውደቂያ ጉድጓድ ሲምሱ አያድሩም። በተራማጅ ዘንድ ሰው ሰው ነው። ባለቡቱቶውም ሰው ነው፣ ባለሱፉም ሰው ነው። እግሩ ነቅቶ በባዶ እግሩ የሚሄደውም ሰው ነው፤ ባለመካናውም ሰው ነው። ተራማጅ ሁሉም ወገኑ መሆኑን ያውቃልና ሁሉንም እኩል ያያል። የበታቹን አይንቅም። በበላዩም አይመቀኝም። ለሁሉም ይሰራል፣ ለሁሉም እድገት ይመኛል። ተራማጅ ዓላማውን በስድብ ሊያሳምን አይሞክርም። በማስተማር መላልሶ በመንገር፣ በግብር በመግለጥ፣ ብዙ ተመታዮችን ያከማቻል። የተበላሹ ወገኖች ሲያጋጥሙት በፍቅር ይስባቸዋል እንጂ በስድብ ብልሹነታቸውን አያባብስም። ከሁሉ ጋር ፍቅር አለው። የሚጠሉትን ብድር ለመመለስ በጥላቻ አያይም። በተግባሩ እንዲወዱት ዓላማውም እንዲከተሉ ያደርጋል እንጂ በግድ ውደዱኝ በንግግሬ አክብሩኝ አይልም። ተራማጅ፣ ወገኑ በሚያልፍበት መንገድ ላይ እንቅፋት የምትሆን ድንጋይ ቢያይ ያነሳታል። የወገኑ ጉዳት ጉዳቱ ነውና ያስብለታል። የመንገድ አጠገብ ጋሬጣን ተሸሎክሉኮ አያልፈውም። ያላየ ወገኑ እንዳይቧጥጥ ለሌላው ወገኑ ማለፊያ ያሳምርለታል። ተራማጅ ለድሃ ዳቦ እንጂ ልፍለፋና ጉራ እንደማያጠግበው ያውቃል። ድሆች ወገኖቹ ከድህነት የሚላቀቁበትን መንገድ ያስባል፣ ይፈጥራል። አሳብ ያቀርባል፣ ያስተባብራል፣ ያሰራል፣ ይሰራልም። ለወገኑ የሚያደርገው ድካም የመንደላቀቂያ ደስታው ነው። ለተራማጅ ከዚያ የበለጠ ደስታ የለውም። ለተራማጅ ሁሉም ወገኑ ነው። በጎሣ አያደላም። ለተወሰነች ክፍለ ሀገሩ ብቻ አይጥርም። በሃይማኖት የማይመስሉትን አይንቅም። ሁሉም የሁሉ መሆኑን ያውቃልና ለሁሉም እኩል ይሠራል። ለሁሉም እኩል ያስባል። ሁሉም ጥሩ ውጤት እንዲያገኙ ይመኛል። ለሁሉም ዕድገት ይጓጓል። ተራማጅ ሁሉም ቁልቁል አዘቅት ወርዶ በድህነት እንዲማስን አይመኝም። በአሳቡም አያሳድርም። ድሆች ከፍ ብለው ሽቅብ የሚወጡበትን መንገድ ያበጃል። ያስባል። ይነግራል። ያስተምራል። ለዚህም ዕድገት ታላቅ ጥረት ያደርጋል። ተራማጅ በቃላት ፈጠራና ድርደራ የሚዘባነን አይደለም። በየቦታውም ያለ ሰው እንደማይሰራ ጽናጽል የሚጮህ አይደለም። ወይም የሌሎችን አባባል የሚያስተጋባ የገደል ማሚቶ አይደለም ወይም በሰው እጅ እንደሚሞላ ሰዓት ቆሞ ሞይውን የሚጠብቅ ግውዝ አይደለም። ራሱ ለወገኑ የሚበጀውን ያውቃልና ይሠራል። ያስተምራል። ይናገራል። ያደርጋል። ይህ ነው ተራማጅነት። ሌላው ግን አጉል ጉራ ነው።

---

## አቢሳ

ከሰይፉ መኩሪያ (አትላንታ)

አቢሳ በየዓመቱ የሚከበር የአፍሪቃውያኖች በዓል ነው። በአይቮሪኮስት ጋራንድ ባሳም በምታባል ከተማ ውስጥ የሚከበረው ይህ ዓመት በዓል የአፍቃሪውያኖችን ሰብዓዊ ስሜትን የሚያንፀባርቅና በተለይ የአፍቃሪውያኖች የነፃነት ስሜት ከአገራዊ ነፃነት በላይ ግላዊ ነፃነትን ቢያንስ በዓመት አንዴ እንደፍላጎታቸው መሆንን ማንፀባረቁ ነው። አቢሣ የዕርቅና የእውነት መናገሪያ አመት በዓል ነው። ከየቦታው እየጎረፉ የሚመጡት ሰዎች ያለአንዳች አስተናጋጅ ወይም ያለምንም ዝግጅትና መመሪያ ተሰባስበው

የልባቸውን የሚናገሩበት ያስቀየማቸውን የሚዘልፉበት፣ ያስቃየሙትን ይቅርታየሚጠይቁበት፣ የሚያፈቅሩትን ሰው ማን መሆኑን/መሆኗን በህዝብ ፊት የሚናገሩበት ... በአጠቃላይ አንጎልና ልብ፣ መንፈስና ሥጋ የሚዋሃዱበትን የአንድ ሳምንት በዓል ነው። በዚች በደቡብ አይቮሪኮስት የምትገኘው ከተማ ውስጥ የሚኖሩት የእንዚማ ተወላጆች አቢሣን የሚያከብሩት በትልቁ ነው። በበዓሉ ሳምንት ሁሉ ነገር ለጊዜው ይቆምና በሚደለቁ ከበሮዎች ዙሪያ ተሰብስቦ ከከበሮው ምት ጋር የሚዋሃዱ ጭፈራዎች ይካሄዳሉ። በዛ ሳምንት ልጅ ሲወለድ ስም የሚሰጠው ከበዓሉ በኋላ ይሆናል። ሰው ሲሞትም እንዲሁ ቀብሩ ከጭፈራው በኋላ ይደረጋል። በዛ ሳምንት ማንም ሰው ጋብቻ አያካሂድም። ሁሉ ነገር ከአቢሣ በኋላ ይባላል። የአቢሣ በዓል ሲጀመር በዝግታ ነው። በዓሉ ከመጀመሩ ከሳምንት በፊት የመንደሩ አለቃ የአቢሣን መምጣት ያበስራል። ቀኑ ሲደርስ 'ሰባቱ ቤተሰቦች' በሚል የሚታወቁት የእንዚማ ሰዎች ከበሮአቸውን በምስጢር ከደበቁበት ቦታዎች ያወጡና የተለመደው ጎዳና ላይ ሆነው ከበሮአቸውን ሲደልቁ የከተማው ሰው ቀስ በቀስ ወደ በዓሉ መጉረፍ ይጀምራል። ጭፈራው ይቀጥላል። እንገት ደፋ ተደርጎ ለምድሪቷ ምስጋና እንደሚሰጥ ከወገብ ጎንበስ ተብሎ እግሮች ከከበሮዎች ምት ጋር እየተዋሃዱ በሚታይ ዳንስ ህዝቡ ወደ መንደሩ አለቃ ቤት ይሄድና ይሰበሰባል። የፀሎት ውሃ በየምረቃው ምድሪቷ ላይ ጠብ እየተደረገ (Libation) ፀሎት ይደረግና የጥንት አያቶች ይመርቁና . . .በዓሉ ይጀምራል። የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ እንዳስቀመጠው አቢሣ ያለ አንዲት ሌላ ፕሮቶኮል የሚካሄድ በዓል ነው። ሴቶች ፊታቸውን ለማሳመር ቀጫጭን መስመሮችን አይናቸው አካባቢ በነጭ ቀለም ያወፍራሉ። ወንዶቹም እንዲሁ ገፅታቸውን በቀለም ያሸበርቃሉ። ቀረብ ብለው ሲመለከቱ ደግሞ ለየት ያሉ ነገሮች መኖራቸው ይታያል። ተለቅ ያሉ ጡቶች ሴቶች ጭፈራው ውስጥ ሲፈነድቁና ሲደንሱ ለሚያይ ሰው የበዓሉ ዋና አዳማቂ ይሆናሉ የሚል ግምት ይሰጣል። ሆኖም ጠጋ ብሎ ለሚመለከት ሰው ባለትላልቅ ጡቶች – ሴቶች ከመሆናቸው ይልቅ ወንዶች መሆናቸውን ይገነዘባል። በሌላ በኩል ደግሞ ኮስተር ብለው ኮታቸውንና ክራባታቸውን አስረው የሚታዩት ወንዶች ደግሞ ወንዶች ሳይሆኑ ሴቶች መሆናቸውንም ያያል። አቢሣ 'ምን ይሉኛል?" የሚል መንፈስ ጭንቀት የሌለው ለአንድ ሳምንት ሙሉ ትዝብት፣ ቅሬታ፣ ይሉኝታ . . . ተቀባይነት የሚያጡበት በዓል እንደመሆኑ መጠን በሰዎች መሃል በየአንዳንዱ ልብ ውስጥ ያለውን ፍቅር በአደባባይ የሚወጣበት መድረክም ነው። የተከለከለ ፍቅር የተደበቀ ፍቅር፣ ነውር የተባለ ፍቅር በሙሉ በዛ ሳምንት እየተፍለከለከ ይነገራል። የአደባባይ ምስጢር ይሆናል። ባለትዳር የሆኑ ወንዶችና ሴቶች የሚወዱትን ሰው (ከትዳራቸው ውጪ) እከሌ መሆኑን በሙሉ ልብ የሚናገሩትም (እንደጋዜጣው አባባል "Erasing all inhibitions") ዓመት በዓል ነው። ዓመት ሙሉ ልብን ሲፍቅ የቆየ የፍቅር ቃጠሎ፣ ጨጓራን ሲገሽልጥ የነበረ ብሽቀትና ንዴት፣ በአደባባይ ያለአንዲት እፍረት የሚገለጥበትና የሚታወጅበት በዓል ነው። የአቢሣ በዓል ላይ ለመሳተፍ በቅድሚያ የሚከፈል የመግቢያ ዋጋዎች አሉ። ደናሾችና ጨፋሪዎች ቅናት የሚባል ነገር ላይኖራቸው፣ በሰው ላይ በደል ያደረሱ ደግሞ ተበዳይ የሚያቀርብባቸው ወቀሳ የህዝቡን ስድብና ውርጅብኝ በፀጥታ ሊቀበሉ፣ መስማማት ብቻ ነው። የመግቢያው ዋጋ ይኸው ብቻ ነው። አቢሣ የአፍሪቃዊ ባህልና መንፈሥ ያፈለቀውና አፍሪቃውያኖች አፍሪቃዊነታቸውን ብቻ ሳይሆን በምዕራቡ ዓለም ውስጥ እንኳ ያን ያሃል መኖሩ የሚያጠራጥረው የግላዊ ነፃነትን የሚቀበሉበት ሚስትነት፣ ባልነት፣ ፖሊስነት፣ ዳኛነት፣ ፖለቲከኛነት፣ ሰራተኛነት ዘመናዊ ተብሎ የሚጠራው ምዕራቡ ዓለም ባህል በየምክንያቱ ያልሳነጣጠቀውና የበታተነው ህይወትን መለስ እያደረገ ዘመናዊ ተለምዶዎችን በግል ነፃነት የሚያስጠይቅ ሲያስፈልግ የሚያስተች አፍሪቃዊ ባህል ነው።

-------------------------

## ተ መ ድ (ከሰይፉ መኩሪያ)

ባለፈው ጊዜ የተከበረው የተመድ 50ኛ የልደት በዓል የአለም መሪዎችን በአንድ ጎራ ስር አሰባስቦ ብዙ ንግግሮች (ከ184 መሪዎች በላይ) ተደርገዋል። ከአሜሪካው ፕሬዚዳንት በስተቀር እያንዳንዱ መሪ የ5 ደቂቃ ንግግር ብቻ እንዲያደርጉ በመደረጋቸው የተንዛዛ ሌክቸር የሌለበት በዓል ነበር ማለት ይቻላል። ሆኖም ቁም ነገር ያዘሉ አዳዲስ ሀሳቦች አልፈለቁም ማለት አይደለም። ከቀረቡት ሀሳቦች ውስጥ የSecurity Council Permanent Members (አሜሪካ፣ ራሽያ፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝና ቻይና ብቻ ናቸው) ጉዳይ አንዱ ነበር። አምስቱ Permanent members ሊሆኑ የቻሉበት የዓለም አቀፍ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ ቦታ ስለሌለው የአባሎች ቁጥር መጨመር ይገባዋል የሚል ነበር። የዓለም ህዝብን ደህንነት በሚመለከት ወደ ቢሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ያላት ህንድ እንኳ አባል አለመሆኗ በአሁኑ ጊዜ ተቀባይነት የማይኖረው ነገር ነው በማለት የበዓሉ ኮከብ የነበሩት የኩባው ፊደል ካስትሮ አማረዋል። ከዚህ ሌላ የኢራኑ መሪ ባደረጉት ንግግር ላይ የተ.መ.ድ እያደር የአሜሪካ ፍላጎት ለሟሟላት የቆመ ድርጅት እየመሰለ መጥቷል በማለት ወቀሳ ሲያቀርቡ ሌሎች የእስያና የአፍሪቃ መሪዎች የምዕራቡ ዓለም ሆዳም ነው። ብዙ ይበላል፣ ብዙ ይጠጣል፣ ብዙ ነዳጅ ያቃጥላል፣ ብዙ ሀብት ይሰበስባል፣ በዚህም የተነሳ ዓለም ውስጥ ብዙ ድህነትን ያስፋፋል በማለት አማረዋል። ከመቶ ሰማንያ አራት በላይ የሚሆኑትን መሪዎች ያስተናገደችው የኒውዮርክ ከተማ በሽንጠ ረጅም መኪናዎች ተጣባ እንደነበረና በተደረገው የጥበቃ (Security) ዝግጅት ምክንያት መንገዶች በመዘጋታቸው የትራፊክ እንቅስቃሴ ብስጩ የሚያደርግ እንደነበረ ተነግሯል።

# የትብብር ውጤት

(ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል)

ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ቸኩለንና ታክሲ ስንጠራ ወይም ስናስቆም የቀረበልንን ታክሲ የሚነዳው ኢትዮጵያዊ መሆኑን ስንመከት የሚሰማን ደስታ ግልፅ ነው። ኢትዮጵያዊ ስለሆነና እኔም ኢትዮጵያዊ ስለሆንኩ በነፃ ይወስደኛል በሚል አይደለም ደስታ የሚሰማን። ወገን የሆነ ሰው የማግኘቱ ለጥቂትም ጊዜ ቢሆን በራስ ቋንቋ ለማውራት ዕድል የማግኘቱ፣ "ታዲያስ ምን ወሬ አለ?" መባባል የመቻሉ ስሜት ነው። ታክሲውን የሚነዳው ኢትዮጵያዊ መሆኑስ ደስ አለን የታክሲ ኩባንያው ባለቤቶች ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን ሲያውቁ ደግሞ ምን ይሰማዎት ይሆን?

ዛሬ በአትላንታ ከተማ መንገዶች ላይ በብዛት የሚርመሰመሱ ታክሲዎች የኩባንያዎቻቸው ባለቤቶች በአብዛኛው ኢትዮጵያዊያን መሆናቸውን ያውቃሉ? ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ "ዩናይትድ ካብ፣ ክራውን፣ አሜሪካን ራፒድ፣ ወዘተ . . . የሚል መጠሪያ ስም ያላቸው ኩባንያዎችን መጥቀስ ይበቃል። በግልም ሆነ በጋራ ጥረት አድርገው የአሜሪካን የኑሮ ዘዴ በመረዳት ለራሳቸውም ሆነ ለወገኖቻቸው የሥራ መስክ በመክፈት የ"አሜሪካው ሕልም" (American Dream) የተሳካላቸውን ወገኖቻችን ልናደንቅና ልንኮራባቸው ይገባል። ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት የበቃነው ዘንድሮ 13ኛውን ዓመት ያከበረውን በአትላንታ ከተማ ከሚገኙት የታክሲ ኩባንያዎች አንዱ የሆነውን የዩናይትድ ካብ ካምፓኒ ታሪክ በመጠኑ ለማውሳት ስለፈለግን ነው።



ከኩባንያው ባለቤቶች ጥቂቶቹ

የዛሬ 13 ዓመት ነበር በታክሲ ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚኖሩ 14 ኢትዮጵያውን ዘር፣ ጎሳ፣ ሃይማኖት ሳይለዩ ይሰባሰቡና በጥቂት ካፒታል (እያንዳንዳቸው ከ$500.00 ያልበለጠ በማዋጣት) ይህን ኩባንያ ይመሰርታሉ። ካፒታሉን ለመፍጠር ያበደራቸው ኩባንያ አልነበረም። ራሳቸው በየዕለቱ ከታክሲ ገቢ ከሚያገኙት በማጠራቀም ነበር። ሃያ አምስት ታክሲዎችን ይዘው ጀመሩ። 14ቱን ራሳቸው እየነዱ 11ዱን ደግሞ ሌሎች እንዲነዱ በማድረግ። ዛሬ ከ13 ዓመት በኋላ በኩባንያው ስም 170 (አንድ መቶ ሰባ) ያህል ታክሲዎች አሉዋቸው። በባለቤትነት ከጀመሩት 14 ሰዎች መሐል አንዱ ብቻ በችግር ምክንያት ሲወጣ 13ቱ አሁንም አንድ ላይ ናቸው። ኩባንያው ከዚሁ የታክሲ ሥራ ጋር የተያያዘ የራስ አገዝ ኢንሹራንስ አለው። የራሱ የሆነ የኢንሹራንስ ኩባንያ ስላለው መኪናዎቹ በሙሉ በዚሁ የኢንሹራንስ አገልግሎት የተሸፈኑ ናቸው። ይህንኑ የኢንሹራንስ አገልግሎት ራሱ ካለው 170 ታክሲዎች ሌላ 80 ለሚሆኑ የሌላ ኩባንያ ታክሲዎች ይሰጣል። ዛሬ ዩናይትድ ካብ ካምፓኒ ትልቅ ኩባንያ ነው። 13ቱ ኢትዮጵያውያንም በኅብረት የመሥራት ጥቅሙን ለወገን ያሳዩበት አንድ ምሳሌ ነው። ይህንኑ በተመለከተ የኩባንያውን ምክትል ፕሬዚዳንትና ገንዘብ ያዥ አቶ ጅፋር አባ ጀበልን አነጋግረናቸው ነበር። ጅማ ተወልደው የአ/አ ጄኔራል ዊንጌት ት/ቤት ተማሪ የነበሩት አቶ ጅፋር ስለኩባንያው ዕድገት በሰፊው ከገለፁልን በኋላ በየደረጃው የገጠሟቸውን ችግሮችና ችግሮቹን ለመቋቋም ያደረጓቸውን ነገሮች አስረድተውናል።

"በግሩፕ ሆኖ መስራት ራሱ በሃሳብ ልዩነት አለመግባባት አንዳንዴ ሊፈጠር ይችላል። መድኃኒቱ ተቀዳሚ በሆነው ዓላማ ላይ በማተኮር መደማመጥና መቻቻልን ዋንኛ መሳሪያ ማድረግ ነው። አንድ አዲስ ነገር ለመፍጠርም ሆነ ለማሻሻል የሁሉንም ስምምነት ስለሚጠይቅ እዚያ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚደረጉ የሃሳብ ልውውጦችና የሚቀርቡ የተለያዩ ሃሳቦችን ሁሉም በቀና መልክ ስለሚያየው እንደማመጣለን፣ እንቻቻላለን፣ ስለተቻቻልንም ይኸው 13 ዓመት ሳንለያይ አሁን ካለንበት ደረጃ ደርሰናል" አሉን። "የውጪ ሰው በመሆናችን፣ በንግግራችንም ዘይቤ (accent) በተጨማሪም ጥቁሮች በመሆናችን አንዳንድ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ ሰራተኞች፣ አንዳንድ ተሳፋሪዎቻችንም ሊቀበሉን ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በሁኔታቸውና በድርጊቶቻቸው ቢያጋጥመንም ችለነዋል። መቻልን የሚያህል ነገር የለምና አብረን ከችግሩ ጋር የመኖር ልምድ ስለቀሰምን አይሰማንም።" አሉን። ስለወደፊቱም ሲያወሱ "በመካከላችን መፋቀር፣ መተማመንና መተሳሰብ ስላለ እድገታችን አያቆምም" ብለውናል።

ከእነኚህ ወገኖቻችን ብዙ እንማራለን። በጋራ የመስራት ጥቅሙን በጉልህ አሳይተውናል። የሃሳብና የአመለካከት ልዩነቶችን ተደማምጦ በመቻቻል ዋነኛ በሆነው የጋራ ዓላማ ላይ ብቻ ማተኮር ለጋራ ብልፅግና ፍቱን መድኃኒት መሆኑን አስተምረውናል። የመተማመንና የመፋቀር ውጤት ጥሩ መሆኑን ህያው ምስክር ሆነዋል።

## <u>በስደት ላይ የምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ውሳኔዎችን አስተላልፋለች።</u>

በካሊፎርኒያ የቤይ ኤርያ መካነ ሰላም መድኃኒአለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ ውስጥ ከጥር ፯ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር ፲ ቀን አራት ቀን የፈጀ ቅዱስ ሲኖዶስ (የጳጳሳት ጉባኤ) እና ርከበ ካህናት (የካህናት ጉባኤ) የተካሔደ ሲሆን በጉባኤውም ላይ ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳትና በምዕራብ ሀገሮች ለአገልግሎት በየስፍራው የሚገኙ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ካህናትና ዲያቆናት በመላ ተካፋይ ሆነውበታል። ማክሰኞ ጥር ፯ ቀን የጉባኤው ተሳታፊዎች ቦታ ቦታቸውን እንደያዙ በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ፓትሪያርኩ እንደራሴ ጉባኤው በፀሎት የተከፈተ ሲሆን የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ ፓትሪያርክ መልዕክት የጉባኤው የመጀመሪያው ንግግር በመሆን በንባብ ተሰምቷል።

ከዚያም በመቀጠል በብፁአን ሊቃነ ጳጳሳት ስለቤተክርስቲያን ዓላማና ተግባር ሰፊ ገለፃ የተሰጠ ሲሆን ጉባኤው በቀረቡት ማብራሪያዎች ላይ ጥልቅ ውይይት ካደረገ በሁዋላ የጋራ መግለጫዎችን ያወጣ ሲሆን ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳት ብቻ የተሳተፉበት ቅዱስ ሲኖዶስ ደግሞ ከዚህ በታች በሰፈሩት ርዕሶች ላይ ሲኖዶሱ ውሳኔዎችን አስተላልፏል። ፩) ስለቀደመው ሲኖዶስ ትክክለኛነት፣ ፪) ስለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሕጋዊ ፓትሪያርክነትና ከበደል ንፁህ መሆን፣ ፫) ስለ ቤተክርስቲያን አንድነት፣ ፬) ስለ ሰው ልጆች መብት መከበር፣ ፭) ስለአዲስ የሚሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ፮) ስለ ሥርዓተ ፀሎት ሲሆኑ፣ በጉባኤውም መዝጊያ ዕለት በሊቃነ ጳጳሳት መሪነት ቅዳሴ ተቀድሶ ሁሉም በመጡበት አኳኋን ወደየስፍራቸው ተመልሰዋል።



## የገብርኤል በዓል በሳንዲያጎ ተከበረ

ከሣንዲያጎ ተዋህዶ

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር December 30, 1995 ቅዳሜ የዋለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የታህሳስ አመታዊ በዓሉን በካሊፎርኒያ ስቴት የሚገኙ አንድ ሊቀ ጳጳስ፣ ካህናት፣ መዝምራንና የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ከልዩ ልዩ ስቴት የመጡ እንግዶችና የሣንዲያጎ ነዋሪዎች የሆኑ ኢትዮጵያውያን በብዛት በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ ተከብሮአል። ለበአሉ ድምቀት ከሰጡት ዋና ዋና ክፍሎች አንዱ ከሁለቱም የሎስአንጀለስ ቅድስት ማርያም አብያተ ክርስቲያናት፣ ከኦክላንድ በርክሊ መድሃኔያለም ቤተ ክርስቲያን የተውጣጡ የመዘምራን ክፍል ያቀረበው ልዩ የመዝሙር ዝግጅት ነበር።

መዝሙሩ መጀመሪያ በህፃናት ተከፍቶ፣ ወጣቶቹ በህብረት የዘመሩት በዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያ እየታጀበ ነበር። በተለይም ከኦክላንድ በርክሊ የመድሃኔያለም ቤተክርስቲያን መዘምራን በሽብሸባ እያስረገጡ፣ በመቋሚያና በፅናፅል ያሰሙት ያሬዳዊ መዝሙር ለበአሉ ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል።

ከዚህም ሁሉ በላይ ሊቀ ጳጳስ አቡነ መልከፃዲቅ የቤተክርስቲያኑ ካህንና አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ሰፋ ያለ ትምህርተ ወንጌል ስለሰጡ በጠቅላላው የበአሉ አከባበር ላይ የተገኘው በሺህ የሚቆጠር ህዝብ ደስታውን በጭብጨባና በእልልታ ገልጦአል። ስዕለትና ብፅአ ተፈፅሞላቸው ከልዩ ልዩ የአሜሪካ ስቴቶች ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ድረስ የመጡ ምዕመናን ነበሩበት።

"የጠየቁትን የማይረሳ፣ የለመኑትን የማይነሣ፣ በደልን ሁሉ ይቅር ባይ የሆነ መሃሪ አምላክ የልባችሁን ምኞት ይፈፅምላችሁ፣ ፀሎታችሁን፣ መባችሁን ሁሉ ተቀብሎ ከፊቱ የሚቆም ሊቀ መላዕክት ቅዱስ ገብርኤልን በመላክ ከአደጋ ሁሉ እንዲታደጋችሁ የአባቶቻችን አምላክ በረድኤት አይለያችሁ፣ ፀጋውን ያብዛላችሁ። ፍቅር አንድነትና ሰላምን ይስጣችሁ። ዛሬም ዘወትርም ለዘለአለሙ አሜን"
(በመጋቤ አእላፍ መከብብ አጥናው የተፃፈ መልእክ ብስራት ከተሰኘው መፅሀፍ የተወሰደ ጥቅስ)

ይህ በአል በተከበረበት ዕለት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያኖች መለያቸው የሆነውን የሀገር ልብሳቸውን በመልበስ ጥራቸውን፣ ከዘራቸውን እንዲሁም ባንዲራቸውን በመያዝ ለበአሉ ልዩ ድምቀት ሰጥተውት ውለዋል። እንዲያውም ከብዙ ሰዎች አንደበት እንደተሰማው በአሉ የኢትዮጵያው የቁልቢ ገብርኤልን በአል አስመስሎት ውሏል።



# ቡናችንን ለዓለም ገበያ ያስተዋወቁት ከድር ኤባ

በአገራችን ብዙ ሰዎች የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ባገርም ይሁን አልፎ አልፎ በውጪው ዓለም ታዋቂነትን አትርፈዋል። በእስፖርት፣ በስነጽሁፍ፣ በሥዕል፣ በሙዚቃ ታዋቂ የሆኑ ወገኖቻችንን የሥራቸው ውጤት ይፋ ሆኖ ሕዝብ ጋ ስለሚደርስ በቀላሉ ታዋቂነትን ያገኛሉ። ሆኖም ድርጊታቸውና አገሪቷን በማሳወቅ ያደረጉትን አስተዋጽዖ በጽሁፍ መልክ አዘጋጅቶ ለመጪው ትውልድ ለታሪክ መዘክርነት ማስቀመጥ ብዙም አይታይም። ታሪክ ተጽፎላቸው በአብዛኛውም ሲወሳላቸው የምናገኘው የፖለቲካ መሪዎችን ነው። አገራችንን ከማሳደግም ሆነ በውጪው ዓለም ከማሳወቅ አንጻር ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት እነኚህ የፖለቲካ መሪዎች ብቻ አይደሉም። ለአገር ብልጽግና በኤኮኖሚው መስክ ትልቅ ተግባር የፈጸሙ ወገኖቻችንን ታሪክ ለማወቅ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ የተቀመጠልን ዘገባ አለ ለማለት ያስቸግራል።

የአገራችን ኤኮኖሚ አውታር በሆነው ግብርና ሥራ የተሠማሩ ገበሬዎችና የግብርናን ውጤት በዓለም ገበያ በማስተዋወቅ አስተዋጽዖ ያደረጉትን ነጋዴዎችን ታሪክ በወሬ ወሬ ከምንሰማው በቀር በጽሁፍ የተቀመጠ ታሪክ አዘል ጽሁፍ አናገኝም። ቢያንስ ቢያንስ ለመጪው ትውልድ ልምድ መቅስሚያ፤ ለባለታሪኮቹም ማስታወሻ እንዲሆን የነኚህን ሰዎች ታሪክ ማጤኑ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም።

የመጽሔት ዝግጅት ክፍላችን ይህንኑ ግንዛቤ በመውሰድ በተለያዩ መስኮች ለአገሪቷ ታዋቂነትን ያተረፉ ግለሰቦችን ታሪክ ማቅረብ አስፈላጊነቱን አምኖበታል። ንግድ ሀገርን የሚያኮራና ወገንን የሚደግፍ እንደመሆኑ መጠን ጠንካራነትን፣ ድፍረትን፣ ብልህነትንና ሀሳበ ቀራጥነትን ይጠይቃል። በተለይም በንግድ ሥራ ከከፍተኛ ደረጃ ደርሶ የሥራ እንቅስቃሴና ፍሬ በሀገር ውስጥና ከውጭ አገሮችም ጋር ግንኙነትን በማድረግ እራስን ለማሳወቅ ታላቅ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ይጠይቃል።

በዚሁ መሠረት የአገራችን ዋና የኤክስፖርት ምርት የሆነውን ቡና በዓለም ገበያ በማቅረብ ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረጉትን የቀኛዝማች ከድር ኤባን ታሪክ በማቀናበር አቅርበናል። እንደ አገራችን አቆጣጠር በ1987 ዓ.ም.ባደረባቸው ህመም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በስፖርቱ ዓለም ታዋቂ የነበሩት የይድነቃቸው ተሰማ የቅርብ አብሮ አደግ ጓደኛ ቀኛዝማች ከድር ኤባን በስም የማያውቅ ኢትዮጵያ አለ ለማለት አንደፍርም። ከድር ኤባ በቡና ሥራ ታዋቂ ለመሆን የቻሉት እንዴት ነው? የሕይወት ታሪካቸውስ ምን ይመስላል? ሌላውስ ከሳቸው ምን ትምህርት ይቀስማል? በማለት ከየቦታው በማሰባሰብ የተጠናከረውን አጭር ዘገባ እናቀርባለን።



ቀኛዝማች ከድር ኤባ በቡናና በወርቅ ሥራዎች ይታወቁ ከነበሩት ከአባታቸው ከነጋድራስ ኤባ አባ ያኢና ከእናታቸው ከወይዘሮ አሚና ሐሰን በ1920 ዓ.ም. ተወለዱ። "ኮንሶላታ" ከሚባለው የኢጣልያን አዳሪ ትምህርት ቤት በመግባት አቶ ይድነቃቸው ተሰማ፣ ከአቶ አባተ ጌታቸውና ከሌሎችም ጋር በመሆን በጊዜው አገራችን ውስጥ ይሰጥ የነበረውን መደበኛ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። የተወለዱበት ዘመን በአገራችን እንደዛሬው ዘመናዊ ትምህርት ያልተስፋፋበትና በተለይም ፋሺስት ኢጣሊያም ሀገራችንን የወረረበት ወቅት ነበረና ቀኛዝማች የከፍተኛ ትምህርት ዕድል አልገጠማቸውም። ሆኖም በኋላ ላይ በግል ጥረታቸው ባደረጉት ጥናት የእንግሊዝኛ፣ የኢጣልያንኛና የአረብኛ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው መናገርና መጻፍ በመቻላቸው ለጠቅላላ የንግድ ሥራቸውም ሆነ ለጉባኤ ወደ ተለያዩ አገሮች ሲሄዱ አስተርጓሚ አላስፈለጋቸውም።

በወጣትነት ዘመናቸው ማለትም በ16 ዓመታቸው ለ50 ዓመት በትዳር ጓደኝነት በፀና ትዳር አብረው የቆዩትን ወይዘሮ አሊያ ከሊፋን በሕግ አግብተው ሰባት ሴቶችና ስድስት ወንዶች ልጆችን አፍርተዋል። 13 የልጅ ልጆችም አይተዋል። ወይዘሮ ከሊፋን እንዳገቡ ይኖሩ የነበሩት እዚያው ከአባታቸው ቤት ስለነበረ በዚህ ወቅት የንግድ ሥራዎችን ለማጤንና ለመከታተል፣ እንዲሁም ከታላላቅ ነጋዴዎች ጋር ለመተዋወቅና የውጭ ሀገር ሸቀጥ ላኪዎች የሚልኩትን የሸቀጥ ዓይነቶች ጠንቅቀው ለማወቅ ጥሩ አጋጣሚ እንደሰጣቸው አብሮ አደግ ጓደኞቻቸው ይናገራሉ።

አባታቸው ነጋድራስ ኤባ አባያኢ በ1944 ዓ.ም. ማለትም የዛሬ 43 ዓመት ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ከድር ገና የ24 ዓመት ወጣት ሳሉ ነበር ወደ ንግዱ ዓለም በሚገባ የተሰማሩት። አባታቸው በሕይወት በነበሩበት ወቅት ቸርና ለጋስ ስለነበሩ ለልጃቸው ትተውላቸው የሄዱት ሀብት ጥቂት ነበር። ከድርም በጥቂት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ 1952 ዓ.ም. ድረስ

ቡና፣ ቆዳ፣ ሰም፣ የቅባት እህሎችና ጥራኝ ገዝተው ወደ ውጭ በመላክ አንቱ የተባሉ ነጋዴ ሊሆኑ ችለዋል።

የውጭ አገር ግንኙነታቸውን ለማጠናከር በማቀድ በባንክ በኩል ሲጻጻፉ ቆይተው በዚያን ጊዜ "ዩጎ ኢትዮጵያ" በኋላም "ዩጎ ኔክስ" የተባለው ኩባንያ ሥራቸውን ይከታተል ስለነበረ በያዙት ሥራ ላይ ለኩባንያው የሀገር ውስጥ ንግድ ሸቀጦችን እያዘጋጁ እንዲያቀርቡለትና የአንድ ክፍል ሃላፊም ሆነው እንዲሠሩለት ተስማማ። በዚህ አኳሃን ለአንድ ዓመት እንደሠሩ ይኸው ኩባንያ ሸቀጦችን የመላክ ሥራ ለመቀጠል ስላልፈለገና የክድርንም ፍላጎት ያውቅ ስለነበረ ኮንትራቱ ወደሳቸው እንዲተላለፍ ጠይቋቸው እርሳቸውም በደስታ ተቀብለው በሸቀጥ ላኪነት ሥራ ደፍረው ገቡ። የሸቀጥ ላኪነት ሥራውን በጀመሩ በስምንት ወር ውስጥ በውጭ አገር ያሉትን ወኪሎቻቸውን ለማየትና ለመተዋወቅ ወደ ኢጣልያ፣ ዩጎዝላቪያ፣ ጀርመን፣ ስዊድን፣ እንግሊዝና ፈረንሣይ አገር ሄደው በተለይም በቆዳና ሌጦ በኩል ስላለው ንግድ በሰፊው ተነጋግረውና ግንኙነታቸውን አጠናክረው ተመለሱ። በ1954 ዓ.ም. ፓሪስ ከተማ ላይ በተካሄደው የቆዳ ሥራ ኤክስፖዚሲዮን ላይ እንዲገኙ በወኪሎቻቸው ተጠይቀው ወደ አውሮፓ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሄዱ፣ እግረ መንገዳቸውን በመካከለኛ ምሥራቅ አገሮች በዮርዳኖስ፣ በሊባኖስ፣ በኢራቅ፣ በኩየትና በሶሪያ አልፈው ቡናና ቆዳ ንግድ ለመሥራት ስለሚቻልበት ሁኔታ ተነጋግረውና ውልም ፈርመው ተመለሱ።

የሀገራችን ቡና ጥራት ተጠብቆ በዓለም ገበያ ብቁ ተወዳዳሪ እንዲሆንና የሚያቀርቡት ቡና ከሌሎች መሰል ነጋዴዎች የተሻለ ጥራት ኖሮት የላቀ ተወዳዳሪ ለመሆን ባላቸው ብርቱ ፍላጎት፣ የቡና መልቀሚያ፣ ማበጠሪያ፣ ማጠቢያና ማድረቂያ ፋብሪካዎች እንዲሁም ቡናውን በቀጥታ ከምርቱ ቦታ ወደ ፋብሪካው የሚያመጡ በርካታ የጭነት መኪናዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባሉ። በፋብሪካዎች ውስጥ ከ1500 በላይ ሠራተኞችን በመቅጠር የሥራ ዕድል ይከፍታሉ።

ከ1956 ዓ.ም. ጀምሮ ኢትዮጵያ ከሚገኙ የአሜሪካን ንግድ ወኪሎች ጋር ግንኙነት መሥርተው ከቆዩ በኋላ በ1959 ዓ.ም. ወደ አሜሪካ ሄደው ከአሜሪካን ነጋዴዎች ጋር በመነጋገር በላኪዎች በኩል የሚሠራውን በእነርሱ አማካይነት፣ ከገዥዎች ጋር የሚሆነውንም በቀጥታ ከነርሱ ጋር የማከናወን ምርጫ እንዲኖራቸው በማድረግና ስምምነት ላይ በመድረስ ይመለሳሉ። አሜሪካ ሀገር ለሚገኘው ለ"ፍልጀርስ" ኩባንያ በብዛት ቡና ማቅረብም ይጀምራሉ።

ቀኛዝማች በተሠማሩበት የንግድ ዘርፍ ብዙ ፈተና ደርሶባቸው እንደነበረ ይነገራል። ብዛት ያላቸው ቡና ላኪ ነጋዴዎች መኖራቸው ቢታወቅም፣ እሳቸው የሚልኩት ቡና መጠን ግን ከሁሉም የበለጠ ሲሆን ውላቸውም ደግሞ ከብ□ራዊ ባንክ ጋር ነበር። በ1964 ዓ.ም. የአሜሪካን ዶላር ዋጋውን ይቀንሳል። ቀኛዝማችም ከብሔራዊ ባንክ ጋር በነበራቸው ውል መሠረት በዶላር 2.50 ብር ማግኘት ሲገባቸው 2.07 ብር ሂሣብ በመከፈላቸው 4 ሚሊዮን ብር ኪሣራ ደርሶባቸዋል። እንደዚሁም በ1970 ዓ.ም. ከብሔራዊ ባንክ ጋር በቡና ኤክስፖርት የ2 ሚሊዮን ብር ኮንትራት ከተፈራረሙ በኋላ በተነሣው ያለመግባባት የ2 ሚሊዮን ብር ኪሣራ ይደርሣል። ያም ሆኖ ቀኛዝማች ፈጽሞ ተስፋ ሳይቆርጡ ጥራት ያለው ቡናን ለፈረንሣይ፣ ለእንግሊዝ፣ ለጀርመን፣ ለስዊድን፣ ለጣልያን፣ ለዩጎዝላቪያና ለአሜሪካን በንግድ ወኪሎቻቸው አማካይነት ማቅረባቸውን ይቀጥላሉ። ወታደራዊ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ በ1971 ዓ.ም. ከቻይናና ከዩጎዝላቪያ ጋር ልዩ ገበያ ፈጥረው ነበር። በተለይም ዩጎዝላቪያ ከ10 ሺህ ቶን በላይ ቡና ለመግዛት ጨረታ አቅርቦ የዩጎዝላቪያ መንግሥት ግን ምንም እንኳን እሳቸው ከፍተኛ ዋጋ ቢጠይቁም ጥራት ያለው ቡና የሚያቀርቡ መሆናቸውን ቀደም ብሎ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በዚሁ መሠረት የተጠየቀውን ቡና እንዲያቀርቡ ከቀኛዝማች ጋር የልዩ ገበያ ውል ሊፈራረሙ ችለዋል። በዚህን ጊዜ ማለትም በ1971 ዓ.ም. የቡናና ሻይ ልማት ሚኒስቴር ተቋቁሞ ስለነበር በጊዜው ሚኒስትር የነበሩት በቀኛዝማች የቡና መላክ ንግድ ሥራ ውስጥ ጣልቃ በመግባት "ከድር ለዩጎዝላቪያ ማርኬት ለብቻው መሸጥ አይችልም፤" በማለት ትዕዛዝ ያስተላልፋል። ዩጎዝላቪያኖቹ ግን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚላከውን ትተው ከከድር መግዛታቸውን ቀጠሉ። በዚህም የደርግ ባለሥልጣናት የከፉ ዓይን ዒላማ መሆን ጀመሩ። ከድር ኤባ ከዚሁ በተጨማሪ ቡና በቻይና እንዲለመድ ማድረጋቸውንና በዚህም በአገራችንና በቻይና መካከል የላቀ የንግድ ግንኙነት እንዲፈጠር ትልቅ አስተዋጽዖ ማበርከታቸው በሰፊው ይነገርላቸዋል። ለአገራቸው ላበረከቱት ውለታም ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ከልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ እንደዚሁም በወቅቱ ከነበሩት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሮች የማበረታቻና የምስጋና ወረቀት ያገኙ ሲሆን በ1964 ዓ.ም. በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ የቀኛዝማችነት ማዕረግ አግኝተዋል።

በ1971 ዓ.ም. የወታደራዊ ደርግ ባለሥልጣኖች ሥራቸውንና ሀብታቸውን ለመዝረፍ ሲሉ ያለ እንዳች ጥፋትና ማስረጃ አስረዋቸው ከእስር ቤት እስር ቤት በማንከራተትና በማሰቃየት ሰባት ዓመት ሙሉ ስላጉላሉዋቸው በዚሁ ምክንያት ከሚወዱት የንግድ ሥራ እንደተለዩ ለዕልፈተ ሕይወት በቅትዋል።

በተያዙበት ዕለት በመጀመሪያ የተወሰዱት ድሮ አውሮፕላን ማረፊያ ከነበረው ሚሊተሪ ፖሊስ ሲሆን ከዚህ እስር ቤት ለስምንት ወሩ ከቆዩ በኋላ ከባድና አስፈሪ ጥበቃ ወደሚደረግበት ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር እስር ቤት ተዛወሩ። በዚያው ሰሞን ደርግ ለህልውናዬ ያሰጉኛል የሚላቸውን እንደነ ኃይሌ ፊዳና ሌሎችንም ከእስር ቤት እያወጣ ይረሽን ስለነበረ እስረኛው በሙሉ በፍርሃትና በጭንቀት ተውጦ የነበረበት ወቅት ነበር። በዚሁ እስር ቆይታቸው ለረጅም ጊዜ የታሰሩና ተስፋ ቆርጠው ብቸኛ የሆኑትን ቀርበው

በማነጋገር፣ ችግራቸውን በማቃለልና በማጽናናት፣ በብስጭት የተነሳ ትዕግሥት በማጣት እርስ በርስ ግጭት የሚፈጥሩትን የክፍላቸውን እስረኞች ከወጣት ዕድሜ እስከ አዛውንት ያሉትን ችግሩ እንዳይባባስ የሚያስታርቁና የሚያስማሙ ትልቅ መካሪ አባት እንደነበሩ አብረዋቸው ታስረው የነበሩ ይናገራሉ። ማንኛውም የቀረባቸው እስረኛ ችግሩን በመግለፅ የሚጠይቃቸውን ዕርዳታ በእሺታ ለቤተሰብ በመጻፍና የተጠየቁትን በማስመጣት ይረዱ እንደነበር የዓይን ምስክር ነን በማለት አብረዋአቸው ታስረው የነበሩና አሁን በሕይወት ያሉ ሁሉ በትዝታ ይናገሩታል። በተለይ በአንድ ክፍል አብረዋቸው ታስረው ከነበሩት እስረኞች ጠያቂ ዘመድ የሌላቸውን በቋሚነት የክርስቲያን ምግብ በማስመጣት የሚመግቧቸው ሲሆን ሌሎችንም ችግሮቻቸውን እንደሚያቃልሉላቸው የእስር ቤት ጓደኞቻቸው ይናገራሉ።

ጳጉሜ 4 ቀን 1973 ዓ.ም. ከ500 በላይ የሆኑ እስረኞች ምህረት ሲፈቱ ቀኛዝማች ከድር ኤባ ወደ ወህኒ ቤት እንዲዛወሩ ተደርገው ሁለት ዓመት የቆዩበት የ4ኛ ክፍለ ጦርም እስር ቤት ተዘግቶ ለሌላ ተግባር ዋለ። ቀኛዝማች ዕድሉ ሳይገጥማቸው ቀረና ወደ ወህኒ ቤት ተወስደው እዚያም አራት ዓመት ያህል ቆይተው በጠቅላላው ለሰባት ዓመታት በእስር ማቀቁ። እስር ቤት በነበሩበት ወቅት ሀብታቸውን ለመዝረፍና ጠቅላላ የንግድ ሥራቸውን በቁጥጥራቸው ስር ለማዋል በወቅቱ የነበሩት ሹማምንት ያላደረጉት ነገር የለም። ቀኛዝማች እንደተያዙ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለቡናና ሻይ ሚኒስትር "ሰውዬው (ቀኛዝማችን ማለታቸው ነው) በቁጥጥር ስር ስላሉ ድርጅቱንና ካምፓኒውን በሚመለከት ሀብቱን እስገምታችሁ ያለበትን የባንክ ዕዳ እንዲከፍል፣" የሚል ትዕዛዝ አስተላልፎ ነበር። በሚስቱና በልጆቹ ስም ገንዘብ ሊያሸሽ ነው በሚል የፈጠራ ወሬ ሰበብ በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመተውን ድርጅታቸውን፣ ሀብታቸውንና ንብረታቸውን የጊዜው ባለሥልጣኖች ወስደው ተጠቅመውብታል። ከእስር ቤትም ከሰባት ዓመት በኋላ ሲፈቱ ወደ ንግድ ሥራቸው እንዳይመለሱ ያደረጋቸውም ይኸው የንብረቶቻቸው መወሰድና አለመመለስ ምክንያት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ቀኛዝማች ከድር ኤባ በንግድ ሥራ ዘመናቸው ደርግ ለምን ይዞ እሳቸው የሚሰማቸውንና ለጓደኞቻቸው ከተናገሩት ይህን እንጠቅሳለን።

"የደርግ መንግሥት የቡናን ንግድ ለማዳከምና የግል ቡና ላኪ ነጋዴዎችን ለመጣል ባለው ዕቅድ መሠረት ከውጭ ዜጎች በወረሰው የቡና ድርጅት አማካይነት ከነጋዴዎች ጋር በመወዳደር የመላክ ሥራውን ይጀምራል። በዚሁ ጊዜ ይኸው መንግሥት የሾመው ነጋዴ ከቡናና የሻይ ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር በግል ጥቅም ለማግኘት ሲሞክር ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ቡና ከበፊቱ ቀነሰ። ይህም ሆኖ እኔና መሰል ነጋዴዎች በተሰጠን ኮታ መሠረት ለውጭ ደምበኞቻችን መላክ ቀጠልን። ይህ በእንዲህ እንዳለ የቡናና የሻይ ሚኒስትር የተባለው ግለሰብ በአገር ውስጥ ቡና አቅራቢ ነጋዴዎች ጋር መመሳጠር ሳያንሰው መንግሥት ቡና በሚልከው ድርጅት ወንድሙን በማስገባት እኔ ቡና ከምልክላቸው የምሥራቅ አውሮፓ ኩባንያዎች ጋር በምስጢር በመገናኘት እሱ ከሚያቀርብላችሁ ዋጋ በቅናሽ እንሸጥላችሁ በማለት ኩባንያዎቹን ሊያግባቡ ቢሞክሩም ከድር ኤባ የብዙ ዓመት ደምበኞችን ስለሆነ ችግር እስካልገጠመን ድረስ አሁንም ወደፊትም ከሱ ነው የምንገዛው በማለት መልስ ሰጡ። በዚህን ጊዜ ሚኒስትሩና ግብረአበሮቹ በአንዳንድ ንግድ ነክ ስብሰባዎች ላይ የእኔን ስም በማንሳት ውግዘትና ዛቻ ጀመሩ። ቀጥሎም አሜሪካን አገር ከሚገኙ ኩባንያ ደምበኞቼ ጋር በጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለቤት ወንድም አማካይነት ንግግር ለማድረግ ተሞክሮ ቀደም ሲል በሌሎች ኩባንያዎች የተሰጠው መልስ ተደገመ። ይኸው መልዕክት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ስላስቆጣ በአስቸኳይ እኔን የማጥፋትና ንብረቴን የመዝረፍ ዘመቻ ተጀመረ፤" ብለዋል።

ቀኛዝማች ከድር ኤባ በልጅነታቸው ስፖርትን ያፈቅሩ ስለነበረ በአራዳ በተለይም እርሳቸው ይኖሩበት በነበረው ጣልያን ሰፈር አካባቢ ከነበሩ ጓደኞቻቸው ከነአቶ ይድነቃቸው ተሰማ፣ ከነአቶ ቱፋ ሻይና ከሌሎችም ጋር የእግር ኳስ ቡድን በማቋቋም ይጫወቱ እንደነበረ በህይወት ያሉ ጓደኞቻቸው ይናገራሉ። ኋላም በስፖርት ቤተሰቦች ዘንድ በእጅጉ እንዲታወቁ ያደረጋቸው ለረዥም ጊዜ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን አባልና ፕሬዚዳንት እንደዚሁም ዋና ደጋፊና የቡድኑ የጥንት ተጫዋች መሆናቸው ነው። የስፖርት ቤተሰቦች እንደሚሉት ከሆነ የእርሳቸው እርዳታ ባይኖር ኖሮ የክለቡ ህልውና አጠያያቂ ይሆን እንደነበረ ይናገራሉ። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብስክሌት ፌዴሬሽንን በፕሬዚዳንትነት ለረጅም ጊዜ በመሩበት ወቅት በዕውቀታቸው፣ በገንዘባቸው፣ በሃሳብ ዋልታ በመሆን ፌዴሬሽኑ ከአቅሙ በላይ የሆነውን ወጪ እሳቸው በመሸፈን ለስፖርተኞች ብስክሌት፣ ጉማና የተለያዩ መለዋወጫዎችን በማቅረብ እንቅስቃሴው እንዳይተጓጎል ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጉ የነበሩ የስፖርት ሰውም ነበሩ።

ከተለያዩ የኦሎምፒክ ውድድሮች ላይ በድል አድራጊነት የሚመለሱ የሀገራችን ጀግና አትሌቶችን በመኖሪያ ቤታቸው በመጋበዝ የሞራል ማበረታቻ ልዩ ልዩ ሽልማቶች ይሰጡ እንደነበር እነሻምበል አበበ አበበ ቢቂላ፤ እነሻምበል ማሞ ወልዴ በዋቢነት የሚጠቀሱ ናቸው። በቅርቡም በስፔን ባርሴሎና ኦሎምፒክ በተደረገው የ10,000 ሜትር የሴቶች ሩጫ ውድድር አንደኛ ወጥታ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ ለሆነችው ለስፖርት ጀግናዋ ለሻለቃ ደራርቱ ቱሉም ከፍተኛ ግምት ያለው የወርቅ ሀብል መሸለማቸው ለአትሌቶቻችን ያላቸውን ከፍተኛ አክብሮት የሚገልጽ ሌላው ምስክር ነው።

ቀኛዝማች ከድር በአገራችን በወቅቱ ተቋቁመው የነበሩትን የተለያዩ በጐ አድራጐት ድርጅቶችን በገንዘባቸውና በጉልበታቸው ርዱ እንደነበረ በቤተሰቦቻቸው እጅ የሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚሁ በጎ አድራጎታቸው የወታደር ሚስቶች የበጎ አድራጐቶ ድርጅት፣ የአካለ ስንኩላን መጠሪያ የበጐ አድራጐት ድርጅት፣ የቀይ መስቀል ማህበር፣ የኢትዮጵያ መጽ ፍ ቅዱስማህበርና የመሳሰሉት የጻፉላቸውን የምስጋና ደብዳቤዎች ተመልክተናል።

ዛሬ ቀኛዝማች ከድርንና መሰሎቻቸውን የምናስታውስበት ታሪካቸውንም ዘግበን የም[illegible]ላይ ከገለጽነው በተጨማሪ ሌላ ምክንያት ይኖረናል። በጐሳና በሃይማኖት ያልተከፋፈለችውን [illegible]ራችንን ለመገንባት፣ ብሎም በውጪው ዓለም ለማስተዋወቅ እንደ ቀኛዝማች ከድር ኡባ ያሉትን ታዋቂ አባቶች ያደረጉት ጥረት ለኛም ትምህርት እንዲሆነን በማሰብ ነው። ከሳቸው ብዙ ትምህርትን እንቀስማለን። ታታሪነትን፣ ጠንካራ ዓላማን ከግብ ለማድረስ ተስፋ አለመቁረጥን፣ ወገንን ለመርዳት ዝግጁ መሆንን፣ ጤናማ ህበረተሰብ ለመፍጠር ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግን፣ ቤተሰብን መውደድንና የመሳሰሉትን ነው። አባቶቻችን ዘር፣ ሃይማኖትና ወገን ሳይለዩ በፍቅር ተከባብረው፣ ተባብረውና ተዋደው ይኖሩ እንደነበረና በዚህም አገርንና ወገንን እንዲሁም ራስን ለማሳደግ ያደርጉ የነበሩትን ጥረት ይህ አጭር ዘገባ ያሳየናል።


ላንዳፍታ

ኢትዮጵያዊ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት በአማርኛ
በየሁለት ወሩ የምትታተም

በሥራም ቦታ ሆነ በዕረፍት ጊዜ እንዲያው ላንዳፍታ ቁጭ ብንል እንድታሳውቀንና እንድታዝናናን የተዘጋጀች ናት። በአራት ዓመት ተኩል ልምድ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ደምበኝነት አፍርታለች።
እርሶም ደምበኛ እንዲሆኑ ትጋብዝዎታለች።

Name ______________________

Address ______________________

City ______________________

St ________ Zip ______________

Single Copy - $2.75 ($3.00 Canada)
Subscription Rates:
Six Issues - $16.00 U.S.
Canada: $22, Europe: $30.00 ,Asia: $38.00, Institutions: $40.00

አምዶቻችን

"ዜናዎች"
"እናስተዋውቃችሁ"
"ኑሮ በአሜሪካ"
"የአሜሪካ ኑሮ ገጠመኞች"
አዳምና ሔዋን
"ልብ ወለድ"
"ስፖርት"
"የግጥም ጉባኤ"
"ለሳቅ ለፈገግታ"
"የስንጠረዥ ጨዋታዎች"

ላንዳፍታ
ታስተዋውቃለች!
ታስተምራለች!
ታሳውቃለች!
ታዝናናለች!
ታስቃለች!
ታጽናናለች!

Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone: (404)728-9122
E-Mail - mgessesse@aol.com

# ኑሮ በአሜሪካ

በአሜሪካ ኑሮአችሁ ምን ገጠማችሁ? ኑሮን ለማሟዋቸት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ባሉ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ላይ ለመወያየት ይህ አምድ አስተዋጽዖ ያደርጋል የሚል እምነት አለን። በውይይት የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል የሚል እምነት አለን። በተጨማሪም በዚህ አገር ኑሮአችን ተሰባስበን በጋራ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማስተዋወቅም ትልቅ አስተዋጽዖ ያደርጋል እንላለን። አንዱ ከሌላው ልምድ ሊማር ይችላልና። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠሙኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩት መሆኑ ይታወቅልን።

## ከ ኢ ም ን ት ማ ሀ ደ ር

ከአንዋር አህመድ

የሰው ልጅ ይወለዳል፣ ለአቅመአዳም ይደርሳል፣ ያረጃል፣ ይሞታል። የህይወት መዋቅሩን ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ለሚያየው ቀላል ይመስላል። ነገር ግን በውስጡ ያዘላቸው ውጣ ውረዶች፣ የሀዘን፣ የደስታ፣ የችግር፣ የጭንቀት የእነዚህ ሁሉ ክስተቶች መኖር አንጎል ከሚያስበው በላይ እንዲሆን ያደርገዋል። እስኪ የአለም አስተዳዳሪ ተብሎ በሚጠራው በታላቁ አሜሪካና በአለም የደረጃ ሚዛን ላይ ቦታ ላልተሰጣት ከባህር ማዶ ኢትዮጵያችን ብለን ስለምንጠራት አገር መካከል ያለውን ልዩነት እንቃኝ። አሜሪካ በሀብት፣ በቴክኖሎጂ፣ በሰው ብዛት፣ በንጣት፣ በጥቁረት፣ በማን አለብኝነት በአለሁ ባይነት ሲታወቅ እናት አገራችን ደግሞ በጥሩ ባህል፣ በደግነት፣ በተፈጥሮ አቀማመጥ፣ በጥሩ አሳቢነት፣ በጎረቤት ተቀባይነት፣ በሆደ ባሻነት፣ በጀግንነትና በታሪክ ጀማሪነት ትታወቃለች። ባህል! ባህል ስንል ምን ማለታችን ይሆን? ባህል የአንድ አገር ልዩ ምልክቷ ውበቷና ማንነቷን ማሳያ መስታወቱ ነው ብንል በአጭሩ ለማስቀመጥ ያህል በቂ ይሆናል።

እንግዲህ ኢትዮጵያ ደግሞ ከላይ ለተዘረዘሩት ነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ነች ብንል ከዕውነት የራቀ ሀቅ አይሆንም። በእጅ ያለ ወርቅ እንደመዳብ ይቆጠራል ይላል የአገሬ ሰው። ያለንን ዕፁብ ባህል ሳናስበው በደማችን ውስጥ የኖረውን ከዕርስ በርስ መተሳሰብ አልፎም ለባዕድ ማሰብ ከምንም ሳንቆጥረው ምናልባትም ስናንቋሽሸው ኖረናል። በየጊዜው በሚፈጠሩ የፖለቲካ ጅቦች ሳንፈልግ በግድ ከሞቀ ቤታችን እየተፈናቀልን ባህር ተሻገርን እንጂ ጥሩ አስተዳደርና ሰላማዊ ጊዜ ቢኖረን ኖሮ ለአገር ልማት ዕድገት ስንል እዛው በቀረን ነበር። ነገር ግን በሌላ በኩል ደግሞ ባህር ባንሻገር ኖሮ የእናት አገራችንን ጠቃሚነት ሳናውቀው እንቀር ነበር። ለነገሩ የተራራ ውበቱ የሚታወቀው ከሩቅ ነው ይባል የለ። አጋጣሚ ሆኖ የብዙዎቻችን መጠለያ አሜሪካ ሆነና ዕድሉን አግኝተን መተን ያየነው እያደነቅነውም፣ እያንቋሸሽነውም ሚዛን ላይ ማስቀመጥ ከጀመርን ቆየት ስንል በአይን ያላዩት ደግሞ አሜሪካ ወይንም ሞት ብለው ዕድሉ ለእነሱም የሚያካፋበትን ጊዜ በጉጉት ይጠብቃሉ። ለነገሩ ያላዩት አገር አይናፍቅም ይባል ነበር። ለእኛ ለሶስተኛው አለም ሰዎች ግን አሜሪካ ሲናፍቀን ኖሮዋል፤ እየናፈቀንም ነው።

እስኪ እናት አገራችንና ህዝባችን ካላቸውና ከረሳናቸው እፁብ ድንቅ ከሆኑ ትንሽ መስለው ከሚታዩ ባህሎች አንዳንዶቹን ለማስታወስ ያህል እንግለፅ:-

ከአገሬ ከወጣሁ በኋላ ካስገረሙኝ አንዱ የአገር ቤት ትዝታ ውስጥ ጠዋት ከቤቴ ወጥቼ መንገድ እንደጀመርኩ በጊዜው ወዛደር እያልን ከምንጠራው አንድ ወጣት መቶ ኪሎ ጤፍ ከመሬት ላይ ማንሳት አቅቶት ሲቸገር ጠጋ ብዬ ለማሸከም ስሞክር ሌሎችም በመንገድ የሚያልፉ ሰዎች ሲተባበሩኝና አሸክመነው ወደስራው ሲያመራ በወቅቱ ማድረግ ያለብን በህግ የተደነገገ ነገር ቢመስለንም አሁን አሁን እርቄ ሳስበው ግን መተሳሰባችን ተፈጥሮ የሰጠን ደግነት፣ ጥሩው ባህላችን መሆኑን አወኩት። አሜሪካኖቹ እንደሚሉት That is your problem አንልም። መጥፎ ጊዜ መጥቶ ሰው እየተቸገረና የሚበላው እያጣ ሳይወድ በግዱ ወደ መጥፎ መንገድ ሲያመራ ቢታይ የሚፈረድበት ወይንም ባህሉን ያጣ ሊያደርገው አይገባም። ለሁሉም ነገር ገደብ አለውና።

ሆድ ጥይት እንደሚያማዝዝ እዚህም ሰልጥነናል በሚሉት አገር ላይ በየቀኑ የሚታይ ለመሆኑ መዘንጋት አይገባም። ሌላው ደግሞ ከዛው ተለይቶ የማይታየውና ትዝታ ከሚፈጥሩ ነገሮች መካከል።

መኪናው የተበላሸ ሰው መንገድ ስንሄድ ቢያጋጥመን ብናውቀውም ባናውቀውም ጭቃ ይሁን ዝናብ የዕርዳታ እጃችንን ዘርግተን መኪናውን መግፋታችን አይቀርም። ይህም አኩሪው ባህላችን የለገሰን እንጂ የህግ ጉዳይ ሆኖ አይደለም።

እዚህ አገርማ በትልቁ ጎዳናቸው ላይ በሌሊት መኪና ተበላሽቶ ያለዕርዳታ በፍርሃት ከመቆየት ባሻገር ዕርዳታ ቢገኝም ወይ ይሞታል ወይ ደግሞ ለዘረፋ ይማገዳል። ይህንን ሁሉ ስዘረዝር አሜሪካ በደፈናው መጥፎ ነው ለማለት ሳይሆን በውስጡ እየቆየን ስንመጣ ውዱ ባህላችንን እያስጣለን ሰው ሰራሽ በሆነ አርተፊሻል ኑሮ እያለበሰ አገራችንን ባህላችንና፣ ማንነታችንን ሊያስረሳን ስለተቃረበ ነው።

በእርግጥም እንደልባችን ወጥተን ከአንድም ሁለት ስራ ሰርተን ሆዳችንን ሞልተን ቤቴ ብለን መግባታችን ቀላል አይደለም። ትንሽም ቢሆን በየወሩ ሳንቲም እየላክን ቤተሰቦቻችንን የምንረዳበት ስራ ስላለንም ተመስገን እንላለን።

እንግዲህ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የአገሬ ሰው እንደሚለው እግዜር ያክብርልን እንላለን። አውቶቢስ ውስጥ ቁጭ ብለን በዕድሜ ከፍ ላለ ሰው መነሳታችን፣ ኖር ማለታችን ሁሉ ክቡር ባህላችን የለገሰን የተፈጥሮ ፀጋ ነው። ከዚህ ሁሉ አልፈን ሰው በሁለት እጅ መጨበጣችን፣ ከአንገት ጎንበስ ብለን ሰላምታ መስጠታችን፣ ስንገናኝ መሳሳማችን ሁሉ በቀላሉ ሊገኝ የማይችል ገፀበረከት ነው። ሌላው ቢቀር እጃችን ውሃ ከነካ ወይንም ከቆሸሸ እጃችንን አጥፈን መጨበጣችን ሁሉ ለሰው ያለን አክብሮት ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

እስኪ የእነዚህን ከላይ የተጠቀስኩትን ነገሮች ጠቀሜታ ለማወቅ ስላለንበት አገር ህዝብ አኗኗርና በእኛ በውጭ ዜጎች ላይ ያላቸውን አመለካከት እንቃኝ።

መቼም እንግዲህ ጭቃ አቡክተን ኳስ ተጫውተን፣ ብይና ጠጠር ወርውረን፣ ካሬ ብለን ካደግንበት ሰፈር አንስቶ በሰፈር ውስጥ ከሚወርደው አስፋልቱን ከሸረሸረው የቆሻሻ ውሃ ድረስ ሁሉም ራሱን የቻለ የትዝታ ማህደር አለው።

እንግዲህ በየፅሁፌ መሀል በተደጋጋሚ ለመግለፅ የምፈልገው ፅሑፉ ለመጠቆም የሚሞክረው የአሜሪካንን ደካማ ጎን በጀርባው ያዘላቸውን የአደባባይ ሚስጥሮቹን እንዲሁም እውነታዊ ገፅታውን እንጂ ማንኛውንም ሰው የመምጣት ዕድሉን ከማግኘት ለማራቅ ወይንም ዕውቀቱን ለመዝጋት አይደለም። ደግሞም አሁን ባለንበት ዘመን የሰው መኪና ተደግፈው ፎቶ እየተነሱ ሀገር ቤት መላክ የቀረበት ጊዜ ይመስለኛልና ሁሉንም ነገር ፍንትው አድርገን ብናየው ለጉዳት አይሰጥም። ለነገሩ ታላቁ አሜሪካም በውሸት ባንዲራ ስለቀለመ የጨለመ ግርዶሹን ከፍቶ እውነቱን ማሳወቅ ለህሊና ቅድመ ዝግጅት ይሰጣል ብዬ አምናለሁ።

በሬውና በጉ ይረባል፣ ይታረዳል፣ ለተጠቃሚው ይቀርባል። ስለስጋ ስናወራ፣ አንድ ከኢትዮጵያ ልጃቸውን ሊጠይቁ የመጡ እናት የገጠማቸውን ትንሽ እንቃኝ። ልጃቸው ካስመጣቸው ከጥቂት ወራት በኋላ እንደማንኛውም አሜሪካ እንደሚኖር ኢትዮጵያዊ በስራ በመጠመዱ ቀን ቀን እቤት እየጣላቸው ይሄድ ጀመር። የልጃቸው መድከምና ብቸኝነት ያሳዘናቸው እናትም አንድ ቀን ልጃቸው ከስራ ሲመጣ ሊያስደስቱት አስበው ከግሮሰሪ ስጋና ለወጥ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ገዝተው ይመጣሉ። ስጋውን አገላብጠው ሲያዩት እላዩ ላይ ያለው ወረቀት መስከረም አስራ አምስት ይላል። በነገሩ ግራ የተጋቡ እናት ቀን መቁጠሪያቸውን ቀጥ ብሎ ቢያዩ የነበሩበት ቀን መስከረም ሰባት ይላል።

ነገሩ ለጊዜው ግራ ቢያጋባቸውም ልጄ ሲመጣ እጠይቀዋለሁ ብለው ስራቸውን ቀጠሉ የሚያስገርማቸው ነገር እየተደራረበ መጣ ለወጥ ከገዙት ከትንሹ ቅመም አንስቶ እስከ ስጋው ድረስ ሁሉም ቀንና አመተ ምህረት አለው። በተለይም ወተቱ ይበልጡኑ ግራ አጋባቸው ልጃቸው ማምሻውን ከስራ ሲገባ ጠይቀውት ሁሉም ነገር የማለቂያ ወይንም የመበላሺያ ቀን እንዳለውና ከዛ ቀን በኋላ ለሚደርሰው ጉዳት መስሪያ ቤቱ ወይንም ፋብሪካው ሃላፊ እይደለንምማለቱ ነው አላቸው። እላቸውም ወይ ጉድ ልጄ የአገራችን ላሞች ለሚታለቡት ወተት ቀን ቢሰጡ ኖሮ ምን እንሆን ነበር ብለው ፈገግ አሉ። እውነትም ሳስበው የምንበላውና የምንጠጣው ነገር በሙሉ ጤናማ እንደሆነ ዶሮ በሶስት ቀን የሚያድግበት አገር ከመጣሁ በኋላ ነው ያወኩት።

በቅርቡ አንድ የእንግሊዝ ሳይንቲስት ተመራምሮ ለልብ ደህና እንደሆነ ስለደረሰበት ዛሬ ይህንን ብሉ ሲሉን ከሳምንት በኋላ ደግሞ በቀደም የነገርናችሁ የምግብ ዓይነት በቅርብ ጊዜ የአውስትሪያው ሳይንቲስት ለጭንቅላት መጥፎ እንደሆነ ተመራምሮ ደርሶበታል ይሉናል። እኛስ መቼም እድሜውን ሙሉ ቃሪያና በርበሬ ሲበላ የኖረ ሰውነታችን አጋልጦ ይሰጠናል ብለን ባንፈራም ግራ የገባን እዚህ አገር የምንወልዳቸው ልጆቻችን ለልብ መጥፎ ነው ከሚባለው ከምግብ መብላቱ አንስቶ እስከ አሰቃቂና ጎጂው የአሜሪካ ባህል ድረስ በደረቅ መርፌ እየተወጉት መሆናቸው ነው።

ጥቁር አሜሪካኖች የመጡበትን የዘር ግንድ ለማግኘት አፍሪካ ድረስ ሲጓዙ እኛ የባህልና የዘር ሀብታችን በቀላሉ ስንሸጠው እንታያለን። "Before they were we were" ያሉት ማንንም አይደለም። እኛኑ ነው የሰው ልጅ ጅምሩ ነንና።

# ነግ በእኔ

ከዮሐንስ ገብረሕይወት ገብረ ሚካኤል)

ከውዷና ከለምለሟ አገራችን አስራሁለት ሺህ ማይልስ ርቀንና አህጉራት፣ ባህርና ውቅያኖስ አቋርጠን መጥተን በዚህ በሰለጠነው ዓለም አሜሪካ አገር ውስጥ እንገኛለን። ምንም እንኳ የአገሩ ሁኔታና የሥራው ጠባይ እንደሀገራችን ዕለት በዕለት ለመገናኘትና ለመጨዋወት ባይመቸንም አልፎ አልፎ በምናገኘው ነፃ ጊዜ በመጠቀም ሰላማዊና ቤተሰባዊ ውይይት በማድረግ ስለአገራችንና ስለቤተሰባችን እንዲሁም ሁለተኛው አገራችን ስለሆነው አሜሪካን ሁኔታ በበጎና በእድገት ጎዳና አንፃር መነጋገር አስፈላጊ ሆኖ ሳለ እንደአይጥና ድመት በመተያየት እርስ በእርስ በመናከስ እድሜአችንን በከንቱ በመጨረስ ላይ ነን።

የሐበሻው ሕብረት እንደሆነ ሬሣ በመላክ ላይ የተመሰረተ ነው ሲል አንድ በጣም የምወደውና የማከብረው የጥንት ጓደኛዬ (ወንድሜ) ከአገር ቤት ስልክ ደውሎ ነገረኝና አንድ ዓመት ሙሉ በዚህ አነጋገርና ቃላት ስስቅበት አለሁ እላችኋለሁ።

እኔም አላረፍኩ ምን ማለትህ ነው ብዬ በቁጣ ጥብቅናዬን ላለሁበት ምድርና ሕዝብ ጀመርኩ ቀጥሎም ጓዴ የማንሰማ መሰላችሁ ሰው ሲሞት ብቻ ገንዘብ ለማዋጣትና ከንፈር ለመምጠጥ ብቻ የተሰለፈ ሩህሩህ ሕዝብ ነው ብሎ ሳላስበውና ሳልጠብቀው አንዴ በኃይለ ቃል ጮኸብኝ። ነገሩ ከሩቁ በስልክ ብቻ ሆነ እንጂ አጠገቤ በገጽታ ቢሆን ኖሮና ፊቱን እያየሁት ቢቆጣኝ ኖሮ እኔም ባለቀቅሁት ነበር። ድሮም ያውቀኛል ብቻ ምን ያደርገኛል ብሎ ይሆን? ለማንኛውም ሐሳቡ ጥሩ ሆኖ ሳለ ይህ ሁሉ ቁጣና ጩኸት ለምንድን ነው ብዬ በእርጋታ ብጠይቀው እባክህን ተወኝ እኛስ በእቁቡም፣ በእድሩም፣ በማህበሩም፣ በመሥሪያ ቤቱም በየቤተክርስቲያኑም ወዘተ ፍቅራችንና ህብረታችን ያለ ነው።

ምንም እንኳ ትንሽ የዘር ልዩነት ቢኖርም ሰው እያደረ ጉዳዩን እየተረዳ የተዋለደ ሕዝብም መሆኑን እያጤነ ወደድሮው ልቡና ፍቅሩ እየተመለሰ ነው። ይብላኝ ለእናንተ ብሎ ቀዝቀዝ ባለስሜት አረጋገኝና ሁለታችንም አለ አይደል በጥንቱ ፍቅራችን በመባባል ስለድሮው ጉዳይ ስለሰራናት በመነጋገር ሳቃችንን አቀለጥነው። ወዲያው ያ ሁሉ ቁጣና ብስጭት ፈረሰና የጥንቷ የጥዋቷ መጣች በቀላሉ ተንፈቀፈቅን እላችኋለሁ። በመጨረሻም አጅሬ አስቡበት ብሎና ሰላምታዬን ተቀብሎ እኔም ሰላምታውን ተቀብዬ በሰላምና በድሮው ፍቅራችን ተሳብለንና ተስማምተን ቻው ቻው በመባባል በዕለቱ ተለያየን። ታዲያ እኔም ስልኩን ከዘጋሁ በኋላ ነገሩን ሳጤነው ለካስ እንዚህ ሰዎች ይታዘቡናልና ይገርማል ጉድ ነውና አልኩ።

እዚህ አሜሪካ የተወራችውም ሆነ የተፈሳችውም አንዲትም ሳትቀር (ያለው ጠቅላላ ሚስጥር ሁሉ) አገር ቤት ነው የሚቀመጠው ለማለት ቻልኩና ገረመኝ። በተለይ በሞት ጊዜ ነው የምትረዳዱት ያለኝ ነገር ልቤን በላው። እውነትም ጓዴ እንዳለው የዛሬ ዓመት አንድ ወንድም በደረሰበት ሕመም ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ሳለ ገንዘብ በዕርዳታ ሲሰበሰብ በተፃፈው ጽሑፍ ላይ ነግ በእኔ እንዳይሆን የሚል ከባድ ቃል ነበረበትና ይህ ቃል በአንድ ጊዜ በዓይነህሊናዬ ብቅ አለ። ለካስ ጎደኛዬ የተናገረው እውነቱን ነው አልኩ። እኔን ያሳዘነኝ እንደዛ እንዳልተግባባን እንዲህ በቁጣ ልቤን ማጥፋቱ ነው እንጂ ነገሩስ እውነት ነው። በመጨረሻ እኔም የጓዴን አባባል አመምንበትና እዚህ ያለው ወገኔን ቀደም ብሎ በመግባባትና በመቀራረብ መንፈስ ነግ በእኔ ከመምጣቱ በፊት ሰላማዊ ህብረቱን ቢያጠናክር ጥሩ ነበር በማለት ለራሴ ተናገርኩ። ለካስ በአጠገቤ ማንም አልነበረም። ለነገሩ ጉዳዩ ትኩረት የሚሰጠው ነውና የሚመለከታችሁ የኮሚኒቲ መሪዎችና ሐበሻው በሙሉ ቀድሞ በመተባበርና ለእድገት አብሮ በመሥራት መጠንቀቅ እንዳለበት የተሰማኝ የአገር ቤቱ ጎደኛዬ የጥንቱ ከጮኸብኝና ካስደነገጠኝ በኋላ ነበር።

ለማንኛውም ነግ በእኔ ከመደጋገሙ በፊት ቀድመን በሁሉም መስክ ራሳችንን እናጠናክር።

# ፍቅርና ጋብቻ በአሜሪካ

## ክፍል ሁለት

ከዮሐንስ ገብረሀይወት ገብረሚካኤል

ውድ አንባቢያን እንደምን ከረማችሁ? የብርዱስ ነገር እንዴት ያደርጋችኋል? የፍቅርስ? የጋብቻውስ ጉዳይ" እኔ ደህና ነኝ።

ያለፈውን ጽሑፌን አንብባችሁት ከሆነ ስለጋብቻ ዓይነቶች፣ በትዳር ውስጥ ስለሚያጋጥመው ችግሮችና ፍቺዎች፣ በዚህም ምክንያት በልጆች ላይ የሚደርሰውን መጉላላት በመግለጽ ለወደፊቱ አሁን ባለው የኑሮ ሕይወት (Life Style) ፍቅርና ጋብቻ በአሜሪካን አገር ውስጥ እንዴት ቢሆን ይሻላል? በሚል ሃሳብ ላይ አነስተኛ የሆነ ጽሑፌን ለማቅረብ ሞክሬ ነበር።

አሁን ደግሞ በክፍል ሁለት ላይ ፍቅር ምንድነው? ጋብቻስ በአሜሪካን አገር እንዴት ቢከናወን ይሻላል? ንፁህ ፍቅር ያለበት ጋብቻስ እንዴት መመስረት ይቻላል? ለጋብቻስ መፍረስ የሚሆኑት ምክንያት ምንድን ናቸው? እንዴትስ ይህንን አላስፈላጊ የሆነ ፍቺ መከላከል ይቻላል? በሚል ሐሳብ ላይ በመመርኮዝ በመጠኑ ለመጣጣፍ እሞክራለሁ።

መቸም ስለፍቅር ጉዳይ ሲነሳ ሁላችንም ደስ ይለናል። ምክንያቱም ያለፍንበትና ወደፊትም ሊያጋጥመን ስለሚችል ማንበቡም ማወቁም አስፈላጊና ስሜትም ሰጪ ነውና።

በዚህም ምክንያት ስለፍቅር ብዙ ተጽፏል። ወደፊትም ይፃፋል። መቆሚያም የለውም ጉዳዩ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ ከሰው ልጅ መፈጠር ጀምሮ አብሮ የመጣ ከተፈጥሮ ሕግጋት ጋር የተሳሰረ፣ ከስሜት ሕዋሳት ጋር አብሮ የተዋሃደና በጎሃድ የሚገለጽ የሚጣፍጥ፣ የሚያስደስት ሕይወት ስለሆነ ሁላችንም ፍቅርን እንወዳለን።

ይህን ስል ብዙ ዓይነት ፍቅር አለ። የአገር ፍቅር፣ የቤተሰብ ፍቅር፣ የስፖርት ፍቅር፣ የሙዚቃ ፍቅር፣ የትምህርት ፍቅር፣ የማንበብ ፍቅር፣ ሲኒማ የመመልከት ፍቅር፣ ቲያትር የማየት ፍቅር፣ የጓደኛ (የተመሳሳይ ፆታ)ና የእንስሳት ፍቅር . . . ወዘተ አለ።

እንግዲህ እኔን ትንሽ ለመፃፍ ያነሳሳኝ ሁላችንም ስለሚያንገበግበንና ስለምንወደው የተለያየ ፆታ (የወንድና ሴት) ፍቅር ሲሆን በዚህም ምክንያት ስለሚፈጠረው የጋብቻ ሁኔታ የሚያካትት ይሆናል።

ይህ ደግሞ የህይወት ኡደት (LIFE CYCLE) በጊዜአቸው ያልፉበታል። ወደፊትም ይቀጥላል። መቆሚያም የለው። በተለያየ ዕድሜ የተለያየ ገጽታና ባሕርይ ያለውና ሁሉንም የሰው ዘር በእኩልነት የሚያስደስተው። ይህ ሲባል በሕፃንነት በታዳጊነት፣ በወጣትነት (በጎረምሳነት) በጎልማሳነት ከዚያም በስተእርጅና ጊዜ ፍቅር አለ ምንም እንኳን ሁኔታውና አደራረጉ ይለያይ እንጂ ከላይ እንደጠቀስኩት ጉዳዩ ዞሮ ዞሮ ፍቅር ነው።

እንግዲህ ወደፍሬ ሃሳቡ ከሆነ በሁለት ከፍየዋለሁ። አንደኛው ዓይነት ፍቅር በጎና ሰላማዊ ሌላው ደግሞ ሁከትና ችግር የበዛበት ዓይነት ፍቅር ነው።

በዚህም መሰረት የመጀመሪያው ዓይነት (ሰላማዊው) የፍቅር ዓይነት ንፁህ ሲሆን ይህ ዓይነቱ ፍቅር በሥነሥርዓቱ የሚጀመርና የሚካሄድ ዓላማ ያለው ሲሆን በወንዱና በሴቲቱ አስተዳደግ የቤተሰብ ባህርይና ባህል ላይ የተመሰረተ ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የተጀመረ ፍቅር ቋሚና ዘለቄታ ያለው ንፁህነትና ታማኝነት ያለበት እጅግ ደስታን የሚሰጥና ዘለዓለማዊ ክብርን የሚያጎናጽፍ ቋሚ ገፀ በረከት ነው።

ሁለተኛው ዓይነት ፍቅር ደግሞ በጥቅምና በጊዜያዊ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ከመሆኑም በላይ ሁከት የበዛበት በተቃራኒውም ሰላምና እምነት የሌለበት በመሆኑ ዘላቂነት የሌለው ነው። በዚህ ምክንያትና ሁኔታ የተፈጠሩ ጋብቻዎች ፈራሽ ስለሚሆኑ ለተወለዱት ሕፃናት ጠንቅና ጎጂ በመሆን ልጆች በሥርዓት እንዳያድጉ፣ እንዳይማሩና ለአገራቸው ብቁ ዜጋ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል።

ታዲያ በዚህ ዓይነት ማንኛውም አፍቃሪ ከሁለቱ የፍቅር ዓይነቶች የቱን ትመርጣለህ? ቢባል የመጀመሪያውን እንደሚል ሳይታለም የተፈታ ነው።

ይህንንም ትክክለኛ እምነት ያለበትን ጣፋጭ ፍቅር እንዴት ማግኘት ይቻላል? ይህንንስ ካገኙ በኋላ እንዴት ቋሚና ዘላቂ ማድረግ ይቻላል።

እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ፍቅር በመጀመሪያው የሚይዘው በማየት (sight love) ሲሆን ይህም ሴቲቱን (ወንዱን) ስንመለከት ከእሱ ወይንም ከእሷ የምንወደውን ነገር እንመለከታለን ወይም እያንዳንዱ ሰው የሚወደው የተለየ ነገር አለው ለዚያም ይማረካል።

ከዚያም ውስጥ ዓይን፣ ፀጉር፣ ጥርስ፣ ከንፈር፣ ጡት፣ ወገብ፣ የእግር ቅርጽ፣ አካሄድ፣ አነጋገር፣ ቁመት፣ ቁመና፣ . . . ብቻ ምንልበላችሁ አንድ ነገር ዓይተን ልባችን ሁለት ቦታ ሲከፈል ዓይናችን ደግሞ ትክ ብሎ ማየት አቅቶን ስብር ይላል ወይም አይናችን ትክል (ቅዝዝ) ብለን እንቀራለን። በዚህ ጊዜ ሕሊናችን መቅበጥበጥ ይጀምራል። በተቃራኒው ፆታ ይህ ጉዳይ በተፈፀመና በአንተ ላይ የተከሰተው ስሜት በሷ ላይ ከተፈፀመ ጉዳዩ ሸጋ ይሆናል። (በአራዳ ቋንቋ ቡሽ ገጥሟል) ብለን እንጠራለን። ከዚህ በኋላ ለመግባባት ቀላል ስለሚሆን በቶሎ እንቅስቃሴ ይጀመራል። እቤት ደስ ሲል ምን ልበላችሁ ሁላችሁም ጉዳዩዋን ስለምታውቋት በቀላሉ እንግባባለን ወዲያውም ተቃራኒውን ፆታ ለማነጋገር ሲባል ብቻ ምክንያት እንፈጥራለን በእጃችን ላይ አሚጋ ሰዓት አስረን ሳለን ሰዓቱን ደቃቂውንና ሴኮንዱን ሳይቀር

በትክክል ሊነግረን ሲችል ለማነጋገር (ለለከፋ) ብቻ ሲባል በኮራ እንደበት እህት(ወንድም) ሰዓት ስንት ነው እንላለን፤ እዚህ አሜሪካን አገር ደግሞ ስለአለቱ አየር ሁኔታና ጠባይ በመናገር (በመጠየቅ) ወይም የምንሄድበትን አድራሻ እያወቅን እንደማያውቅ በመምሰል አድራሻ እንጠይቃለን።

ከዚያም ሁለተኛውና የሚቀጥለው ሁኔታ ደፈር ብለንና ትንፋሽ ወደውስጥ ዋጥ በማድረግ ንግግር ጀምረን የማውቅሽ መሰለኝ እንላለን። ብናውቃትም ባናውቃትም ሴቲቱም እንደዚሁ በዚህ ዓይነት ነው ለመግባባትና ለመተዋወቅ የሚሞከረው አገር ቤትም ሆነ እዚህ አሜሪካን ሌሎችም ብዙ ብዙ የመግባቢያ መንገዶች አሉ። እንደው ለምሳሌ ያህል ጠቀስኩት እንጂ ይህንን ሁሉ አታውቁትም ብዬ ሳይሆን ይህ በመጀመሪያ ከማየት የሚመጣው የፍቅር ዓይነት እጅግ ኃይል ያለው መሆኑን ለማሳየትና እንዴት ለትውውቅ እንደሚጋብዝም ለማስረዳት ነው።

እኔ ስለዚህ ጉዳይ ማወቅ የጀመርኩት ገና በልጅነቴ ነበር እስቲ የዓይን ፍቅርን በተመለከተ አንድ ያጋጠመኝን ነገር ከአገር ቤት ላጫውታችሁ። ዘመኑ ትንሽ ራቅ ያለ ነው በጊዜው አንድ ከእኔ በእድሜ የሚበልጠኝ አብሮ አደጌ ማለትም በወቅቱ ለፍቅር የደረሰ አንዲትን ልጅ ወዶ ኖሯል፤ አደገኛም በሆነ (Sight Love) የዓይን ፍቅር ተመቶ ነበርና አንድ ቀን አብረን ስናጠና ልጅቷን ከሩቅ ይመለከታታል። ለነገሩ ለእኔ አልታየኝም። እሱ ግን በጣም ይወዳት ነበርና ከሩቅም ሆነ ከሰዎች መካከል እንኳ ይለያት ነበር፣ ብቻ ምን ልበላችሁ ከመቅጽበት ከአጠገቤ ተነሳና ስሜን ጠርቶ ስማ ዮሐንስ አሁን በአጠገቧ ሳልፍ ሰላም ብያት አልፋለሁ፤ ከዚያ ዞር ብዬ አልመለከታትምና አንተ እሷ ዞር ብላ የምትመለከተኝ ከሆነ አንተ እይልኝ ብሎ ልክ እንደመቶ ሜትር ሯጭ ከአጠገቤ ተስፈንጥሮ ተፈተለከ። ከዚያም እንዳለው አጠገቧ ሲደርስ ሰላም ብሏት የሞት ሞቱን ቀጥ ብሎ ሄደ። ብቻ ምን ልበላችሁ ልጅቷ አላስችል ብሏት ዞር አለች። እኔም ደግሞ በተነገረኝ መሰረት በዓይነቁራኛ የእሷን እንቅስቃሴ እከታተል ነበርና አንድ አልኩ። አደራዬን ለመጠበቅ እጅሬ እኔን እንደቪድዮ ካሜራ አቁሞና በልቡ ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ቀጥ ብሎ ዞር ሳይል ጉዞውን ቀጠለ። አጅሪት ጉዳዩ አላስችል ብሏት መታጠፊያው ጋ ስትደርስ ደግማ ዞረች እኔ ደግሞ ልክ ነጥብ እንደሚይዝ ዳኛ ሁለት ማለት ከዚህ በኋላ አብሮ አደጌ ውጤቱን ለማወቅ ወደእኔ ተመልሶ መምጣትና ወዲያውኑ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ እህ እንዴት ነው አየችኝ ሲለኝ እኔም የዳኝነቴን ሁለት ለዜሮ አልኩ እላችኋለሁ። ለነገሩ የእኔ ድጋፍ ባይኖረው ኖሮ ውጤቱ የተገላቢጦሽ ይሆን ይሆን? ለመፍረድ አስቸጋሪ (HARD TO SAY) ነው። እሱም አያስችለውም ነበርና ነው። በዕለቱ ጓደኛዬ ተደሰተ እኔም አሟሟቅሁት (ሞራል ሰጠሁት) በጉዳዩ ላይ ለመመካከር ዘወትር ቡናና ሻይ ወደምንጠጣበት ቦታ ለመሄድ ፕላን አወጣን እላችኋለሁ።

የዓይን ፍቅሩ ሁኔታ ተገባዷል አሁን የሚቀረው ተገናኝቶ መነጋገር ብቻ ነው የቀረው ተባባልን ተስማማን እንዴትና መቼ? የት ቦታ? እንደሚሆን ከፍተኛ እቅድ አወጣን መቸም የበሰለ ነገር ነበርና መግባባቱ ተሳክቶና ፍቅሩ ተጀምሮ በዛው ሰሞን ከነፉ እላችኋለሁ። እንዲህ እየሆነ በጊዜው ወጣቱ ሁሉ በዕድሜው የፍቅር አዝመራውን ያጭዳል ነው የምላችሁ አሁንም ቢሆን ይህ ነገር አይለወጥም በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ቋሚ ፀጋ ነው ደስም ይላል።

በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች ይህን ድርጊት በተለያየ ቦታና ጊዜ እናድርገው እንጂ የምንወደውን ዓይነት ሴት(ወንድ) ስናይ መደንገጥ፣ እንዳይነቃብን ደግሞ ቀስ ብለን በቆረጣ ማየት፣ አንዳንዴም ከጓደኛ ጋር በመሆን እንደ እኔና ጓደኛዬ አንተ ታየኝ እንደሆነ እይልኝ አደራህን መባባል ወይም በልጁ(በልጅቷ) የቅርብ ጓደኛ በኩል መወደድን ለማወቅ ማሰለል ያለነገር ነው። ዋናው ቁምነገር ግን ከልብ መውደድና መወደዱ ላይ ነው። አንፍራ አንንቀጥቀጥ ከወደድን ጠጋ ብለን እንይ።

እንግዲህ በእይታ የሚመጣውን ንፁህ ፍቅር ዘለቄታ እንዲኖረው ለማድረግ ራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ተፈቃሪ ለመሆን ንፁህ አፍቃሪ መሆን ያስፈልጋል? ያለበለዚያ ያየነውን ሁሉ የምንመኝና የምንወድ ከሆነ እንደአሻንጉሊት መጫወቻና ርካሾች እንሆንና ወደዝቃጮቹ ተቀላቅለን ወደታች መውረድና መዋረድ ይመጣል።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ የአይኑካው (የእይታው) ነገር ከተሳካ ወደመተዋወቁ ደረጃ ላይ እንሸጋገራለን። በዚህ ጊዜ ከበድ ያለጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በማንኛውም ጊዜ ደግሞ ሥነሥርዓት የግድ አስፈላጊ ሲሆን በተጨማሪ ከምንተዋወቀው ሰው ጋር ፀባይና ሁኔታ ጋር አብሮ ለመሄድ መሞከሩ ደግሞ ወሳኝና አስፈላጊም ነው።

ሌላው በትውውቁ ጊዜ የምንናገራቸው (የምንግባባቸው) ቃላቶች የተመረጡ መሆን አለባቸው። በማንኛውም ወቅትና ጊዜ በመጀመሪያ የትውውቅ ወቅት የሚደረጉ ቃለምልልሶች በፍቅር ህይወት ውስጥ የማይረሱና ቋሚ ትዝታን በፍቅረኞች ላይ የሚፈጥሩ ስለሆነ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። እኔ እስካሁን በሰዎች ላይ ካዳመጥኳቸው የመጀመሪያ ቀን የመተዋወቅ ታሪኮች ላይ ከንግግር ጥንቃቄ ባለማድረግ ብቻ ብዙ ሊያድጉና ሊቀጥሉ የሚችሉ ግንኙነቶችና ፍቅሮች በአቀራረብ ጉድለት ብቻ በከንቱ ሳያድጉ እንደተቀጩና እንደቀሩ አውቃለሁ። አያድርስ! ስለዚህ በትውውቁ ጊዜ በአግባቡና በሥነሥርዓት ተቃራኒው ፆታ እንደሚፈልገው በመሆን መፍጠን በሚያስፈልግበት ጊዜ ቀልጠፍ በማለት፣ ቀዝቀዝ ማለት በሚያስፈልግበት ጊዜ ረጋና ኮራ በማለትና ራስን በመጠበቅ ወይም እንደሁኔታው በመሆን የሚያስፈልጉትን ዓላማ መምታት አስፈላጊ ሲሆን እንደው ላየነው(ላየናት) ሁሉ መንበርከኩ ተገቢ አይደለም። ዓላማው ትክክለኛ አፍቃሪና ተፈቃሪ

በመሆን ዘለዓለማዊ የሆነ ህይወትን ለመቅረጽ ስለሆነ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚያም ትውውቁ የተሳካ እንዲሆን ማድረግ ተገቢና አስፈላጊ ነው።

ይህንን ባለማድረግ የሚመሰረቱ ጋብቻዎች ምንም እንኳ የተለያየ ምክንያት ይሰጣቸው እንጂ ጊዜያቸውን ጠብቀው ሲፈርሱ እንመለከታለን። እስቲ በዘመናችን ለትዳርና ለቤተሰብ መፍረስና መበተን ምክንያት ከሆኑት ጠባዮችና ባህርያት መካከልና ለፍቺ የሚያበቁ ነገሮችን በጥቂቱ እንመልከት።

1) ከትዳር ውጭ ከሌላ ሴት ጋር የሚደረግ የግብረሥጋ ግንኙነት (መቅበጥ) ሲሆን ይህም አሳስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንደኛውና ዋናውም የፍቺ ምክንያትም ነው። ትክክለኛ ትዳር ፈላጊ የሆነ ሰው ወደ ትዳር ዓለም ከመግባቱ በፊት የነበረበትን የአመንዝራ ፀባይ ሁሉ አስወግዶ ለራሱና ለባለቤቱ ቃልኪዳን ገብቶ አዲስ ህይወት መጀመር አለበት። ይህ ባለመሆኑ ምክንያት ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ህፃናትን ከማስከተሉም በላይ ቤትን ያፈርሳል። ምንም የማያውቁ ህፃናት በአባትና እናት እጅ ከማደግ ውጭ ይሆኑና ህይወታቸው የሚያሳዝን ይሆናል። ይህም በልጆች ላይ የሚፈፀም የስነልቦና ወንጀል ይሆናል።

2) በትዳር ውስጥ እያሉ በሚደርስ አደጋ ምክንያት ከሁለቱ አንዱ የብልት አለመስራት(impotence) ለፍቺ የሚያበቁና በህግ የተደነገገ ሲሆን በጋብቻ ሕይወት ውስጥ እያሉ ደግሞ የፍትወተሥጋ አለመጣጣም፣ የወንዱ ወይም የሴቷ ቀድሞ ሁልጊዜ መርካት፣ አንደኛው ሌላውን ሁልጊዜ ማርካት አለመቻል ለባል (ለሚስት) መቅበጥ፣ ከሌላ ጋር የፍትወተሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ስለሚገፋፋ ትዳርን ከሚያፈርሱ ዋነኛ ምክንያት አንዱ ይሆናል።

ይህንን ችግር ለማስወገድ ሐኪምን በቶሎ ማማከር ተገቢ ከመሆኑም በላይ አለመጣጣምን ለማስወገድ የሚቻለው በትውውቁና በመጠናናት፣ እንዲሁም በመግባባቱ ዘመን ስለሆነ በዚህ ጊዜና ወቅት በትክክል አረጋግጦ ወደ ጋብቻ ህይወት መራመዱ በዚህ ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን መለያየት (ፍቺ) ከወዲሁ ማቆም ይቻላልና ጠንቀቅ በሉ።

3) መካንነት በመግባባቱና በመጠናናቱ ዘመን ይህንን ጉዳይ ባለማወቅና ባለመረዳት ጋብቻ ይፈፀምና ከጥቂት ዓመታት በኋላ ልጅ ማግኘት ባለመቻላቸው ምክንያት ብቻ ሁለቱም ወገኖች እድላቸውን ለመሞከር ሲሉ የፍቺ ተግባር ይፈጽማሉ። አንዳንድ በሥርዓት የተዋወቁና የተጋቡ መካንነት ቢያጋጥማቸውም እንኳ በንፁህ ስለሚዋደዱ እስከለተሞታቸው ድረስ አብረው ይኖራሉ በዚህ ጊዜ የማደጎ ልጅ በማሳደግ ወይም የቤት እንስሳትን እንደልጅ በማፍቀር ያለባቸውንና ያጋጠማቸውን ሕይወት ያካክሱታል።

4) በትዳር ውስጥ እያሉም ሆነ ከትዳር ውጪ ለሕብረተሰብ ጎጂ የሆኑ ባህርያት:-

ሀ) ቁማርተኛነት ቤትን ያራቁታል፣ የቤተሰብን ኢኮኖሚ ያዳክማል፣ በቁማር ጨዋታ ቦታ የሚፈጠር ግጭት ለሕይወት መጥፋት (አደጋ) ምክንያት ሲሆን እንዲሁም ሁልጊዜ አምሽቶ መግባትን ከትዳር ጓደኛ ጋር ግጭትን አምጥቶ ለትዳር መፍረስ ምክንያት ይሆናል።

በተጨማሪም ለልጆች የሚገባ እንክብካቤን ይቀንሳል። እንዲያውም አልፎ ተርፎ ልጆች ከቤተሰባቸው አካል አንዱ ቁማርተኛ መሆኑን ካወቁ ከተረዱ ወደ መጥፎ ዓላማ ይገፋፋሉ። ይህ ደግሞ ስውር የሆነ የስነልቡና ወንጀል ነው።

ለ) ሰካራምነት(Alcholism):- ይህ ጠባይ በጣም ጎጂ ከሆኑትና ለትዳር መፍረስ ጠንቅ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛ ሲሆን በመጠናናቱ ጊዜ ላይ የጓደኛን ጠባይ ማረቁ ተገቢ ይሆናል። ካለበለዚያ ይህ ጠባይ መኖሩ እየታወቀ ትዳር ተመስርቶ ልጆች ከመጡ (ከተወለዱ) በኋላ መጥፎ ገጽታን ስለሚፈጥርና ለጤንነትም ጎጂ ከመሆኑም በላይ ብዙ የመኪና አደጋዎች ከስካር ስለሚመጣ ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረጉ ለሁሉም ችግር መፍትሔ ይሆናልና አስቡበት አደራ የራስና የሌሎችም ሕይወት ጉዳይ ነውና።

ሐ) የተለያዩ ዕፆች (ሱስ) drug መውሰድ:- በመጀመሪያ የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከትላል፣ ቀጥሎም የባህርይ ለውጥን ያስከትላል፣ ከዚያም በጤንነት ደረጃ ላይ ጉዳትን ያስከትላል (ያመጣል)፣ በሚወለዱ ህፃናት ላይም ችግርን ያስከትላል፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወደወንጀል ህይወት ያስገባል። በአጠቃላይ በዚህ ባህርይ ውስጥ የተጠመደ (የተጠመደች) ሰው ለትዳር መፍረስ ቀረቤታ ያለው ስለሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ታዲያ ይህ ባህርይ ከሁለቱ የታ በአንዱ ላይ ካለ የጋብቻ በፊት ማስወገድ ተገቢ ይሆናል። ካለበለዚያ ውጤቱ አደጋ ይሆናል።

5) የሃይማኖቱ ልዩነቶች:- በፍቅርም ሆነ በጋብቻ ላይ ለዘመናት ችግር ሲፈጥሩ ከቆዩት ጉዳዮች አንዱና ዋነኛዎቹ ናቸው። ሰውየው ክርስቲያን ሴቷ እስላም ይሆኑና ፍቅር ቢኖራቸውም በሃይማኖት ልዩነት ብቻ የተለያዩ (ሳይጋቡ የቀሩ) ብዙ ሲሆኑ በተጨማሪ በክርስቲያኖች መካከል እንኳ ኦርቶዶክስ፣ ጴንጤ፣ ጆሆባ በመባባል የተለያዩ ባለትዳሮች አሉ።

ሌሎች ከተጋቡና ከተዋለዱ በኋላ በመካከሉ በወንዱ (በሴቷ) ሃይማኖት በመለወጣቸው ምክንያት የሞቀ ትዳራቸውን አፍርሰው ቤታቸውን ዘግተው ልጆቻቸውን በትነው የቀሩም አሉ። በጣም ያሳዝናል። እንግዲህ ከጋብቻ በፊት የሰውየው (የሴትየዋ) ሃይማኖት ማወቅና አንድ ዓይነት እምነትና (ሃይማኖት) መኖርን ማወቅ ማረጋገጥ ከተጋቡም በኋላ ሃይማኖትን አለመለወጥ በትዳር ለመጽናት ከሚያስችሉት ጉዳዮች አንዱ ነውና በመጠናናት ዘመን ይህን ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው።

6) የፖለቲካ እምነት (አስተሳሰብ) ልዩነት ካለ በትዳር ሕይወት ውስጥ አስቸጋሪ ስለሚሆን ቶሎ በመጠናናቱ ዘመን አንድ እምነት ለመያዝ ጥረት ማድረግና መደጋገፍ አብሮ ለዘለቄታው መሥራት ወይም ሁለቱም ወገኖች ተስማምተውና ከዚህ አስተሳሰብ ወጥተው በቤተሰብ ህይወት ላይ ቅድሚያ በመስጠት ወይም ስለፖለቲካው ተሳታፊ (ሰውየው ወይም ሴትየዋ ሊሆኑ ይችላሉ) እምነት በትክክል አውቆ ጣልቃ ገብነትን አለመፈፀም ካለበለዚያ ለወደፊቱ ልጆች ከተፈጠሩ በኋላ አስቸጋሪ ስለሚሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።በዚህ ምክንያት የፈረሱ ቤቶች ያሳዝኑኛልና ለወደፊቱ ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ ነው እላለሁ። ለወደፊቱ አደራ አደራ።

7) በተለይ በአሁኑ ወቅት በዘር ልዩነት ምክንያት ብዙ ፍቅረኛሞች ግንኙታቸውን ሲያቆሙ፣ ብዙም ትዳሮች ፈርሰው ልጆች ያለአባትና ያለእናት የመቅረት ሁኔታ ሲታይ ያሳዝናል። ይህ ችግር በእኛ ሕዝብ ላይ ብቻ የሚታይ ሳይሆን በመላው ዓለም ህዝብ ውስጥ ያለ ችግር ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም። ስለዚህ በመጠናናቱ ጊዜ ይህንን ችግር አስቀድሞ በማጥናት ወይም በማወቅ ወደ ትዳር ሕይወት ከመግባቱ በፊት ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ ነው። ይህ ካልሆነ ችግር መኖሩ እየታወቀ በጊዜያዊ ውሳኔ ወደጋብቻ ህይወት ብናመራ ጊዜውን ጠብቆ ይህ የዘር ልዩነት ጥያቄ ይመጣና ለሞቀ ትዳር መፍረስ ምክንያት ይሆናል።

በዚህ ጉዳይ ወሳኞቹ ሁለቱ ፍቅረኛሞች ናቸው። በንፁህነት ከተዋደዱና ከተፋቀሩ ለዘለአለም አብረው መኖር ይችላሉ ዋናው ቁምነገር የፍቅርን ዓለምአቀፋዊነት (Universal) ማመን ብቻ ነው።

በንፁህ ፍቅር (True Love) ምክንያት የመጣባቸውን የዘር፣ የሃይማኖትና የፖለቲካ ጥያቄዎች ተቋቁመው አብረው የሚኖሩ ወይም ከነልጆቻቸው ከዚህ ልዩነት ለመራቅ ሲሉ የተሰደዱና ከነገርና ከሰው ርቀው የሚኖሩ ብዙ ፍቅረኛሞች አሉ። እጅግ ደስ የሚል ታላቅ የፍቅርና የዓላማ መስዋዕትነት ነው። በርቱ ግፋበት አንድ ቀን ይቅርታ ይጠይቁአችሁ ይሆናል።

8) በሐብት መቀነስ(ኪሳራ) ምክንያት ብዙ ፍቅረኛሞችና ትዳሮች ሲፈርሱና በጥቅም ላይ የተመሰረተ ስለሚሆን ሰውየው (ሴትየዋ) ላይ የንግድ ኪሣራ፣ ከሥራ መውጣት፣ መታሰር ወይም ሌሎች ችግሮች ሲፈጠሩ ክደት ይመጣል። ይህም በሰላማዊው እምነት ላይ ያልተመሰረተ ፍቅርና ጋብቻ ስለሆነ በአደባባይ ሲፈርስ እናያለን። ስለዚህ በመጠናናቱ ወቅት ጥንቃቄ ማድረጉ ወደፊት በሚደርሰው መከዳዳትና መለያየት ሲያድን፤ በችግርም በመከራም ልትኖር(ሊኖር) የምትችል (የሚችል) ጓደኛና ሚስት (ባል) መፈለጉና ማግባቱ የብልህ ወይም የአዋቂ ሰው ተግባር ነው እላለሁ። እውነተኛው ፍቅር ቋሚና ዘላቂ ነው።

9) የአእምሮ ቀውስነት ያለበትን (ያለባትን) ሴት (ወንድ) ማግባቱ በወደፊት ህይወት ላይ አስቸጋሪ ሁኔታን ይፈጥራል። ይህንን ሁኔታ አስቀድመን በመጠናናቱ ዘመን ማወቁ አስፈላጊ ይሆናል። የአእምሮ በሽታ ጉዳይ ከተነሳ ሰዎች ከተጋቡ በኋላና ልጆች ከወለዱ በኋላ ይህ በሽታ ከሁለቱ በአንደኛው ላይ ሊመጣ ይችላል። በዚህ ጉዳይ በህግ አንፃር የፍቺ መብትን ማግኘትን ይቻላል። ነገር ግን በንፁህ የተፋቀረ ሰው እስከመጨረሻው በማሰብም የግለሰቡን ወይም የግለሰቧን አእምሮ የበለጠ ከመጉዳት ማዳን ያስፈልጋል። ይህም በአበደ ሰው ላይ የበለጠ ብስጭትን ፈጥሮ የበለጠ እብደትን ላለመፍጠር ለንፁህ ፍቅር ሲባል የሚከፈል መስዋዕትነት ይሆናል። እንግዲህ ይህንን ሃሳብና ሌሎችንም የፍቺ ምክንያቶች ያስቀመጥኳቸውና የማስቀምጣቸው ከጋብቻ በፊት በፍቅር ህይወት ወጣቶች አውቀው ወደጉዳዩ ይገቡበት ዘንድ ነው።

10) በወንጀለኝነት ሰውየው (ሴትየዋ) እስር ቤት የገባ (የገባች) እንደሆነ በህግ ፍርድ ቤትን ፍቺ በመጠየቅና በማስፈቀድ መፋታት ይቻላል። ንፁህ ፍቅር ግን ይህን ሁኔታ ይቃወማል፣ ይቋቋማልም። በችግርም ይሁን በመከራ ጊዜ አይለወጥም።
ብዙ ጠንካራ ሰዎች ለረጅም ጊዜ ባሎቻቸው ወይም ሚስቶቻቸውን ባለመታከት ሲጠይቁ ቆይተው ሲፈቱ አብረው የኖሩና የሚኖሩን ንፁህ አፍቃሪዎችን ተመልክቻለሁ። ይህ የሰላማዊና የንፁህ ፍቅር ውጤት ሲሆን በሁለተኛውና በህገወጡ ዓይነት ፍቅር ግን እንኳንስ ከእስር ቤት እስኪፈቱ ድረስ ለመጠበቅ ቀርቶ ያለን ንብረት ለመዝረፍ ሩጫውና እሽቅድድሙ መከራ ነውና ጉዳዩን ከወዲሁ ተረድተን በንፁህ የምታፈቅረንን (የሚያፈቅረንን) ማግባቱ ጥሩ ይሆናል።

11) በመኖሪያ ክልል ምርጫ ምክንያት ብዙ ፍቅሮች ይቀጫሉ። እንዲሁም በመኖሪያ ቦታ ምርጫ አለመግባባት ምክንያት ጋብቻ በህግ ሊፈርስ ይችላል። ለምሳሌ ወንዱ ወይም ሴቷ በጤንነት ምክንያት ሞቅ ያለ የአየር ጠባይ ያለበት ቦታ መኖር አስፈላጊ ቢሆንና አካባቢ መለወጥ አስፈላጊ ቢሆን ሁለተኛው ሰው አብሮ መሄድ ባይችል ወይም ባይፈልግ መፍታት ግዴታ ሊሆንበት (ሊሆንባት) ይችላል። ሌላው ሰዎች ንፁህ ፍቅር እያካሄዱ እያሉ በሥራ ጠባይ ምክንያት የመኖሪያ ክልል የመቀየር ሁኔታ ሲፈጠር አንዱ አብሮ ለመጓዝ ባለመፈለጉ ምክንያት ስንት ዓመት የተለፋበት ትዳር ይፈርሳል።
ብዙ ወጣቶች በትምህርት ምክንያት አካባቢ ይለውጣሉ። ሁለተኛ ደረጃ ሲጨርሱ ከነበሩበት ቀዩ ወጥተው ወደሌላ ከተማ ይሄዳሉ፣ ኮሌጅ ሲጨርሱ እንደገና ወደሌላ ዩኒቨርስቲ ይተላለፋሉ። በዚህ ጊዜ ከሚወዷት (ከሚወዱት) ልጅ ሳያስቡት ሊለዩ ይችላሉ። እጅግ ያሳዝናል፣ እያድርሰ ነው የሚባለው።

ዋናው ዓላማ በመጠናናት ዘመን ይህ ችግር እንዳይመጣ ቀደም ብሎ ማሰብና መጠንቀቅም ያስፈልጋል። በኋላ በፍቅር እንዳትንዘፈዘፉና ብስጭት ውስጥ እንዳትወድቁ ከወዲሁ አስቡበትና አብራችሁ ለመኖር ሞክሩ። ካለበለዚያ አብራችሁ በትምህርቱም በሥራውም ተሰደዱ፣ አምላክ ያውቃልና። በፍቅርም አይጨክንምና።

ካለበለዚያ ፍቅረኛ እየራቀ (እየራቀች) ስትሄድ ነገሮች ሁሉ እየቀዘቀዙ ይሄዱና ጊዜው ሲቆይ መረሳት ይመጣል። አንዳንድ ንፁህ አፍቃሪዎች ጊዜ ቢቆይም ቦታ ቢርቅም ቃልኪዳናቸውን የጠበቁና የተጋቡም ሞልተዋል። እነዚህ ንፁህ አፍቃሪዎች ስለሆኑ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

12) አላስፈላጊ የሆነ የጾታ ፉክክር "ሴት ከወንድ እኩል ናት አይደለችም" የሚለው ሃሳብ ስሜት) የተፈጥሮን ህግና የፍቅርን ምንነት በትክክል ካለመረዳት የተነሳ ከዘመናት ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ችግርነቱ ቀጥሏል።

ምንም እንኳን በሕፃንነትና በወጣትነት ዕድሜ ላይ እያለን በመጀመሪያ ፍቅር (First Love) ውስጥ እያለን ይህ ችግርና ስሜት ባይኖርብንም እድሜአችን ጨምሮ ወደ ትዳር ህይወት ከገባን በኋላ ልጆች ሲወለዱና ሁለቱም ፆታ ስራ ሰርተው ሲገቡ አንዳንድ ጥቃቅን ችግሮች ይመጣሉ።

ብልህና ንፁህ ተፈቃሪዎች ይህንን ጎጂ አዝማሚያ በጥንቱ ፍቅራችን ብለው ወዲያውኑ ይቀጩታል። ይህም ጥያቄ ለዘለአለም ላይነሳ ይችላል።

እነዚህ ስርዓት በሌለው ፍቅር በኩል የመጡ ደግሞ ሴትን ልጅ በመናቅ ከወንድ ያነሰች ታዛዥና ገረድ በማድረግ ያቀርቧትና እኔ የማዝሽን ብቻ አድርጊ የሚል አላስፈላጊ የሆነ የራሳቸው የበላይነትን በቤተሰቡ ውስጥ ለማስፈን ጥረት ያደርጋሉ።

በተቃራኒውና ሥርዓት በሌለው ፍቅር በኩል የመጡ ደግሞ ሴትን የቤተሰብ አዛዥና ተቆጣጣሪ በማስመሰል ግብዝነትን ለማሳየት ጥረት ያደርጋሉ። ከባላቸውም ጋር ፉክክርን ይያያዙታል። እንዲያውም አልፈው ተርፈው ወንዱን ልዘዝህ፣ እኔ የምልህን ብቻ አድርግ፣ እታምሽ ከቤት አትውጣ በማለት ጭቅጭቅን ይፈጥሩና የሞቀ ትዳራቸውን ያፈርሳሉ።

በእውነት ነው የምላችሁ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታና የበላይነትና የበታችነት ፉክክርና ክርክር ለረጅም ዓመታት ሳዳምጥ ቆይቻለሁ። በየትኛውም የዓለም ክፍል በማንኛውም ቦታና ጊዜ ሴት ልጅ ወንድንም ሴትንም የምትወልድና ብዙ ጀግናዎችንም ምሁራኖችንም የምታፈራ ስትሆን ወንድ ልጅም እንዲሁም ይህንን ሁኔታ ለመፍጠር ምክንያትና አስፈላጊ የሆነ ፆታ ነው። ሁለቱ ፆታዎች በመግባባትና ሰላማዊውን ፍቅር ለመገንባት በዚህች ውብ ዓለም ውስጥ ያሉትን የተፈጥሮ ስጦታዎች በመቀበል ያለቻቸውን እድሜ በስምምነት በፍቅርና በክብር ማሳለፍ አለባቸው።የሰው ልጅ ተራቆ ወደሌላው ዓለም ምርምር ውስጥ በገባበት ዘመን ይህንን ዝቃጭ (ትራሽ) የሆነ የማይጠቅም ሃሳብ አምጥቶ ከተፈጥሮ ህግ ጋርና ሁኔታ ማጋጨቱ ኃጢአት ስለሚሆን ሴትን ልጅ በሴትነቷ ወንድን ልጅ በወንድነቱ ማየትና ማክበር እንዲሁም አብሮ ሰርቶ ለቤተሰቡ ዕድገት የተለያዩ ዕቅዶች በማውጣትና ተግባራዊ በማድረግ ቀሪውን እድሜ በደስታ ማሳለፍ ተገቢ ነው እላለሁ።

13) በጋብቻ ላይ እያሉ ባልታወቀ ምክንያት ከሚስት (ከባል) ከ2 ዓመታት በላይ መሰወር (መጥፋት) ለጋብቻ በህግ መፍረስ ምክንያት ሲሆን ይህም የሚፈፀመው ከሁለቱ አንዱ አካል የፍቺ መብት የጠየቀ እንደሆነ በፍርድ ቤት የፍቺ መብት ይፈቀዳል። ብዙውን ጊዜ እንዲህ ዓይነት የመጥፋትና የመሰወር (አድራሻን የመደበቅ) ሁኔታዎች የሚፈጥሩት ከጋብቻ በፊት ወይም ከጋብቻ በኋላ ጓደኛን እጮኛን ሚስትን (ባልን) ሚስጥር በመደበቅ ከሌሎች ሕገወጥ ሰዎች ጋር ግንኙነት በማድረግ የሕጋዊ ሰዎች ክትትል ሲበረታ ለማንም ለምንም ሳይናገሩ (ሳያሳውቁ) ብዙ ሰዎች ይሰወራሉ። ይህም የራስን ህይወት ለማዳን ከሚደረግ ውሳኔ ጋር የተያያዘ ነው።

በዚህ ጉዳይ እኔ የምለው ነገር ቢኖር በዚያ በመጠናናቱና በመጋባባቱ ዘመን በዚህ ዓይነት አላስፈላጊ ጉዳዮች እጃችንን አስገብተን ከሆነ እዛው እንደፍጥርጥራችን ራሳችን መወጣቱ እንጂ የሌላውን ንፁህ አፍቃሪ ህይወት መጉዳቱ (ማስገባቱ) ተገቢ ካለመሆኑም በላይ ከጋብቻ በፊት ይህንን ለወደፊቱ ለፍቅርና ለጋብቻ ጠንቅ የሆነውና የሚሆነውን የሌላ ግኑኝነት በቶሎ ማስወገድና ንፁህ ሆኖ በንፁህ አፍቅሮ ወደ አዲሱና ዘለአለማዊ ህይወትና ደስታን ወደሚሰጠው ደረጃ ላይ መሸጋገር ያስፈልጋል።

ሌላው ስህተት ደግሞ አንዳንድ ሰዎች በፍቅርና በጓደኝነት በእጮኝነት ጊዜ ፍቅረኛቸውን ለማስደሰት ሲሉ በማይረባና በማያዛልቅ ጉዳዮች ውስጥ እጃቸውን ያስገባሉ። ያላቸውንም ትክክለኛ የኢኮኖሚ ደረጃና የስራ ፀባይ ሳይገልፅ እንደሐብታምና እንደባለሥልጣን ሰው ተመስለው በመቅረብ አለአግባብ በፈጠሩት ግኑኝነትና ቋሚ ባልሆነው ገቢ ደስታን ሲፈጥሩና ገንዘብ ሲረጩ ይቆዩና በአንድ አጋጣሚ ይህ ጉዳይ ሲቆም (ሲደረስበት) ያ የሞቀ ፍቅር እንደጤዛ ይረግፋል። ይህም በጣም ያሳዝናል። ወገኖቼ ካላችሁ አቅም በላይ በሀሰት ለመከበርና ለመፈቀር ጥረት አታድርጉ፣ በንፁህነት ቅረቡ ግልጽ ሁኑ። ካለበለዚያ ራሳችሁ አዝናችሁ ንፁህ አፍቃሪዎችንና የዋሆችን ታሳዝናላችሁ። ወገኖች ይህ ጉዳይ በብዙ ሰዎች ህይወት ላይ የታየና የተረጋገጠ ሐቅና እውነትነትም ያለው ነው። በጣም ያሳዝናል። እኔን በዚህ ጉዳይ የበለጠ የሚያሳዝነኝ በትዳር

ህይወት ውስጥ እያሉና ልጆቹ ከወለዱ በኋላ የሚሰወሩ ሰዎች ዘለአለማዊ ፀፀትን በቤተሰባቸውና በወለዱት ልጆች ላይ ስለሚፈጥሩና ልጆችም ባደጉ ጊዜ አባታችን (እናታችን) የት አለ (አለች) በማለት ለዘለዓለም ስለሚያስቸግሩ ቀድመን ይህንን ጉዳይ አውቀን ራስንም ሌሎችንም ከመጉዳት እንጠንቀቅ እደራ እደራ እላለሁ።

14) ከዚህ ዓለም በሞት በመለየት ምክንያት ጋብቻ በህግ ይፈርሳል። ይህም እያድርስ የሚባል ጉዳይ ነው። ፍቅረኛሞች በሞቀ ፍቅርም ውስጥ እያሉም ወይም በእጮኛነት ደረጃ ውስጥ ሆነው ስለወደፊቱ ሕይወታቸው እየተመካከሩ ሳለ ከሁለቱ አንዱ በድንገተኛ አደጋ ወይም በአጋጣሚ በሥራ ጉዳይ በወታደራዊ ግዳጅ (በጦርነት) ላይ ይሞታሉ። በጣም ያሳዝናል ሌሎች ደግሞ ተጋብተውና ልጆች ወልደው በፍቅር ሲኖሩ ሳለ በመካከሉ አንደኛው በዕድሜ፣ በአደጋ በጦርነት ሲሞቱ ጋብቻ በሕግ በፍርድ ቤት ይፈርሳል።

ሁሉም ያሳዝናል። ከዚህ ሁሉ አሳዛኝ ሁኔታ እምላክ ያውጣን። ዘለቄታ ያለውን ፍቅር ያውርሰን። የእኔ ፀሎትና እምነት ንፁህ ፍቅርን የሚገኝበትንና የሚጠናከርበት ሰዎችም በዚህ ተጠቃሚ ሆነው የሚኖሩበትን ለመግለጽ ነው እንጂ ሰዎች በህግ በፍርድ ቤት ይፈርሳል።

ለጠቅላላ እውቀትና በፍቅርና በጋብቻ ውስጥ ፍቺና መለያየት እንዳለ አስቀድሜ በማስጠንቀቅ ሊመጣ የሚችለውን ችግር ለማቆም ወይም ለመቀነስ እንዲሁም ለጠቅላላ እውቀትም ጭምር ነው።

እኔ አዲሱ ትውልድና ወጣቱ እንዲያውቀው ብዬ ፃፍኩት እንጂ ስለመለያየት (ፍቺ) ጉዳይ እንኳንስ መፃፍ ቀርቶ ለደቂቃም ማሰብ ፈቃደኛ አልነበርኩም።

ያም ሆነ ይህ ጽፌዋለሁ። እኔ በበኩሌ የምወደው ግን አለ አይደለ እነ እጅሬ የሚያውቁትን የምታቅበጠብጠውን፣ እርቦን እያለ ምግብን በቃኝ በቃኝ የምታሰኘውን በደቂቃ ውስጥ የምታስደስተውን፣ የምታስቀውን የምታስለቅሰውን፣ ስለእሷ እሷ፣ ስለእሱ እሱ ብቻ የምታሰኘውን ወይም ከእሱ ወይም ከእሷ በፊት እኔን ያስቀድመኝ ተብሎ መስዋዕትነት የሚከፈልበትን ወይንም መቼ አይቻት፣ መቼ አይቸው (መንፋፈቅ) መቼ ምሳ (እራት) አብረን በልተን ወይም አብረን ወጥተንና ደስታን አብረን ተካፍለን፣ የተፈጥሮን ህግ ፈጽመን በመጨረሻም ቤተሰቤን አስተዋውቄው (አስተዋውቄአት) መቼ ቀለበት አድርገን ተጋብተን፣ ልጅ ወልደን የሚባልበትን በዚህ ፍቅር ዘመን በመካከል ዕለት በዕለት ስልክ እየተደዋወለ ሰዓት መግደሉን፣ ጠዋት እንገናኝ ተባብሎ ተገናኝቶ የሚወራ ወሬ የለ ዝም ብሎ መተያየት ዓይን ቅዝዝ ማለት አንዳንዴም እወድሃለሁ (እወድሻለሁ) ተባብሎ መላቀስ፣ ለአንድ ቀን ከተለያዩ ዓመት እንደቆየ መምሰልና ጥምጥም ብሎ መተቃቀፍ ጉድ ነው።

ይህ ነው ፍቅር ማለት፤ መጨነቅ፣ መጠበብ ዓይንን ጨፍኖ በዓይነህሊና ስለምትወደው ሰው ማሰብ፤ እቤት ደስ ሲል፤ ልብ ጥፍት እኮ ነው የሚለው፤ ያም ሆነ ይህ ደስ ይላል። ይህ ዓይነቱ መውደድና መወደዱ አእምሮም እያደገ ይሄድና በየደረጃው ይቀጥላል። መወደዱን ማፍቀሩን መንዘፍዘፉን የአራዳ ልጆች ፎንቃ ይሉታል ያለ ጉዳይ ነው። የእውነተኛው ፍቅር ምልክቶች ናቸው። በዚህ ዓይነት የመጣና የዳበረና ያደገ ንፁህ ፍቅር (True Love) ለወደፊቱ ህይወታችን ጠቃሚና ዘለዓለማዊ ደስታን የሚሰጥ ስለሆነ በርቱበት። እንግዲህ ከላይ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ አስራ አራት ድረስ የጠቀስኳቸውን የፍቺ ምክንያቶች በህግና በማህበራዊ አንፃር ችግሮችና በጋብቻ ውስጥ የሚያመጡትን ፍቺና ጎጂነት በማወቅ ለወደፊቱ ጥንቃቄ በማድረግ ንፁህ ሁኔታን በመፍጠር ወይም ይህንን በጎና ሰላማዊ ግንኙነት ለማጠናከርና ከወዲሁ በመጥረግ፣ በማጽዳት በመጠናናቱ በመግባባቱ ሁሉን አሳምረን ሰዓቱ ሲደርስ ወደማይቀረው ጋብቻ በእምነትና በድፍረት በታማኝነትና በዘለዓለማዊነት እንዘፈቅበት። በዚህ ጊዜ እመኑኝ እንጎዳበትም፣ እናተርፍበታለን፣ እንደሰትበታለንም እሺ!

ወገኖቼ እውነቱን ልንገራችሁ የተፈጠርነው ለዚሁ ነው። አጠቃቀሙንና አደራረጉን እንወቅበት ይህንን ሁኔታ ደግሞ ከመሰረቱ ለማሳመር ከተፈለገ ታዳጊ ወጣቶችን ከትምህርት ቤት ጀምሮ ትክክለኛውን የፍትወተ ሥጋ አጠቃቀም (Sex Education) ትምህርት በማስተማርና በመከታተል ጤናማ የሆነ ሕብረተሰብ መፍጠሩ የአባቶችን የእናቶች ኃላፊነት ሲሆን የመንግሥትም ኃላፊነት ጭምር ነው። መንግሥት ማለት ደግሞ ሕዝብ ማለት ነው። ለወደፊት አገርን የሚረከቡ ወጣቶችን በሁሉ አቅጣጫ በትክክልና በሥርዓት ካልቀረጽና ለወደፊቱ ጥፋት ማን ነው ተጠያቂው? በዚህ ጽሑፌ ላይ ወደፊት ለሚመሰረተው ቤተሰብና ሕብረተሰብ ማለቴ ነው Ok! እንደው ለማስታወስ ያህል ድሮ በአገራችን አባቶቻችን እናቶቻችን ከባህላችን ጠንካራነትና እርስ በእርሳቸው ቤተሰብ ለቤተሰብ ከመዋደዳቸው የተነሳ ለጓደኛቸው ልጁ ገና ያልተወለደች ልጅ በእናቷ ሆድ እያለች ሴት ከሆነ ለልጅህ ሰጥቻለሁ ይባባሉ ነበር። በዚህም ዓይነት ተወልደው አብረው አድገው ሳይፋቱ ልጆቻቸውን ወልደው እነሱም እንደአባቶቻቸውና እናቶቻቸው አድርገው እኛን አቆይተውናል። አሁን ደግሞ ዘመን እየለፈና እየተለዋወጠ ሲመጣ ባህልም እየታደሰ እየተለወጠና እያደገ ሲመጣ ወጣቶች በትምህርት ቤት በአብሮ አደግነት (በጉርብትና)፣ በሲኒማ ቤቶች፣ በትያትር አዳራሾች፣ በስፖርት ማቀውተሪያ ስፍራዎች፣ በመዝናኛ ቦታዎች፣ በምሽት መዝናኛ (Night Club)፣ በቤትና በሆቴሎች በሚደረግ የጭፈራ ዝግጅት (party)፣ በሥራ ቦታ . . . ወዘተ በመተዋወቅ በራሳቸው ምርጫ ፍቅርን ጀምረው ፍቅሩ ሲያይል ለአባታቸውና ለእናታቸው ወይም ለወንድሞቻቸውና ለእህቶቻቸው ጓደኛዬ ናት ጓደኛዬ

ነው (Boy Friend or Girl Friend) ብሎ ማስተዋወቁ የማያሳፍርበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ይህም በጣም ግሩም ነው ። ፍቅሩ ቋሚና ዘለቄታነት ካለው ይህ የማስተዋወቁ ነገር ከአሁን በፊትም ሆነ አሁን ሲደረግ ወላጆቻችንም በደስታ ተቀብለውታል። ይህም አዲሱን ባህል እየተቀበልን የመጣን መሆናችንን ያሳየናል። ጥሩ ነው ግን አደራ አትከዳዱ። ይህ ቢሆንም በሥርዓት ከመተያየቱ ጀምሮ ወደመግባባቱ ወደመጠናናቱና መግባባቱ ስንሄድ ፍላጎታችንን አንድ ማድረግ ወይም ማቀራረብ ያስፈልገናል። በተለይ በመግባባቱና በመጠናናቱ ዘመን (Boy friend or Girl Friend) ስንሆን የጓደኛችንን ፍላጎት ጠንቅቀን ማወቅና ከእሱ ወይም ከእሷ ፍላጎት ጋር አብሮ መሄድ ወይም የእሱን ወይንም የእሷን ፍላጎት አለመንካት ለምሳሌም ያህል ስፖርት መሥራት ወይም መጫወት ይወድ እንደሆነ ቢቻል እሱ የሚወደው የስፖርት ዓይነት ተሳታፊ መሆን ያ ካልሆነ ደግሞ የእሱን ፍላጎት አለመቃወም የጓደኛን ፍላጎት መደገፍና መጠበቅ ለራስ የሚሆነውን ሌላ ዓይነት ስፖርት መስራት ለፍቅር መዳበር ይጠቅማል። በተጨማሪም የአካል እንቅስቃሴ ዕለት በዕለት ማድረጉ ለአካል መዳበር፣ ለአእምሮ ንቃትና ቀልጣፋነት ከመርዳቱም በላይ በማህበራዊ ግንኙነት ላይ የጠቃሚነት ባህርይ አለው። እንዲሁም በጤንነት በኩል እጅግ የሚጠቅም ሲሆን ሁለቱንም ፍቅረኞሞች በሁሉም ጉዳይ ጠንካራና ብርቱ ያደርጋቸዋል።

ሌላው ፍላጎትን ማቀራረብ ወይንም አንድ ማድረግ ከሚገባን ጉዳዮች አንዱ ሙዚቃ ነው። መቼም ሙዚቃን ቢቻል መጫወት ባይቻል ደግሞ መስማት የማይወድ ያለ አይመስለኝም። ምናልባት ሰዎች የሚወዱት የሙዚቃ መሳሪያ ዓይነት ሊለያይ ይችላል። የሚያዳምጡትም የሙዚቃ ዓይነት እንደዚሁ ለምሳሌ አንዳንዱ ሰዎች የአማርኛ፣ የትግሪኛ፣ የኦሮምኛ፣ የጉራጊኛ፣ የአደርኛ . . ወዘተ ዘፈኖችን ወይም በአገራችን ባህል ውስጥ የሚዘፈኑ ዘፈኖችን ይወዳሉ። በዚህም ባቢያ መደነስና መጨፈር የሚወዱ ወጣቶችም በብዛት ይገኛሉ። ሌሎች ደግሞ የአገራቸውን ሙዚቃ እያዳመጡ በተጨማሪ የሌላውን ዓለም ሙዚቃ የሚያዳምጡና የሚወዱም አሉ ማለት ርክ ኤንድ ሮል (Rock and Roll)፣ ካንትሪ ሙዩዚክ (Country Music)፣ ብሉስ (Blues)፣ ራፕ (Rap)፣ ሪዝም ኤንድ ብሉስ (Rthyem & Blues)፣ ፓፕ (Pop)፣ ሬጌ (Reggae)፣ አፍሪካን ሙዩዚክ (African Music)፣ ክላሲካል (classical) ሙዩዚክ ...ወዘተ የሚወዱትን ዓይነት ሙዚቃ አብሮ በማዳመጥና ፍላጎትን በማቀራረብ ብሎም አንድ በማድረግ ወደ ትዳር ህይወት መግባቱ እጅግ በጣም አስፈላጊና አስደሳችም ጭምር ነው። ሌላው ፍቅረኛችሁ ሰዓሊ ወይንም ቀራጭ ቢሆን የሥራው ጠባይ ብዙ ጊዜንና ትዕግስትን የሚጠይቅ ስለሆነ ይህንኑ ቀድሞ በማወቅ የሥራን ጠባይ ጊዜና የፍቅርን ጊዜ ማወቁና በፕሮግራም መጠቀሙ አስፈላጊ ሲሆን በዚህ ሙያ ውስጥ ሁለቱም የታ ያሉበት ከሆነ እሰየው ካልሆነ ግን አንዱ ወገን የሌላውም ሥራ የሚወድና የሚያደንቅ ቢቻል አስተያየት የመስጠት ችሎታ ቢኖረው ይመረጣል፣ ከፍተኛ ትዕግስትንም ይጠይቃልና አውቃችሁ ግቡበት።

ሌላው ብዙ ሰዎች አገር መጎብኘትን ይወዳሉ። ይህ ጠባይ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑትና ማንኛውንም ሰው ቢያደርገው ማለትም ከፍቅረኛው ጋር ቢያደርገው ፍቅሩን ሲያዳብርበት (Romantic Love) ስለሚችል ይህንን በጋራ ማድረጉ ለፍቅር እድገት ይረዳል።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከሁለቱ አንዱ የዚህ ጠባይ ኖሮ ሌላው ከሌላው ለፍቅር መቀጨት ምክንያት ይሆናልና በዚህ የመጎብኘት ልምድ ላይ በመግባባቱና በመጠናናቱ ጊዜ ጉዞ በመነጋገር መፍትሔ መስጠቱ ጠቃሚ ነው። ከፍቅረኛ ጋር አብሮ አገር መጎብኘት እጅግ ደስ አይልም?

በአጠቃላይ በጓደኛነት በእጮኛነት ዘመንና በጋብቻ ጊዜም ቢሆን የራስን ፍላጎት ብቻ ከማስቀደም ይልቅ ፍቅረኛ (ተቃራኒውን ፆታ) የሚፈልገውን አብሮ ማድረጉ ለፍቅር እድገት ጠቃሚ ሲሆን ሌሎችንም ፍላጎትች ለምሳሌ ሲኒማየ ቲያትር፣ ኦፔራ፣ ታላቅ የሙዚቃ ዝግጅት (concert) ሲደረጉና ሲታዩ አብሮ ጊዜን ማሳለፉ ለፍቅር እድገት አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ሲሆን በተለይ መጽሐፍ የማንበብ ፍቅር ያላቸውን ሰዎች በምንግባባት ጊዜ አንድም አብሮ አንባቢ መሆን ያለበለዚያ ከፍተኛ ትዕግስትን ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ካለበለዚያ እንደምንተዋወቀው እባክህን (እባክሽን) አትደብረኝ ወይም አትደብሪኝ ይመጣና ቀጥሎም ተው ተው እንደባበር፣ ቀጥሎም ፍቅር ወደመፍረሱ ደረጃ ይሸጋገራል። ሌላው የደራሲዎች (የፀሐፊዎች) ህይወትና ባህርይ ጠንቅቆ ማወቅ ቢቻል ራስም ለመፃፍ መሞከር ካለበለዚያ የተፃፈውን በማንበብ አስተያየት መስጠት ማድነቅ ወይም በሚጽፍበት (በምትጽፍበት) ጊዜ ቡናና ሻይ በማፍላት አልፎ አልፎ ቀስ ብሎ ጉንጭን በመሳም ማባረታታት አስፈላጊ ነው። ይህ ሁሉ ድካም ፍቅርን ለማዳበርና ፍላጎትና ጠባይን ለማዋሃድና አንድ ለማድረግ ጭምር ነው።

ስለዚህ በፍላጎት አጠባበቅና ፍላጎትን በማዋሃድና አንድም በማድረግ ፍቅር የሚዳብርበትን የሚጎለብትበትን የሚያድግበትን ብሎም የሚሞቅበትን ሁኔታ ሁልጊዜ ለመፍጠር ጥረት እናድርግ።
ሌላው ዋናውና መሰረታዊው ጉዳይ የሥራና የትምህርት (የዓላማ) ጉዳይ ሲሆን ሁለቱም ወገኖች (ፍቅረኛሞች) በዚህ የህይወት እንቅስቃሴ ላይ ህብረትና መደጋገፍ ሊኖራቸው ይገባል።

አገሬ በነበርኩበት ጊዜ በጣም ብዙ ሰዎች በመጠናናቱና በመግባባቱ ጊዜና እንዲሁም ከተጋቡና ልጆች ከወለዱ በኋላ ጠንክረው በመሥረትና

በመተባበር በመሥራትና በመማር ለቁም ነገር ደረጃ የደረሱ በጣም ብዙዎች ናቸው።

ብዙዎች በንፁህ ከመፋቀራቸውና ከመተማመናቸው የተነሳ ከሁለቱ አንዱ (ወንድ ወይም ሴቷ) መስዋዕትነትን በመክፈል በማስተማር ወይም ተራ በተራ በመማማር ሳይከዳዱ ለቁምነገር የበቁ ሕይወታቸውን ያሻሻሉ እዚህም አሜሪካን አገር አጋጥመውኛል አብረው እየኖሩ ፀባይ ለፀባይ እየተዋሃዱና እየተቀናጁ አብረው እያደጉና ያልፈለገ እርግዝና እንዳይመጣና ዓላማቸው እንዳይጨናጎል እየታገሉ ትምህርታችውን ሲጨርሱና ነገሮች ሲስተካከሉላቸው በሥርዓት ወደ ጋብቻ ደረጃ የሚሸጋገሩ (የተሸጋገሩ) ብዙ ንፁህ አፍቃሪዎችም አሉ ደስ አይሉም። በእውነቲ ደስ ይላሉ። በርቱ አይዟችሁ። ሁሉም ያልፋልና አሁንም በዓላማ ያላችሁ ገፉበት ወደፊት የበለጠ ትደሰታላችሁ።

በአንፃሩ ደግሞ አንዳንድ ሞጭላፋዎችና እምነተቢሶች በፍቅረኛቸው ላይ ተጠቃሚ በመሆን ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላና ግሩም ደመወዝ ካገኙ በኋላ ጓደኛቸውን፣ እጮኛቸውን፣ ባላቸውን (ሚስታቸውን) የሚከዱና የሚክዱ ባለጌዎችንም አይቻለሁ፣ አውቃለሁም፣ አዝናለሁም። እግዚአብሔር ይቅር ይበላቸው ሌላ ምንም አልል። የንፁህ ፍቅር ጠንቆች ናቸውና ለወደፊቱ ታረሙ ሌላ ምን ይባላል?

ታዲያስ አንበሳው ወገኔ ጉዳዩ እንዴት ይታይሃል? የሆነውስ ሆነ የተፈፀመውስ ተፈፀመ ያለፈውስ አለፈ ለወደፊቱ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ታስባለህ? ታልማለህ?

ፍቅር እንደሆነ ላወቀበት የማይጠገብ የማያልቅ ዘለዓለማዊ ደስታን ክብርን የሚሰጥ ንፁህ ስጦታ መሆኑን እናውቃለን።

ይህንን ፀጋ ለማግኘት ደግሞ በመጀመሪያ ራሳችንን የልብ አፍቃሪና ተፈቃሪ መሆናችንን ከተረዳንና ማንነታችንን ካወቅን የት መድረስ እንደምንችል ማወቁና (መገመቱ) ቀላል ይሆናልናል።

እኔ በበኩሌ አገሩንና ዘመኑን ባህሉን የአሁኑን የአዲሱን ትውልድ የፍቅር አስተሳሰብ ስመለከተው ትልቅ ለውጥ አይቻለሁ። ያም ቢሆን ግን ፍቅር ፍቅር ነው። አያስፈራኝም፤ ደስታ ነውና።

ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት በወቅቱ የቀድሞውን ባህላችን ከአዲሱ ባህል ጋር በማዋሃድና በማገናዘብ ራስን ዘመናዊ (Moderate) ማድረግ ትዳርንና ቤተሰብን በጊዜውና በወቅቱ መስርቶና ራስን ተክቶ የወለዱትን ልጅ ደግሞ በሥነሥርዓት በማሳደግ ራስንም ሆነ ልጆቻችንን ለቁምነገር ማብቃቱ አስፈላጊ ነው።

ወገኔ በዚህ ዓለም ላይ ስንኖር ከዚህ የበለጠ ደስታና ቁምነገር የለምና የተፈጠርነውም ለዚህ ስለሆነ ከአሁኑ አእምሮአችን አሰባስበን ጓደኛ ለመያዝ እጮኛ በማድረግ የተከበረና የተቀደሰ ጋብቻ ለመፈፀምና ልጆች በማፍራትና ለቁምነገር በማብቃት የተከበረና የተመሰገነ ቤተሰብ ለመፍጠርና ለመተካት የምድርንም የኑሮ ኃላፊነት እንወቅ። ይህንን የተቀደሰ ተግባር ለመፈፀም ከዛሬዋ ዕለት ጀምረን ቃልኪዳን እንግባ። እስቲ አስቡት። ተጨፈረ ተጨፈረ ዞሮ ዞሮ ያው ነው። ከጭፈራው ጋር ዕድሜንም የወደፊቱን ማሰብ ያስፈልጋል። እስቲ ለጥቂት ሰኮንድ ስለአለፈው የፍቅር ሕይወታችን ወደኋላ እናስብ ጓደኛ (Girl Friend or Boy Friend) አለን። እጮኛ አለን ሚስት ወይም ባል አለን። ልጆች አሉን። ምንድንስ ነው የወደፊቱ ዓላማችን? በሥርዓት አግብተንና ወልደን ራሳችንን መተካቱ የተፈጥሮ ግዴታም ጭምር አይደለምን?

በዚህ ቅዱስ ዓላማና ሃሳብ ሙሉ በሙሉ እንመን ላመንበት ዓላማ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተገዥዎች እንሁን።

ከላይ ከጠቀስኳቸው ሁኔታዎች የሚመጣው ፍቅርና ጋብቻ ደግሞ የእግዚአብሔር ክብርና ፀጋ ይጨመርበትና ዘለአለማዊውም ይሆናል። አትጠራጠሩ ብቻ እኛ እንበርታ ወደፊት እንበል። የፍቅርንና የጋብቻን ጉዳይ እዚህ በአሜሪካንና በአገራችን እንዲሁም በመላው ዓለም እናደበላልቀው በሰርጉም እንንበሽበሽ ነው የምላችሁ። ተግባባን አደራ አደራ የምላችሁ በከንቱ እንዳንቀር ዕድሜአችንን በከንቱ እንዳያልፍ ከአሁኑ እንጠንቀቅና የምትሆነን (የሚሆነን) ላይ እናነጣጥር። መልካም የዘራ መልካም ያጭዳልና።

እንግዲህ በሚቀጥለው ጽሑፌ ላይ እስከምንገናኝ ድረስ መልካም የመተያየት የመጠናናት የመግባባት ብሎም የፍቅርና ጋብቻ ዘመን እንዲሁም የተሟላና የተሳካ የኦሎምፒክ ዝግጅትም ይሁንልን።

ውብና ጤናማ የሆኑ ልጆች ወልደን ለመሳምና ለማቀፍ ያብቃን አሜን።

የእናንተው ዮሐንስ ገብረሀይወት ገብረሚካኤል
ከውቧ የኦሎምፒክ ከተማ አትላንታ ጆርጅያ

# አዳም ና ሔዋን

አዳምና ሄዋን የተሰኘው አምዳችን የሚያተኩረው በተቃራኒ ጾታዎች መሃል በሚኖረው ግንኙነት ላይ ነው። የገጠመኝ ታሪኮችና አስተያየቶች የመሳሰሉት ይቀርባሉ— በእውነተኛ ገጠመኝ ላይ የተመሠረቱ የፍቅር ታሪኮችንም እናቀርባለን። አምዱን የመወያያና የመግለፃ አምድ ለማድረግ እንዲቻል አንባብያን አስተያየታችሁን እንጠይቃለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩት መሆኑ ይታወቅልን።

## ዕጣዬ

### ከአብርኽት

"ዕጣዬ" በተሰኘ ርዕስ አብርኽት (የብዕር ስሟ ነው) በስደት ኑሮዋ የገጠማትን በተከታታይ እያቀረበችልን ነው። ይህን አሳዛኝ የፍቅርና የስደት ታሪክ ለአንባብያን ስናቀርብ አቀራረቡን እንዲጥም ከማድረግ በቀር በታሪኳ ላይ የጨመርነው ሆነ የቀነስነው ነገር የለም። እሷ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር በስደት ላይ ናት።

## ክፍል 11

የእናቴ ልጅ እህቴ ፍርዷንና ውሳኔዋን ከሰጠች ቆይታለች። እንደዚህ ያለ አነጋገር ጭካኔ የተሞላበት ጥላቻ ይኖራታል ብዬ ገምቼም አላውቅ። ድሮ አገር ቤት የማውቃት እህቴ ሆና አልታየችኝም። ተለውጣለች ማለት ነው። አሜሪካ ይሆን እንዲህ ያስቀየራት?

"የገዛ እህቴ፣ የእናቴ ልጅ ከአድጊ አማራ ጋር ያውም እየተዳማን ትዳር እመሰርታለሁ ስትል መርዳት ቀርቶ መስማት አልፈልግም . . ." የሚለው አባባሏ የእህቴ የምፅላል አልመሰለኝም። እህቴን ተገን አድርጎ የሚያወራ ሰይጣን ነው የመሰለኝ። እህቴ ደግሞ መቼ ነው አማራ፣ ትግሬ ወዘተ . . . እያለች ማውራት የጀመረችው። ሥልጣኔ ወደሰፈነበት፤ የሰው ልጆች ዘር ሳይለዩ በጋራ ለዕድገት ከሚሯሯጡበት አገር ከመጣች ነው ወይስ ድሮም ከልጅነቷ ነበር? ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ፣ አገር ቤት የትምህርት ቤት የቀድሞ ጓደኞቿ እንዲያውም የቅርብ ጓደኞቿ አማሮች፣ ጉራጌዎች፣ ኦሮሞዎች እንደነበሩ ነው የማውቀው። ቀደም ሲል ያልታያት የዘር መለዮዋ አሁን ጎላ ብሎ የታያት ሥልጣኔ ካለበት አገር ስትመጣ ነው ብዬ ማመን አዳገተኝ። የምናገረው ጠፍቶኝ በእንባዬ ጭጋግ ውስጥ ሳያት መልኳ ሁሉ ልውጥውጥ አለብኝ። እህቴ መስላ አልታይ አለችኝ። ሊወርድ የደረሰውን የእንባዬን ጠብታ በለበስኩት ሹራብ ጫፍ ጠረግሁና:-

"ትብለፅዬ፣ ይህን የምትይው አንቺ ነሽ ወይስ ሌላ አልኳት፣ ወይኔ እኔ አላምንም?" አልኩኝ እንባ እየተናነቀኝ።

"እኔው ነኝ አብረኽት፤ ምኑ ነው ነው የገረመሽ" አለችኝ። ድምጿ ሁሉ የእህትነቱ ቃናውን እያጣ የሄደ መሰለኝ።

"ከመቼ ወዲህ ነው ደግሞ የዚህ ዓይነት ኋላ የቀረ አመለካከት ያመጣሽው?" አልኳት የምትለውን በናፍቆት እየጠበቅሁ፣

"ምኑ ነው ኋላ የቀረ" አለችኝ።

"እንዲያው ደግሞ እዚህ ያሉት የእኛ ልጆች ምን እንደሚሉሽ ያልሽው አልገባኝም" አልኳት። ጥያቄዋን መመለስ አቅቶኝ አልነበረም፣ እሷም የምሰጣትን መልስ አታጣውም ከሚል ነበር።

"እሱን መች አጣሽው። ይልቅስ ኋላ ቀር ያልሽኝ ምኑ ነው? እንዴት አማራ ታገቢያለሽ ማለቴ ነው?" አለች። የፌዝ አጠያየቅ መሰለኝ።

"ከወደድኩት ምንስ ቢሆን ምን? ዋናው ነገር ፍቅርና መተሳሰብ መስሎኝ" አልኳት።

"እንዲያው ከመሬት ተነስቶ ከጠላት ጋር ፍቅር ይያዛል እንዴ?"

"ማነው ጠላት ያደረገው?"

"አማራ ማለት ጠላታችን ነው። አልሰሜን ግባ በለው" ይባላል።

ያ ሁሉ ጦርነት ያ ሁሉ ግፍ ኤርትራ ውስጥ የሚካሄደው በማን ሆነና ነው፤

"ትብለፅ፤ አንቺ ነሽ ወይስ ሌላ ሰው" አልኳት። በእርግጥ ከልቤ ነበር ይህን ጥያቄ ያቀረብኩላት።

"አብረኽት እህቴ ነሽ፣ ያውም ታላቂቱ። ለአንቺ የሚሰማኝንና የማውቀውን አልደብቅም። አንቺም አላጣሺውም። እስቲ ትዝ ይበልሽ፣ አባዬ ምን ይለን እንደነበር። ከዚያም ወንድማችን ሄዶ የሚዋጋለት ዓላማ እኮ ነው። እንዴት አይገባሽም?" አለችኝ።

"ታዲያ ያ ከሰይፉ ጋር ምን አገናኘው?" አልኳት።

"የሰይፉ ዘሮች አይደሉም የሚወጉን?"

"የት ነው አንቺን የወጉት? አንቺ ተወልደሽ ያደግሽው አዲስ አበባ?"

"አፍንጫን ሲመቱት ዓይን ያለቅሳል ብለው አማሮች ሲተርቱ አልሰማሽም?

"እና ምን ለማለት ነው?" አልኳት

"እናማ በጦርነት እየጨረሱ ያሉት የእኛን ዘሮች ነው" አለችኝ። እህቴ እንደዚህ ያለ አስተሳሰብ ይኖራታል ብዬ ግምቴ ውስጥ ከትቼ አላውቅም። ይህን ባህሪ የፈጠረችው እዚህ አሜሪካ ከመጣች መሆን አለባት። ከሁሉ የገረመኝ ከእህቴ ጋር የነበረን አመለካከት ያው እንደድሮው አንድ ዓይነት ይመስለኝ ነበር። እዚህም መጥቼ እስከ ጥቂት ጊዜ ድረስ። አሁን ግን እንደዚህ መሆኗን ለማመን አቃተኝ።

"ከመቼ ወዲህ ነው ደግሞ እንደዚህ ፖለቲካኛ የሆንሽው?" አልኳት

"ይህ እኮ ፖለቲከኛ መሆን አይደለም። ለወገን ከመቆርቆር የመጣ ነው።" አለችኝ

"ኢትዮጵያዊ እንደመሆንሽ መጠን የምትቆረቆሪው ለሁሉም መሆን አለበታ?" አልኳት "መንግሥቱ የሚቀጠቅጠው ሁሉንም ነው እኮ!"

"አብረኸት በዚህ ነገር ብዙ ባንጨቃጨቅ ጥሩ ነው። እኔ በበኩሌ ሁሉ ነገር የተገለፀልኝ በቅርብ ጊዜ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ እኔ ወንድሜ ተሰልፎ እየተዋጋ ያለበትን ዓላማ፣ አባቴም የሚደግፈውን ዓላማ ከእነሱ የበለጠ አዋቂ ነኝ ብዬ ልተችና ልቃወም አልችልም። ብችልም አቅሙ የለኝም። አንቺም እያደር ሁኔታው ይገለፅልሻል።" አለችኝ ቁርጥ ያለ አነጋገር እንደሆነ ያስታውቃል። የገዛ እህቴን የእናቴን ልጅ ችግሬንና ዓላማዬን ነግሬያት ላሳምናት እንኳ አለመቻሌን ተገነዘብኩት ታዲያ ሰይፍዬ ሊቀር? ሕሊናዬ የማይቀበለው ጉዳይ ነው። የፖለቲካውን ክርክር አለማንሣቱ ጥሩ እንደሆነ ተረዳሁ። ለማንኛውም የሰይፉን ጉዳይ ብቻ ችላ እንዳትል አጥብቄ ልለምናት በማለት።

"ትብለፅዬ እሱን እንዳልሽው ሁኔታውን እያደር ልረዳ እችል ይሆናል። አሁን ግን የዚህን ልጅ ነገር አደራ ነው የምልሽ። በእናታችን ሞት ይዤሻለሁ። ለእኔ ሲል አገር ለቆ የወጣ፣ እናቱን እህቱን ጥሎ የወጣ እንዴት ሜዳ ላይ ልተወው?" አልኳት በማሳዘን። የሚያዋጣኝ መለማመጡ ብቻ ነው።

"ችግርሽ ይገባኛል። ማድረግ የሚቻልም ነገር ቢኖር እኮ እሱ ሲገኝ አይደለም? በደብዳቤ ቀርቶ በስልክ እንኳ ፈልገሽ ልታገኚው አልቻልሽም። እና እሱም ደግሞ አልፃፈ፣ አልደወለ፣ ምን ይባላል? ደግሞ የወንዶችን ነገር ታውቂያለሽ። "ከዓይን ሲርቁ ከልብ ይርቁ" ይላሉ አማሮች። የአንቺን ወደዚህ መምጣት፣ ብቻውን መሆን፣ ደግሞ ለአንቺ አልነግርም የሌሎች አማሮች ጓደኞቹ ምክር በአንድ ላይ ተጨማምሮ ዘግቶሽ ይሆናል" አለችኝ።

"ትብለፅዬ አንቺ እኮ ሰይፉን አታውቂውም። ይለወጣል ብዬ በፍፁም አልፈራም። እምነዋለሁ። የሰው ወሬ የሚሰማም አይደለም። ይልቅስ ጥፍት ማለቱ በጣም አሳስቦኛል" አልኳት።

"አውቆ የጠፋ ቢፈልጉት አይገኝም የእኔ እህት። ይህች ትግሬ ምን ልታደርግልህ ነው? የሚለው የጓደኞቹ ቅስቀሳ የሚቀር መሰለሽ? እና ለማንኛውም እሱ አውቆ ነው የጠፋው ብዬ ነው የማምነው" አለችኝ።

"እሱን ለእኔ ተይልኝ። ባይመቸው ይሆናል። አንቺ ግን በሚቻልሽ ሁሉ እርዺኝ አደራሽን" አልኳት።

"ለማንኛውም እስቲ ይገኝ። ይልቅስ አሁን ሥራ ብትጀምሪ ጥሩ ነው። ለዚህም የመኖሪያ ወረቀቱ ይስተካከልና ቶሎ ጀምሪ፣ እሱም መጣ አልመጣ አንድ ነገር መደረጉ አይቀርም።" አለችኝ።

ይህም ተስፋ ነው። ከእንግዲህ ጭቅጭቅ ማንሳት እንደሌለብኝ ተረዳሁ። የእህቴን ቁርጥ ያለ ሀሣብ ስላገኘሁ። በዚህ ላይ ደግሞ ያለሁት እቤቷ በመሆኑ መጠንቀቅ እንዳለብኝ ተረዳሁ። ከሷ ፈቃድ ውጭ መውጣቱ ብዙ ሊያወላዳኝ አለመቻሉን ተገነዘብኩ። ከዚያ በኋላ የሆዴን በሆዴ ይዤ ሥራ ለማግኘት የሚያስችለኝን የሥራ ፈቃድና የመሳሰሉትን ወረቀቶች እህቴ አግኝታልኝ በእሱ አማካይነት የመጣሁት አሜሪካዊው እስፖንሰሬ እንዲያወጣልኝ አደረገችልኝ። ጊዜ አልፈጀም። ወረቀቱ መጣ። ትንሽ የቋንቋው ጉዳይ ችግር ስለነበረብኝ የቋንቋ ትምህርት ቤት ገባሁ። ሥራም አንድ ሆቴል የጠራጊነትና እልጋ እንጣፊነት ሥራ ተገኘልኝ ብዙ ቋንቋ የማይጠይቅ ነበር። ሥራውን ጀመርኩ። ይህ ሁሉ ሲሆን ለሰይፉ ሳላቋርጥ በየሳምንቱ ደብዳቤ እጽፍ ነበር። ሙያ በልብ ይባል የለ። ሥራ እየሠራሁ ገንዘብ ማጠራቀምና ሰይፉ የሚመጣበትን ሁኔታ ማመቻቸት እነኚህ ሁለቱን ቅድሚያ የምሰጣቸው ነገሮች ሆኑ።

መቸም የማይለመድ ነገር የለም። ሥራውም እየለመድኩት መጣሁ። በጠዋት ሥራ እገባለሁ፣ እዚያው ውዬ ማታ ቤቴ እመለሳለሁ። እህቴ በመጀመሪያ አካባቢ ሥራ ታደርሰኝና ትመልሰኝ ነበር። ኋላ አውቶቢስና ባቡር መያዙን ለመድኩና ራሴው መመላለስ ጀመርኩ። በምሰራበት ሆቴል ብዙ አበሾች ተቀጥረው ስለሚሰሩ ከአንዳንዶቹ ጋር ለመተዋወቅ ቻልኩ።

ከሁሉ ቀደም አድርጌ የተዋወቅኳት አበራሽ የምትባል ልጅ ነበረች። ሥራዋ ከእኔ ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ከእሷ ጋር በቀላሉ ልተዋወቅ ቻልኩ። አበራሽ እንደኔው የመጣችው ከሱዳን ነበር። በአንድ ቤተክርስቲያን ስፖንሰርሺፕ ከሌሎች ጓደኞቿ ጋር ነበር የመጣችው። ዕድሏ የተሳካ ሆኖ አብራው ሱዳን ለረዥም ጊዜ የኖረችው ቦይፍሬንዷ ጋር ነበር የመጣችው። ከእኔ አንድ ዓመት ያህል ቀደም ብላ ነው የገባችው። እዚህም እንደመጡ ከዚሁ ጓደኛዋ ጋር ተጋብተው አብረው ነው የሚኖሩት። ከኢትዮጵያ አመጣጧ ከጎንደር ክፍለ ሀገር በመሆኑ ትንሽ ትንሽ ትግሪኛ ትሞክራለች። እዚያ ከሚሰሩት ሁሉ በንፅህናና በደግነት ያለፍርሃት ቀርባኝ የተዋወቅኳት እሷ ብቻ ነበረች። አንድ ሁለት የኤርትራ ልጆችም እዛው ሆቴል ሌላ አካባቢ የሚሰሩ መጥተው ተዋወቁኝ። እህቴን እንደሚያውቁትና ችግር ከገጠመኝ እንደሚረዱኝ ገለፁልኝ።

መላመድ አይቀርም፣ ከሁሉም ጋር እየተላመድኩ መጣሁ። ከአበራሽ ጋር ግን በጣም ተቀራረብኩ። አንድ ቀንም ከሥራ መልስ ከቤቷ ወስዳ ከባሏ ጋር አስተዋውቃኝ ጋበዘችኝ። ኑሮአቸውን በተለይ ደግሞ መፈቃቀራቸውን መተሳሰባቸውን ስመለከት ለአፍታ ሰይፍዬ ትውስ አለኝ። መቼ ይሆን እኔም ሰይፍዬ መጥቶ በዚህ ዓይነት የምኖረው ብዬም አሰብኩ። ሁልጊዜ በሃሳቤ የማይለየውን የእኔንና የሰይፉን ሁኔታ ለአበራሽ ለማጫወት ፈልጌ ነበር። ግን ትንሽ መቆየቱን መረጥኩ። ሀሳብ የሚካፈል ሰው ማግኘትን የሚያህል ነገር የለም። አበራሽ እቤቷ ከጋበዘችኝ በኋላ የበለጠ ተቀራረብን ብዙ ነገሮችንም መወያየት ጀመርን። በአብዛኛው የምናወራው የኑሮ ጉዳይ ነው። የፖለቲካም ወሬ ሆነ ተመሳሳይ ነገር በፍፁም አናወራም።

ቀደም ሲል ሥራ እንደጀመርኩ አካባቢ እኛ ሆቴል ከሚሰሩት ከተዋወቁኝ የኤርትራ ልጆች አንዱ የበለጠ እኛ ወደምንሰራበት አካባቢ መመላለስ ጀመረ። እየመጣም ሰላምታ እየሰጠኝ ትንሽ ያዋራኝና ይሄዳል። ስሙም ኃይለ ይባላል። ኃይለ ከአኳኋኑ ዓላማውን መረዳት አላዳገተኝም። እኔን ማውጣት እንደሚፈልግ ገና ከመጀመሪያው ነው ያወቅሁበት ቢገርማችሁም ባይገርማችሁም ወንዶች አንዲት ሴት ሲፈልጉ ገና ሳይናገሩ ሴቶች ያውቁባቸዋል። እና የኃይለን ሁኔታ እንደተረዳሁ (ምንም በቃሉ አፍ አውጥቶ ባይነግረኝም) ጥያቄውን እንዳያነሳ መንገዱን የምዘጋበትን ሁኔታ መሻት ጀመርኩ። በእህትነት የበለጠ እቀርበውና ስለራሴ የግል ጉዳይ አጫውተው ጀመር፣ በአብዛኛው የምነግረው ነገር ዝምብዬ ነው ያልሆነ ያልተፈጠረውን። ቢገባው ብዬ በወንድምነት እንደማየው ብዙ ምልክቶች ሰጠሁት። ችግሩ ደግሞ በወንድምነትም የሚቀርቡት አይደለም።

ወሬውና ጉራው ችክ ይላል። ወሬው ለዛ የለውም። ከእኔ ቀደም ብሎ የመጣ በመሆኑ ይህንኑ እንደትልቅ ነገር በመቁጠር አንድ ትንሽ ወሬ ስንጀምር ይህን ሳያነሳ አይቀርም። በምናወራው ወሬ ሁሉ መሀል ስለእሱ ሁሉን ነገር አዋቂነት፣ ስለእሱ ዘመናይነት፣ ስለሌላው አላዋቂነት፣ ስለሌላው ኋላ ቀርነት አንዳንድ ነገሮች ጠቀስ ያደርጋል። "ጉራ በኪሱ" የሚባለው ዓይነት ነው። እንዲሁ እንዲሁ እያለ አንድ ቀን ነገሩን አነሳው።

በምሳ ዕረፍቴ ሰዓት እምበላበት ቦታ ድረስ ምሳውን ይዞ መጣና ቁጭ አለ። መቼም ሁኔታው ያስቃችኋል። አሜሪካኖችን ለመምሰል ሲል የሚያደርገው ነገር ሁሉ እንደሚያስጠላበት ማንም የነገረው አይመስልም። አበላሉ፣ ውሃ አጠጣጡ፣ አንዳንዴም አካሄዱ። ታዲያ ያቺ ቋንቋ ትመጣና ጉድ ታደርገዋለች። እዚያ ላይ ችግር እንዳለበት ስለሚያውቅ ብዙ አይገፋበትም። ከትግሪኛው በርከት ያደርግና አልፎ አልፎ የእንግሊዝኛ ቃል ጣል ያደርጋታል። አቤት ታዲያ እንግሊዝኛዋ! "የ"ን በ"በ" ድምፅ ሲጠራት ትደብራለች። ታዘቡኝ እንጂ የተሰማኝን ከመናገር አልቆጠብም። ምናልባትም ጥምድ ስላደረግሁት ይሆናል ሁኔታው ሁሉ የማያምረኝ። እኔን ሲቀርብ ደግሞ እንደፈረንጆቹ ልሁን ባይነቱ ነው የገረመኝ።

"የሚቀጥለው weekend ምን ሥራ አለሽ? አለኝ በወሬ መሐል።

"ለምን ማወቅ ፈለግህ?" አልኩት

"አንድ ጓደኛዬ ቤት ባርቲ (Party መሆኑ ነው) አለ" አለኝ።

"ቢኖርሳ!" አልኩት

"ልጋብዝሽ ነው" አለኝ

"ምንድነው የምትጋብዘኝ?" አልኩት። ሳይገባኝ ቀርቶ ሳይሆን ፋራ ለመምሰል ነው። ደስ ይበለው።

"ባርቲ ነው፤ ባርቲ አታውቂም?" አለኝ እየሳቀ፤ አሳሳቁ አንድ ፋራ ስላገኘ የተገረመ መምሰሉን ያመለክታል።

"እኔ ባርቲ ሄጀም አላውቅ" አልኩት።

"አሜሪካን ከመጣሽ እንግዲህ መልመድ አለብሽ እኮ! እዮሽ ሙዚቃ አለ፣ ጥሩ ጥሩ ዘፈኖች በዚህ ላይ ዳንስ አለ። እንዴት ደስ ይላል መሰለሽ አለ። ዳንስ ምን እንደሆነ እየደነሰ ቢያሳየኝ በወደደ — አላውቅማ። "እኔ እንዲህ ያለውን ነገር አላውቅም" አልኩት። እንዴት አታውቅም ብሎ እንደጠረጠረ ይገርመኛል። ከአገር ቤት የመጣ ሰው ሁሉ አሜሪካን ብዙ ካልኖረ ጥሬ ነው ብሎ ከሚያስቡ ወገኖች እንደሆነ ተረዳሁ። የጥሬና የብስል መለኪያው ብዙ መቆየት አለመቆየት ብሎም ዳንስ መቻል አለመቻል ብሎ ነገር አይገባኝም። መቼም ገብቶኝ አያውቅ። እንኳን ያኔ ገና ብዙ ጊዜ ሳልቆይ አሁንም ቆይቼ ቢሆን ይህ ነገር ግራ ይገባኛል። አንዳንዶቹ ጭንቅላታቸው ውስጥ ልጥፍ ብሎ የተጋገረ ነገር ሆኖ ይህ አለመሆኑ በአንዳንድ ሁኔታዎች ግልፅ እያለ ሲመጣ እንኳ Realityውን መቀበል አይፈልጉም። ኃይለ ከእነኚህ ሰዎች የሚደመር ነው። ■

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

# « እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ »

## ከአትናትዮስ

## ክፍል አምስት

የፍቅር ትርጉሙን ብዙዎች ተመራምረውበታል። ብዙ ተብሎለታል። ፍቅር ሲይዝ እንዲህ ያደርጋል፣ እንዲህ ይሰራል ብሎ ማለት ያስቸግር ይመስለኛል። ሃሣብ፣ ጭንቅ ጭንቅ፣ መንፈስ ረበሽ ረበሽ ይበል እንጂ አንድ ውስጣዊ ተስፋና ደስታ ይሰማል። እኔም እንግዲህ በአሰገደች ፍቅር መያዜ እያደር ይሰማኝ ጀመር። እንኳን አብራኝ ሳትሆን ይቅርና አብራኝም ሆና ትናፍቀኛለች። ቢመች በየቀኑ ቀርቶ በየሰዓቱ አብሬአት ብሆን ትልቁ ምኞቴ ነበር። ከአሰገደች ጋር ያለኝ ግንኙነት እንደገና እየጎለመሰና ለእሷ ያለኝም ስሜት እያደገ መምጣት ጀመረ። በሳምንት ሁለት ቀን አብረን ልንሆን ተስማምተን ስለነበረ እነኚያን ሁሉቱን ቀኖች በናፍቆት ነበር የምጠብቀው። እኔ ተፈጥሮዬ ሆኖና ስሜቴን መደበቅ አልችልም። ፍቀሬን አልደበቅሁዋትም። እንደምወዳት ብዙ ጊዜ ነግሬያታለሁ። እሷም እንደምወዳት አውቃለች። እኔኑቴን ለእሷ ፍቅር ተገዥ ላድርግ እንጅ እሷ መጀመሪያ ታሳየኝ ከነበረው ሁኔታ ትንሽ እየቀነሰ መምጣቱ ነው የሚሰማኝ። ምናልባት የእኔ ፍቅር እያየለ መምጣት የእሷ ግን ባለህበት እርጋ ሆኖ እኩል ባለመሄዱ ሊሆን ይችላል የሚልም ግምት አድሮብኝ ነበር። ያም ሆነ ይህ ግን ቻልኩት። ፍቅሬ እያየለ ለእሷ ያለኝ ስሜት እየጋለ መምጣቱ እንደተሰማኝ ለጋብቻ ልጠይቃት ወሰንኩ። ከመውደድ ሌላ ምን ልፈልግ። ይህን ጥያቄ ለማቅረብ (እንደፈረንጆቹ propose የማደርግበት) አንድ ቀን ጥሩ ከተባለ የፈረንጆች ሬስቶራንት ራት ጋበዝኳት። አሰገደች ዘመናዊ ናት ብዬ ስለማምን እንደአገሩ ባህል ይህን ጥያቄ የማቀርብበትን ምሽት ልዩ ላደርግ አስብኩና ከምግብ ቤቱ ልዩ ዝግጅት አደረግሁ። 'የማነህ ጉረኛ ፈረንጅ' እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ልዩ ጠረጴዛ ለሁለታችን፣ በመሃሉ ሻማ በርቶበት እኔ የገዛሁት አበባ እንዲቀመጥ፣ በተጨማሪ ራታችንን በልተን እንደጨረስን በስሟና በስሜ የተሰራ አነስ ያለ ኬክ እንዲዘጋጅ አደረግሁ። መቸም የምንኖረው አሜሪካ ነው። እንደአገሩ ሲሆን ያምራል። ደግሞ በፊልም እንዳየነው የጋብቻ ጥየቃ (Marriage Proposal) በዚህ መልኩ ሲካሄድ ውበት አለው። ውበት ብቻም ሳይሆን ታሪካዊነት ይኖረዋል። እና ይህን ያህል ዓመት በሚስት እጦት ስንከራተት ለነበርኩት እንደ ግለሰብ አሁን የምወዳትንና የማከብራትን ልጅ አግኝቼ ለጋብቻ ስጠይቃት ያንን ዕለት በትዝታ ካሜራ ብቀርፀው ምናለበት። ባዶ ከነበረው ሕይወቴ የመሸጋገሪያ ዋዜማ ዕለት ነውና ልዩ ክብር ይገባዋል። የምወዳት አሰግዬም ብትሆን ለእሷ ያለኝን ክብር፣ ለእሷ ያለኝን ፍቅር ገልፄላት ሳግባሽ ብዬ ስጠይቃት እንደማንኛውም ተራ ነገር መስማት የለባትም። አስግዬ ልዩ ክብር ይገባታል። ምክንያቱም እወዳታለኋ።

ከሳምንት በፊት ቀደም ብዬ የያዝኩት ቀጠሮ ነበር። መቸም እዚህ አገር ኖረን አይተነዋልና፣ ሴቶችም ይወዱታልና ጥያቄዬ surprise እንዲያደርጋት ስለፈለግሁ ፍንጩን አልሰጠሁዋትም። እና እኔ አንድ ሳምንት ያህል የተዘጋጀሁበት ምሽት ነበር። በዕለቱ ከምሽቱ 7:00 ሰዓት ላይ ከቤቷ ሄጄ በመኪናዬ ይዣት ሄድኩ።

"እንዴት ነው? ዛሬ ሽክ ብለሃል" አለችኝ መኪናዬ ገብታ ከተቀመጠችና ቀና ጎንበስ ብላ ካየችኝ በኋላ።

እርግጥ ዘንጬ ነበር የለበስኩት። ዕለቱን ለማክበር።

"አንዳንዴ አያስፈልግም ብለሽ ነው" አልኳት።

መልስም አልጠየቀችኝ። ዝም እንዳልን ደረስን። ሬስቶራንቱ ገብተን እንደተቀመጥን የእኛ ጠረጴዛ ከሌላው ተለይቶ የተዘጋጀ መሆኑን አላስተዋለችም ነበር። ትንሽ እንደቆየችና በተለይ የእኛ ጠረጴዛ ከሌሎቹ የተለየ የአበባ ጉንጉንና ትልቅ ሻማ እንዳለው ስታይ ግራ የገባት መሰለችኝ። እኔም ሁኔታዋን ለማጤን ትክ ብዬ አያት ስለነበር።

"ዛሬ ትንሽ ለወጥ ያልክ ይመስላል" አለችኝ

"ምኔ ተለወጠብሽ?" አልኳት

"ሁለመናህ፣ ደግሞ እኛ ያለንበት ጠረጴዛ የተለየ ይመስላል?"

"ተለየብሽ፣ አልመሰለኝም።" አልኳት

ራታችንን ቀደም ብዬ ያዘዝኩ ስለሆን አሳላፊዋ ስትመጣ የጠየቀችኝ ሌላ ነገር ነበር።

"ራት አሁን ይቅረብ ወይስ በኋላ?" አለች አሳላፊዋ

"የምንጠጣው ብታመጪልኝ" አልኳት

"ዛሬ ደግሞ የምንጠጣውም መጠጥ ዓይነት አይጠየቅም እንዴ?" አለች አሰገደች በመገረም

"ዛሬ አንጠየቅም። የልባችንን አውቀው ይሆናል?" አልኳት

"እባክህን ቀልድህን አቁም፣ ነቅቼብሃለሁ።"

"ምኑን ነው የነቃሽው?" አልኳት የጎሪጥ እያየሁዋት።

"የልደት በዓልህ ወይም የእኔ አይደለም፤ አንድ ደስ ያለህ ነገር አለ ማለት ነው። አገኘሁት አይደል" አለችና ፈገግ አለች።

"አውቀሻል" አልኩና እጄ ከጠረጴዛው ላይ ያለውን እጇን ያዝ አደረገ።

"ንገረኝ ምንድነው እሱ?" አለች

"አትቸኩይ፤ መጀመሪያ እንብላ" አልኳት

"ልገምት?" አለችኝ።

"እስቲ ገምቺ!" አልኳት "እኔ እንደሁ ኋላ እንጂ አሁን አልነግርሽም"

"ሥራህ ቦታ ይሆናል"

"ሥራዬ ቦታ ምን ሆነ?"

"ምናልባት የደመወዝ ጭማሪ፣ የሥራ ዕድገት፣ ልክ ነኝ?" አለች።

የሴቶች ባህሪ ይገርመኛል። አንድ ነገር ማወቅ ከፈለጉ ዕረፍት ነው የሚነሳቸው። መልሱን ሳልሰጣት አሳላፊዋ ጠርሙስ የወይን ጠጅ ከሚያማምሩ ብርጭቆ ጋር ይዛ መጥታ በመጀመሪያ አስቀምሳን በየብርጭቆቻችን ሞልታ ሄደች። ብርጭቆዬን አንስቼ "እሰግዬ። ለጤናችን!" አልኳት።

"እሷም አንስታ ለጤናችን! ምንም ባላውቀው እንኳን ደስ ያለህ" አለችኝ

አንዳንዴ ከተጎነጨን በኋላ "አወቅሁ ወይስ አላወቅሁም!" አለችኝ።

"አላወቅሽም! ከዚያ የሚበልጥ ነገር ነው። እባክሽ ራት እስክንበላ አትጠይቂኝ። ራት እንደበላን እነግርሻለሁ" አልኳት

"እንዳልክ" አለችኝ።

ራት ቀረበ፤ ቆንጆ ራት ነበር። በላን። እሷም ወደደችው። ራት እንደተነሳ የተዘጋጀው ኬክ ተሸፍኖ መጣ። ሆዴ ትንሽ ፈራ ቢልም ኬኩን የተሸፈነበትን ልባስ ሳነሳው መሐሉ የልብ ቅርፅ ግራና ቀኙ በእንግሊዝኛ የእኔና የአሰገደች ስም ታየ። ትክ ብላ አየችው። ቀና ብላ እኔን አየችኝ። ግራ የተጋባች መሰለች።

"ምንድነው እሱ!" አለች ዓይን ዓይኔን እያየች።

ከኪሴ አንዲት ትንሽ ሳጥን ብጤ ነገር አወጣሁና ከፍቼው በጥሩ ዋጋ የገዛሁላትን ቀለበት ወደ እሷ ጠጋ አደረግሁኝ። በመገረም መልከ አየችኝ።

"እሰግዬ ወድጄሻለሁ፣ በጣም ስለወደድኩሽ ፈቃድሽ ሆኖ ለጋብቻ ልጠይቅሽ" አልኳት። በፊልም እንዳየሁት እንደፈረንጆቹ ተነስቼ ከፊትለፊቷ ተንበርክኬ ባደርግሁ ኖሮ ብዬም አሰብኩ። ግን ኣላደረግሁትም። ቀለበቱን አላነሳችም።

እኔኑ ትክ ብላ እያየችኝ

"አልገባኝም" አለችኝ

"ምኑ?" አልኳት። ያልገባት ነገር እኔ ደግሞ አልገባኝም።

"ማለቴ ይህ ቀለበት ምንድነው?"

"ለአንቺ ነው?"

"እና"

"እናማ ስጦታ ነው"

"እሱ ገባኝ። ማለቴ የጋብቻ ቀለበት መሆኑ ነው?"

ግራ ገባኝ ጥያቄዋ "አይደለም፣ እሱ ስጦታ ነው። ለጋብቻ ያልኩት ደግሞ ጥያቄዬ ነው።"

"ቀለበቱን ተቀበልኩ ማለት ጋብቻውን እሺ አልኩ ማለት ነው?" አለችኝ

"አባባልሽ አልገባኝም፤ ቀለበቱ ማስታወሻ ነው። እሱ ስጦታዬ ነው።"

"እና እኮ ቀለበቱን አዘጋጅተህ የመጣኸው ለጋብቻ ልትጠይቀኝ ነው አይደል?" አለች።

ግራ ገባኝ። አሰገደች የዚህ ዓይነቱ አቀራረብ አዲስ ይሆንበታል ብዬ አላሰብኩም። ደግሞ አሜሪካ አገር የቆየች በመሆኑ ይህን መረዳት ያቅታታል የሚልም ግምት አልነበረኝም።

"እሰግዬ እንደነገርኩሽ ቀለበቱ ስጦታዬ ነው። የጋብቻው ጥያቄዬን ክብር ባለው መንገድ ላድርግ ብዬ ነው ይህን ምሽት ያዘጋጀሁት"

"ጥሩ የራት ግብዣ፣ ያማረ ቀለበት ስጦታ፣ ይህ ሁሉ አሰገደች በእነኚህ ነገሮች ተሞኝቼ ጋብቻን ያህል ነገር እሺ ትላለች ብለህ እንዴት ገመትከኝ?" አለች።

"አሰገደች አንቺን ለማሞኘት አይደለም፣ እንዴት እንዲህ ትያለሽ?" አልኳት።

"ወስነሃል እንጂ! አንተ ጨርሰሃል። ኬኩ፣ ልቡ፣ ደግሞ ስማችን ይህ ሁሉ ምንድነው?" አነጋገሯ ቁጣ ያለበት ይመስላል።

የምመልስላት ነገር ጠፋኝ። እስቲ ይታያችሁ። ጥሩ አደረግሁ፣ ጥሩ ሰራሁ፣ እሷን አስደሰትኩ ብዬ ያደረግሁት ነገር ያሳሰብኩትን ውጤት ሲያመጣ ምን እንደሚሰማኝ ሳይታያችሁ አይቀርም። ኬኩ፣ ልቡ፣ ስማችን ምን ማለት እንደሆነ ሳይገባት ቀርቶ እንኳ አይመስለኝም። ይህን ለመረዳት ትልቅ ዕውቀትና ዘመናዊነት አይሻም። ጥፋት አጥፍቶ እናቱ ወይ አባቱ የደረሱበት ሕፃን ዓይነት በፍርሃት አፍጥጬ አየሁዋት። እንደምንም መናገር ቻልኩ።

"አሰገደች የምርሽን ነው ወይስ የቀልድሽን? በእውነት ይህ ያደረግሁት ነገር ክፉት ሆኖ ነው እንዲህ የምትዪው? ወይስ ለጋብቻ አንቺን መጠየቄ አግባብ አይደለም ለማለት ነው?" አልኳት ግልፅ የሆነ መልስ ነበር የፈለግሁት።

"ምኔ ነው የሚቀልድ የሚመስለው? ቀለበት አዘጋጅተህ ኬክ አሰርተህ ስትጠብቅ ውሳኔውን ከእኔ ሳታማክር አንተው የጨረስክ ነው የሚያስመስልብህ። እኔ እንግዲህ እንደዚያ ነው የታየኝ።"

"አይደለም አሰገደች። እኔ በበኩሌ ውሳኔዬን ለመግለፅ ነው። ደግሞ ለአንቺ የሚሰማኝ ስሜት ከፍተኛ በመሆኑ እልባት ላብጅለት አውጥቼ አውርጄ ለጋብቻ ልጠይቅሽ ወሰንኩ። አጠያየቁ ደግሞ ትንሽ celebrated ቢሆን በማለት ነው ቀለበቱም፣ ኬኩም። በአንቺ ስሜት እኔ ወሳኝ ሆኜ አይደለም። ምናልባት ሁለታችን የምንረዳው አዝማሚያችን ወደዚያው ነው በማለት ነው።" አልኳት እንግዲህ ከዚህ በላይ ምን ልበል?

"ጋብቻ እንዲህ ቀላል ነገር አይደለም። ደግሞ በጣም ቸኮልክ። በደንብ የምንተዋወቅ አልመሰለኝም። እኔ ቢገርምህ የዚህ ዓይነት ነገር ታስባለህ ብዬ አልገመትኩም።" አለች ፍርጥም ብላ

"ምን ማለትሽ ነው?" አልኳት በመገረም፤

"በቃ አለ አይደል!" ዝም ብለን የምንወጣ እንጅ ልንጋባ አስበን የተገናኘ አይመስለኝም ለማለት ነው። የአንተን እንጃ እንጂ እኔ በፍፁም አላሰብኩትም።" አለች።

"ዝም ብሎ መውጣት የሚሉት ነገር እንኳ አይገባኝም። ከተዋወቅንና አብረን መውጣት ከጀመርን በኋላ መዋደድና መግባባት ሲመጣ ለዘላቂው relationship ማሰብ ይመጣል። የእኔና የአንቺም እንዲሁ መሰለኝ። ስለዚህ እኔ አንቺን ለጋብቻ መጠየቁ ሊገርምሽ አይገባም። እንዳልኩሽ የእኔን ስሜትና ዓላማ ገልጨልሻለሁ። የአንቺን ደግሞ ማወቅ እፈልጋለሁ።" አልኩኝ ቁርጥ አድርጎ መናገሩ የሚሻል ነው ብዬ በማሰብ።

"ስማ አትናትዮስ፣ የአንተን ዓላማ ነግረኸኛል። ለእኔ ያለህንም ፍቅር ገልፀህልኛል። እኔ ግን አንተን ማውጣት ስጀምር ለዚህ ነገር ማለት ለጋብቻ አስቤህ አይደለም። ከልቤ ልንገርህና እኔ ስለጋብቻ ሃሳቡም የለኝ። ገና ነኝ። ብዙ ዓላማ አለኝ። በቤተሰብ ኃላፊነት ከመያዜ በፊት ማድረግ የምፈልጋቸው ነገሮች ብዙ ስላሉ እነሱን መፈፀም አለብኝ። ስለስጦታው አመሰግናለሁ። ግን ጥያቄህን ለመቀበል በጣም ያስቸግረኛል። አልተዘጋጀሁበትም፣ አላሰብኩበትም።" አለች ኮስተር ብላ። "ይህ አባባሌ ሊያስዝንህ አይገባም። አንተ ስሜትህን የገለጽክውን ያህል እኔም ለመግለጽ መቻል ያለብኝ መሰለኝ። እና ከማግባቴ በፊት ብዙ ማድረግ ያለብኝ ነገር አለ። ቤተሰብ ስትይዝ ልጅ አለ። ልጅ ከመጣ ደግሞ መንቀሳቀስ የለም። በስሜት ብቻ ተገፋፍቶ የሚደረግን ነገር አላምንበትም።" አለች።

ዕጢዬ ዱብ አለ። በፍፁም ያላሰብኩት ነገር። ታዲያ ከእኔ ምንድነው የፈለገችው? ያ ሁሉ ዕቅድ፣ ያ ሁሉ ዓላማዬ በአንዴ አፈር ሲበተንበት ለአፍታ ውልብ አለብኝ። ታዲያ ከእኔ ምን ፈልጋ ነው? አብራኝ ስትወጣ የነበረው? ለብቸኝነቷ ማስታመሚያ ወይስ እኔን የወሲብ ስሜት ማርኪያ ብቻ ለማድረግ?

. . . ምን ልንገራችሁ? የምለው የምናገረው ጠፋኝ። ልለማመጣት ይሆን? ልለምናት ይሆን? እንዴት እንዲህ ያለ መልስ የሰጠ ሰው ሊመለስ ይችላል? ምን ማለቷ ነው? በዚያች ደቂቃ ውስጥ በአዕምሮዬ የተመላለሱት ነገሮች መቁጠር አልችልም። አንድ ነገር ራሴን የመታኝ ያህል ዥው አለብኝ። እንዴት ከአፌ እንደወጣ አላውቅም ብቻ።

"ጊዜ ስጠኝ ላስብበት ነው የምትይኝ አሰገደች?" አልኳት፤ ሊያለቅስ የደረሰው የድምፄ ቃና ለእኔም ለራሴ ተሰማኝ።

"እየነገርኩህ አትናትዮስ፤ እኔ ጋብቻ የሚባል ነገር በፍፁም አስቤም አላውቅ። ከእንግዲህም ለረዥም ጊዜ ያሰብኩትን ነገር እስካከናውን ድረስ ላስበውም አልፈልግ። እንዳው ከፈለግህ እንውጣ እንጂ . . ." አለች

"በቃ! ተይው ዓረፍተነገሩን አትጨርሺው። እንደው እንውጣ ማለት አይገባኝም። ለምን? ለሩካቤ ሥጋ እርካታ? ተይ አስገዬ ባይሆን ጊዜ ሰጥተሽው ብታስቢበት ጥሩ መሰለኝ። እወድሻለሁ። አንቺ እንደምትፈልጊው ልሆንልሽ እችላለሁ። ግዴለሽም ክፉ አይደለሁም" አልኳት ምናልባት ብትራራልኝ በማለት።

"አትናትዮስ፣ ጠልቼህ እኮ አይደለም። ቢገባህ ብጠላህ ከአንተ ጋር አልወጣም ነበር። ግን እኔ ለጋብቻ ገና ነኝ።"

ገና ማለት ስንት ይሆን? ዕድሜዋ ሰላሳ ቢያንስ እንጂ አይበዛም። እና ትክ ብዬ አየሁዋት፣ እሷም አየችኝ።

"በቃ ይኸው ነው መጨረሻው የእኔና የአንቺ ነገር?" አልኳት።

"ከፈለግህ ዝም ብለን እንውጣ" አለችኝ በድጋሜ ትክ ብላ እያየችኝ።

አልገባኝም። ለማንኛውም ኬኩ ሳይቆረስ በመጠቅለያ አስጠቅልዬ ሂሳባችንን ከፍዬ ወጣን። ዝም ብለን ለመውጣት። ዝም ብሎ ነገር፤ አለ አይደል?

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

# ስ ፖ ር ት

## እንደጥንቱ

ከዮሐንስ ገብረ ሕይወት

በቅርቡ በሳንዲያጎ ከተማ በተደረገው የመላው አሜሪካና ከአውሮፓ የመጡ ስፖርት ክለቦች ውድድር ላይ የአትላንታው እግር ኳስ ቡድን ሁለተኛ መውጣቱን ሁላችሁም ሰምታችኋል።

እንዲሁም ለተደጋጋሚ ዓመታት በተደረጉት ውድድሮች ላይ ቡድኑ ሁለተኛ ሲወጣ ቆይቶ ባለፈው ዓመት በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ በተደረገው የዋንጫ ውድድር የአሸናፊነት ደረጃ በማግኘት የዋንጫ ባለቤት ሆኗል።

በተጨማሪም በአትላንታ ከተማ በሚገኙ ክለቦች መካከል በተደረገው የጥሎ ማለፍ ውድድር በማሸነፍ የዋንጫ ባለቤት ሲሆን እስቴቱን በመወከል በናሺቪል ቴኒስ በተደረገው የዞን ውድድር ላይ ሁለተኛ በመውጣት የሚያስመሰግን ውጤት ይዞ ተመልሷል። እንዲሁም ለእስቴቱ ምርጥ 1ኛ) አፈወርቅ ከበደ(ካቻ) 2ኛ) ዳንኤል ክፍሌ 3ኛ) ጎላ ብርሃኑ 4ኛ) ቻላቸው መልሰ 5ኛ) መኮንን ጉርሙ በማስመረጥ ከክለቡ የሚፈለግበትን ድርሻ አበርክቷል።

እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ በስፖርት ያደግኩ ነኝ። እንዲያውም በስፖርት ሙያ በአገር ቤት ለብዙ አመታት ሰርቻለሁ። የእግር ኳስ ጨዋታን እጫወታለሁ፣ እወደዋለሁም ሌሎቹንም ስፖርቶች ከማዘውተሬ በተጨማሪ የስፖርትም ቤተሰብ ነበርኩ።

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ የቡድኑን ሁለተኛ መውጣት ወይም የእኔን ስፖርት ባለሙያነት ለመግለጽ ሳይሆን ይህንን በኢትዮጵያ ብሄራዊ፣ ተስፋና ወጣት ቡድን የተገነባ ታዋቂ ተጨዋቾች ያሉበትን ቡድን እንዴት በሚቀጥለው ዓመት በዋሺንግተን ዲሲ ከተማ በሚደረገው ውድድር ላይ የዋንጫ ባለቤት ማድረግ ይቻላል? በሚልና ሌሎችንም ጠቃሚ ሀሳቦችንም ለማቅረብ ጭምር ነው። በመሰረቱ የቡድኑንና የኮሚቴውን አባላት የቡድኑን መሪዎች አሰልጣኙንና ተጨዋቾቹን እንዲሁም የቡድኑን ደጋፊዎች አውቄአቸዋለሁ። ባለፈውም ጊዜ ቡድኑ በሳንዲያጎ ውድድር ዝግጅትና ልምምድ ሲያደርግ አብሬ ልምምድ በማድረግ ገምግሜዋለሁ። በወቅቱ በቂ ዝግጅት አላደረጉም እንዲያውም ካገኙት ውጤት የተረዳሁት ነገር ቢኖር አንደኛ ቡድኑ ውስጥ ባሉት ተጫዋቾች ብስለት ምክንያትና ቀድሞ በመተዋወቅ የተገኘ ውጤትና የሌሎች ተወዳዳሪ ስቴቶች ከአትላንታው ቲም ባነሰ አቋም ላይ መገኘት እንጂ ቡድኑ እንደዝግጅቱ ሁለተኛ መውጣቱ በጣም የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ነው።

ይህንን ያስኘኝ ቋሚ ተሰላፊ ተጨዋቾች አንድ ላይ የታክቲክ ልምምድ (ቲም ወርክ) ሲያደርጉ አላየሁም። ለትንፋሽና ለአካል ብቃት የሚደረግ ልምምድ ሲደረግ አላየሁም የስነ ልቦና ዝግጅታቸው ዝቅተኛ ነበር።

እዚህ ላይ መረዳት ያለባችሁ ዋናው ቁም ነገር ድሮ በአገራችን የስፖርት ክለቦች እንደአሁኑ ሳይጠናከሩ ተጨዋቾች ለክለቦቻቸው፣ ለማሊያቸው ካላቸው ፍቅር የተነሳ በእግራቸው፣ በአውቶቢስ፣ በታክሲ እየተጓዙ በልምምድ ቦታቸው ላይ ከሰአቱ ቀድመው እየተገኙ በጭቃ፣ በዝናብና በፀሐይ ላይ እየተለማመዱ ከርቀት ቦታ በመምጣት በጃንሜዳ፣ በፖሊስ ሜዳ(አቫሲዮን)፣ በራስ ኃይሉ ሜዳ፣ በት/ቤቶችና፣ በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ እየተለማመዱ አሰልጣኞቻቸውን የቡድን መሪዎቻቸውን እንዲሁም ደጋፊዎቻቸውን እንደ አባቶቻቸውና እንደታላቅ ወንድሞቻቸው እያከበሩ ምን ዓይነት ስፖርታዊ ጨዋነትና ዲሲፕሊን ያሳዩን እንደነበር በወቅቱ የነበራችሁ ከመካከላችሁ አላችሁና መስክሩ?

በኋላ ነው ክለቦች ሲጠናከሩ የትራንስፖርት ሰርቪስ መኪና፣ የኪስ ገንዘብ፣ ስራና ህክምና የመሳሰሉት ነገሮች የተጀመሩት። ይህም ለስፖርተኛው የስነ ልቦና እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል።

ሁላችንም እንደምናውቀው ደግሞ በጥንት ጊዜኽ ሆነ አሁን አብሮ ኳስ የተጫወቱ ስፖርተኞች የሚተያዩት እንደወንድማማቾች መሆኑን እናውቃለን፣ እናያለንም። ይህም የሚያሳየን ስፖርት ምን ያህል ፍቅርና ህይወትም ጭምር እንደሆነ ነው።

ታዲያ ዛሬ በአሜሪካን አገር የስፖርት ትጥቁ እንደልብ፣ ምግብ እንደልብ፣ የትራንስፖርት ችግር የለም። ሁሉ ባለመኪና ከተማሪዎች በስተቀር ሁሉ ባለስራ በመሆኑ ገንዘብ ይከፈለኝ የሚል የለም። እንዲያውም ለስፖርቱ ማጠናከሪያ ከራሱ ገንዘብ የሚሰጥ ነው። አልፎ ተርፎ ከሚታየው የሜዳ ችግር በስተቀር ለዚሁም ዕድሜ ለፒድሞንት ፓርክ በክፍያ በቂ የልምምድ ቦታ እስካሁን ድረስ አለን። እንግዲህ በዋሺንግተንና በካሊፎርኒያ እንዲሁም በሌሎች እስቴቶች ያለውን የልምምድ ሜዳ ችግር ስናነፃፅረው አትላንታ በጣም እድለኛ ከሆኑት ክለቦችና እስቴቶች አንዱና ዋነኛ ነው።

ታዲያ ምንድነው ችግሩ? መፍትሄውስ? እኔ በእውነት ነው የምላችሁ ይህንን ቡድን በቋሚ መሰረት ላይ ለማኖር ከተፈለገ

ሀ) የቡድኑን ቋሚ ተሰላፊዎችና ተተኪ ተጨዋቾች ለልምምድና ለጨዋታ በሚያስፈልግና በሚያመች የስራ ፀባይ ላይ እንዲሰሩ ማድረግ፣

ይኸንን ማን ያደርጋል? ራሱ ተጨዋቹና የቡድኑ ደጋፊዎችና መሪዎች

ለ) ተተኪ ወጣት ተጨዋቾችን ከአሁኑ ከስር ከስር ማዘጋጀት።
ከየት? ከት/ቤቶችና ከኮሌጆች፣ ከዩንቨርስቲዎች መምረጥና ማዘጋጀት።

ሐ) በኮሚቴ አባላት በቡድን መሪዎችና አሰልጣኝ እንዲሁም በተጨዋቾች መካከል ስፖርታዊ የሆነ ቤተሰብነትን (የዕለት ዕለት ግኑኝነት) ማጠናከር፣ መከባበርና መፋቀር ይኖር ዘንድ አመቺ ሁኔታን መፍጠር እንደጥንቱ፣

መ) ለማንኛውም እንቅስቃሴ መፍትሄ ወይም መሰረቱ ገንዘብ እንደመሆኑ መጠን ከአባላት የሚደረገው ወርሃዊ መዋጮ ቋሚ የሚሆንበትን፣ በዓላትን በማዘጋጀት ገንዘብ የሚገኝበትንና ለቡድኑ ቋሚ የገንዘብ ምንጭ የሚገኝበትን (ስፖርት ክበብ) መፍጠር አስፈላጊና ወቅታዊም ነው። ይህ የስፖርት ማዘውተሪያ ያለበት ክበብ፣ ምግብ ቤት፣ ቡና ቤት በስፖርት ክለቡ ስም ቢከፈት ተጨዋቾቹ የቡድን መሪዎቹና እንዲሁም ደጋፊዎቹ ከነጓደኞቻቸው ከነቤተሰቦቻቸው በዚህ ቦታ ጊዜያቸውን ቢያሳልፉ እንኳ ቡድኑ በቋሚነት ከፍተኛ ገቢ እንደሚያገኝ እርግጠኛ ነኝ።

ሠ) ለወደፊቱ በአጭርና በረጅም ጊዜ ፕላን ለሌሎችም የውድድርና የቤት ውስጥ ጨዋታዎች እንዲሁም ጅምናዚየም የሚገኝበትን ሁኔታ በመፍጠር ህፃናት መጣቶች ሴቶች አባቶች፣ እናቶች በአባልነት በወርሃዊና በአመታዊ ክፍያ የሚመዘገቡበትና የሚሳተፉበት ሁኔታን ደረጃ በደረጃ መፍጠር ሲቻል ይህም መሳውን የአትላንታን ነዋሪ ጤንነት ለመጠበቅ ከማስቻሉም በላይ የስፖርት ቤተሰቦችን ያበራክታልና ከአሁኑ ይታሰብበት።

እንግዲህ ይህ ሀሳብ ምንም እንኳ በዚህ አትላንታ ለሚገኘው ስፖርት ክለብ የተሰጠ ይሁን እንጂ በመላው አሜሪካና አውሮፖ እንዲሁም ኢትዮጵያም ጭምር ለሚገኙ ስፖርት ክለቦች ዘር ሃይማኖትና ፆታ ሳይለይ ስፖርትን በስፖርትነቱ እንዒር ስፖርት ለሰላም፣ ለፍቅር፣ ለወንድማማችነትና ለአንድነት በሚለው መርሀ ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ ማጠናከር የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ እንደሆነ ይታየኛል።

በመጨረሻም የቡድኑ መስራች አባላት (የጥንቶቹ) ከአዲሶቹ ጋር በመሆን ፍቅርን አስተምሩ። ከላይ ጀምሮ እስከታች ድረስ ያሉትን የቡድን አባላት እንደ አንድ ሰው በመሆን ይህንን እድለኛ ቡድን የበለጠ ታዋቂ የሚሆንበትንና ለሌሎች ምሳሌ የሚሆንበትን ሁኔታ በመፍጠር በሚቀጥለው አመት በዋሺንግተን ዲሲ ከተማ በሚደረገው ውድድር ላይ የዋንጫ ባለቤት እንዲሆን ከአሁን ጀምሮ በንቃት እንሰራ። ካለበለዚያ ልክ እንደ ጤና ቡድን ጨዋታ ሲኖር ብቻ ተሰብስቦ መሄድና እርስ በእርስም አለመከባበሩ (መናናቁ) ቡድኑን ይጎዳዋልና ከአሁን ጀምራችሁ አስቡበት። ■

## አዛውንትና ወጣት

ወጣት "ጥንት በእናንተ ጊዜ ብዙ ሰውና ወረት ነበርን?፡

አዛውንት "በእኛ ጊዜ ሰው ከፍቅር ጋር ብዙ ነበር። ገንዘቡም ትንሽና በቂ ነበር።"

ወጣት "በአሁኑ ጊዜ በወጣቶቹ ጊዜስ? ምን ይመስሎታል?"

አዛውንት "በእናንተ በአሁኑ ጊዜ፣ ፍቅሩ ትንሽ ገንዘቡ ብዙ ነቀዙ ብዙ ነው።"

ወጣት "ባቄላ የበላ ነቀዝ፣ ሽምብራም የበላ ነቀዝ፣ ስንዴና ጤፍም የበላ ነቅዝ እኩል ነውን?
አዛውንት "በግና በሬ እኩል ናቸው ማለትህ ነውን?"

ወጣት "በግና በሬ እኩል አይደሉም፤ በሬው በውፍረትም ሆነ በቁመት ይበልጣል።"

አዛውንት "ታዲያ እያወቅኸው ለምን ትጠይቀኛለህ? የድሮ ሰው ይሳሳታል ብለህ ነውን እኛ ውሉን መች እንስታለን?" ሲሉ መልስ ከሰጡ በኋላ

ወጣቱ "ሆ.ሆ.ሆ. የድሮ ሰው ለንግግር ማን ብሎት ይበሉ ይቅርታ ደህና ይሁኑ" ብሎ ተሰናብቷቸው መንገዱን ሲቀጥል፣

አዛውንቱ ብቻቸውን ትክዝ ብለው ይገርማሉ። "ይህ ልጅ ክፉኛ ጠየቀኝ . . .የዛሬ ሰው እስቲ ምን ቸገረው ባገኘው ነገር አምላኩን አመስግኖ እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም የመረዳዳት መንፈሱን አጠንክሮ ቢኖር . . ." አሉ በሆዳቸው።

አካሉ (ከሳን ሆዜ)

# እ ና ስ ላ ው

(ከሰይፉ መኩሪያ)

አንድ ተማሪ በስሌት ችሎታው ከጓደኞቹ አድናቆትን ሲያገኝ አስተማሪው ግን በተማሪው ጉብዝና ይበሽቅ ነበር። ጥያቄ በተጠየቀ ቁጥር መልሱን ከመቅፅበት ጠብ የሚያደርገው ይህ ተማሪ አስተማሪው ጥያቄ አቅርቦ ሌሎች ነገሮችን ለመስራት ገና ዞር ሲል መልሱን ወዲያው ስለሚነግረው ነበር አስተማሪው የሚበሽቀው።

አንድ ጊዜ ትንሽ ፋታ አግኝቶ የተማሪዎችን ፈተና ለማረም ጊዜ አገኛለሁ በማለት ለተማሪዎቹ ሂሳብ ጥያቄ አቅርቦ ገና ቁጭ እንዳለ ያ ጎበዝ ተሚሪ መልሱን ጠብ አደረገለት። (ጥያቄው ከአንድ እስከ መቶ ያሉትን ቁጥሮች ደምሩ የሚል ነበር።

አስተማሪው በመገረም ያንን ተማሪ እንዴት መልሱን ለማግኘት እንደቻለ ጠየቀው። "ቀላል ነውኮ!" አለ ተማሪው "አንድንና መቶን ደመርኩ። መቶ አንድ ሆኑ። ከዛ ደግሞ ሁለትና ዘጠና ዘጠኝን ደመርኩ። መቶ አንድ ሆኑ። ቀጠልኩና ሶስትንና ዘጠና ስምንትን ደመርኩ እነርሱም መቶ አንድ ሆኑ። እንግዲህ በዚህ አያያዝ ሐምሳ የሚሆኑ መቶ አንዶች ይኖሩኛል ማለት ነው። ስለዚህ መቶ አንድን በአምሳ ማባዛት ብቻ ነው" ብሎ መለሰለት።

------- // ------

ሌላው የስሌት ታሪክ ዘጠኝ ቁጥርን የሚመለከት ነው። ዘጠኝ ቁጥር "አስማታዊ ቁጥር" (Magic Number) በሚል የሚታወቅ አሐዝ ሲሆን ለዚህ መጠሪያ ምክንያት አለው።

ማናቸውም ቁጥር በዘጠኝ አባዝቶ የሚገኘውን ውጤት (በመደዳ) ቢደምሯቸው ተመልሰው ዘጠኝ ስለሚሆኑ ነው። ለምሳሌ 9x4=36 ሲሆን ሶስትና ስድስትን መደመር ውጤቱ ዘጠኝ ይሆናል ማለት ነው። ሌላ ምሳሌ 101x9=909 ሲሆን ዘጠኝ ሲደመር ዜሮ ሲደመር ዘጠኝ አስራ ስምንት ይሆናል። ከዛ በኋላ አንድና ስምንት መደመር ውጤቱ ዘጠኝ ይሆናል ማለት ነው።


------- // ------


## ፓይ!!

የሂሳብ ነገር አንዳንዴ አንጎልን ያዞራል። አንዳንዴ ደግሞ መንፈስን ያስደንቃል። አንድ ዙሪያ ክብ (Circle) በውስጡ የያዘው ሂሳብ ጉዳይ አስደናቂ ከሆኑት የሂሳብ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው። አንድ ዙሪያ ክብ (Circle) በውስጡ መሀል ነጥብ (Center) ዙሪያ ክብ (Circumference)፣ አጋማሽ መስመር (Diameter) እና የክብ ርቀት (Radius) ያዘለ ነው።

ጥንታዊ ግብፃውያን (አፍሪቃውያን ናቸው) በአንድ ዙሪያ ክብ የሚገኘውን አጋማሽ መስመር ከዙሪያ ክብ ርዝመት ጋር ሲያነፃፅሩት ግራ የሚገባ ውጤት አገኙ።

ለመረዳት እንዲቀል በእንግሊዘኛው እንጠቀምና የአንድ circle diameter ከcircumference ጋር ሲነፃፀር የተገኘው ውጤት እንዲህ ነበር። ዲያሜትሩን በCircumference = 3.142 Diameter ሆነ። እንግዲህ Pi በመባል የሚታወቀው የስሌት ፎርሙላ አመጣጡ ይህ ሲሆን Pi ደግሞ ራሱን የቻለ ታሪክ ይዞ ቁጭ አለ። ይኸውም ፓይ ማለት 3.14285 ... ወይም 22/7 ሲሆን የፓይን የመጨረሻ ማግኘት እስካሁን ድረስ ያልተደረሰበት ጉዳይ ይሆናል። ሃያ ሁለትን በሰባት ማካፈል ማለት ማለቂያ የሌለው የማካፈል ሂደት ስለሆነ ነው። አንዳንድ የታሪክ እና የስሌት መጽሐፎች እንደሚሉት ከሆነ የፓይን ውጤት ለማግኘት ዘመናዊና ረቂቅ በሆነ ኮምፒውተሮችን በመጠቀም የተገኘው ውጤት ማለትም ሃያ ሁለትን በሰባት ማካፋል 3.14285714285 ... እያለ በተከታታይ የሚቀጥለው የቁጥሮች ጋጋታ ከአንድ መቶ ገፅ በላይ መድረሱን ይናገራሉ።



# የላንዳፍታ አራት ዓመት ዕድገት

ቀደም ሲል በየሶስት ወሩ በኋላም በየሁለት ወሩ እየታተመች አራት ዓመቷን አገባዳ አምስተኛውን ይዛለች። እስካሁን አስራ ሰባት እትሞች አውጥታለች።



መስከረም 1984



መስከረም 1987

ያለፉትን እትሞች ለማዝዝ ለእያንዳንዱ እትም $2.50 ይላኩ።


ጥር 1986



የካቲት 1984

Name ______________________

Addresse ______________________

City ______________ St. ____ Zip ____________


ህዳር 1987



ሐ ምሌ 1984


ሰኔ 1985


መጋቢት 1986



ጥር 1987


መስከረም 1985


መስከረም 1986



ግንቦት 1986



ሚያዝያ 1987



ጥር 1985


ህዳር 1986


ሐ ምሌ 1986


ሐ ምሌ 1987

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

ለ6 ተከታታይ እትሞች
(Six Consecutive Issues)

| | |
|---|---|
| U.S. | $16.00 |
| Canada | $22.00 |
| Europe | $30.00 |
| Asia | $38.00 |
| Institutions | $40.00 |

**የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።**
**በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።**

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ
## LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________

PHONE ( _______ ) ______________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይሆንኑ ይጥቀሱ
ክፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $2.50 ነው።

**ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።**
Please, send my gift subscription to the following person.

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________

PHONE ( _______ ) ______________

**እባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።**
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

# አባይ ምግብ ቤት
# Abbay Restaurant



ከእሁድ እስከ ሐሙስ ከ 11:30 a.m. እስከ 11:00 p.m.
ዓርብና ቅዳሜ ከ11:00 a.m. እስከ 12:00 midnight (ራት)
የመዝናኛ ፕሮግራም እስከ 2:00 a.m.

ለሠርግ፣ ለቀለበት፤ ለክርስትና፤ ለልደትና
ለመሳሰሉት በልዩ ትዕዛዝ እናዘጋጃለን።




የተለያዩ ባህላዊ ምግቦቻችንን ይወዳሉ።
ብቅ ይበሉና እናስተናግድዎት።


በዕረፍት ቀናት ምሽት
የመዝናኛ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።
ደስ ሲላችሁ እኛንም ደስ ይለናል፤
ስለዚህም በመስተንግዶአችን እናስደስትዎታልን።

## AUTHENTIC ETHIOPIAN RESTAURANT

Have a spicy authentic Ethiopian dinner
and stay for the cultural entertainment on weekends.

3375 Buford Highway # 1050
Atlanta, GA
(404) 321-5808






1. ሰበቡ
2. እትት
3. ትዝታ
4. ጠይም
5. ሰላሌ
6. የሸበሉ
7. ፍቅር አነሠኝ
8. ወለላ
9. ሰኞ

aster CD $14.00
aster CASS $ 7.00




Ebo Poster $10.00
Actual size 18"x24"/Full color

# ባርከንስ ሬከርድስ

ኤቦን አቅርቦላችኋል።
አሁን ደግሞ በተጨማሪ
ካሴትና ሲዲዎችን፣
ፖስተሮችና
ከነቴራዎችን
ያቀርብላችኋል!!




1. ምኑ ተነካና
2. ኤቦ
3. ያለ ስሜ
4. የኔ ቆንጆ
5. ባለ ጋሪ
6. እስቲ ልኑርበት
7. የዋህ ልቤን
8. አሸወይና

Ebo CD $14.00
Ebo CASS $ 7.00



Aster Poster $10.00
Actual size 18"x24"/Full color




Aster Cap (Black/ Red) $10.00

Ebo T-Shirt $15.00
( L, XL) / Full Color




1. የዲ ጎሽ
2. ያሀ
3. ካቡ
4. ከዚራ
5. ባቲ
6. ተማወታ
7. ኢዮሃ
8. ብቸኛ

Kabu CD only $14.00

Make Check or money order payable to:

**BARKHANNS RECORDS**
**115 West California Blvd.**
**No. 450**
**Pasadena, CA 91105-3005**
**Tel: (818) 405-9071**
**Tel: (202) 828-3058**

## ORDER FORM

| ITEM | Price | Quantity | Total Price |
|---|---|---|---|
| aster CD | US$14.00 | | |
| aster CASS | US$ 7.00 | | |
| Kabu CD | US$14.00 | | |
| Ebo CD | US$14.00 | | |
| Ebo CASS | US$ 7.00 | | |
| Ebo T-Shirt (L / XL) | US$15.00 | | |
| Ebo Poster | US$10.00 | | |
| Aster Poster | US$10.00 | | |
| Aster Cap (B / R) | US$10.00 | | |
| | | | |
| Please add US$2.00/ item for shipping & | | Subtotal | |
| handling. Outside USA, add US$4.00/ item. | | Ship. & Hand. | |
| | | Grand Total | |

Name :
Address:

Phone :

**Ship Gift To:**

Name :
Address :

Phone :

# MRA'G TRAVEL

## ሚራኽ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*

ለአለም አቀፍና
ለአገር ወሰጥ ጉዞዎ አለንልዎ!

Excellent Service!
Special Fare!
Group Fare!

ገነት ፈቀደ
ፕሬዚዳንት
Genet Fekede
*President*

አስተማማኝ ጉዞ ወደ

አዲስ አበባ
አስመራ
ጆሀንስ በርግ
ቴላቪቭ
ኢየሩሳሌም
ፍራንክፈርት
ለንደን



92 Piedmont Ave N.E
Atlanta, GA. 30303
(404)577-4404 Fax (404)222-9305

# ላንዳፍታ

ኢትዮጵያዊ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት በአማርኛ
በየሁለት ወሩ የምትታተም

በሥራም ቦታ ሆነ በዕረፍት ጊዜ እንዲያው ላንዳፍታ ቁጭ ብንል እንድታሳውቀንና እንድታዝናናን የተዘጋጀች ናት። በአራት ዓመት ተከል ልምድ የብዙ ኢትየጵያውያንን ደምበኝነት አፍርታለች።
እርሶም ደምበኛ እንዲሆኑ ትጋብዝዎታለች።

*Name* ____________________

*Address* ____________________

*City* ____________________

*St* ________ *Zip* ____________________

Single Copy - $2.75 ($3.00 Canada)
Subscription Rates:
Six Issues - $16.00 U.S.
Canada: $22, Europe: $30.00 ,Asia: $38.00, Institutions: $40.00

## አምዶቻችን

"ዜናዎች"
"እናስተዋውቃችሁ"
"ኑሮ በአሜሪካ"
"የአሜሪካ ኑሮ ገጠመኞች"
እዳምና ሔዋን
"ልብ ወለድ"
"ስፖርት"
"የግጥም ጉባዔ"
"ለሳቅ ለፈገግታ"
"የስንጠረዥ ጨዋታዎች"

ላንዳፍታ
ታስተዋውቃለች!
ታስተምራለች!
ታሳውቃለች!
ታዝናናለች!
ታስቃለች!
ታጽናናለች!

*Landafta*
*P.O.Box 49301*
*Atlanta, GA 30359*
*Phone: (404)728-9122*
*E-Mail - mgessesse@aol.com*